# ራእይ፡ ምዕራፍ
# አምስት ክፍል ሁለት

... ዛሬ ማለዳ ጌታ አምላክ እንዴት ያለ መልካሙን ነገር እንዳደረገልን፡ መልካሙን ዜና ለመናገር፡ ወደ ተበርናክሉ ተመልሰን መጥተናል።

2 ባለፈው እሁድ ራእዩ ሲነገር፡ አብዛኞቻችሁ እዚህ ነበራችሁ (ወገቡ ላይ ስለተገደለው እባብ ሲነገር)፡ ያ ራዕይ እዚህ መድረክ ላይ ከተነገረ በኋላ በሃያ-አራት ሰዓታት ውስጥ ቃል በቃል ተፈጸመ። ጌታ አሰራሩ እጅግ ይደንቅ ነበር። አሁን አምሳ-ሁለት ዓመት ሆኖኛል፡ በሕይወቴ ሁሉ... ሳይፈጸም የቀረ አንድም አይቼ አላውቅም። የተፈጸመውም፡ በትክክል ቃል በቃል ነበር። እና እጅግ እረፍት፡ እረፍት ተሰምቶኛል።

3 አሁንም ይህ ሁሉ ስናገረው የነበረውን፡ ያ ክስ ሁሉ ይህ ነው። በርግጥ፡ ክስ አይደለም፡ ከቅን-ልብ፡ ፈሪሃ-እግዚአብሄር ካላቸው ሰዎች የመነጨ ነው፡ አገልግሎቴ ትንሽ ላቅ ስላለባቸው-... እጅግ መለኮታዊ ስለሆነባቸው ነው፡ በዚህም ምክንያት እኔ ኢየሱስ ክስርቶስ መሆኔን ማሰብ ጀመሩ፡ ይህም አነስ ያለች-... ዶክትሪን አስጀመረ። ይሁን እንጂ ወዲያው እንዲቆም ተደርጓል። ለዚህም ጌታ ይመስገን!

4 እኔ ከራሴ አውጥቼ በጌታ ፊት ባስቀመጥኩት እና ለጌታ አደራ በሰጠሁበት ቅጽበት፡ ወዲያውኑ ቆመ፡ በሃያ-አራት ሰአት ውስጥ ሁሉም ተጠናቀቀ። ትንሽ የመረበሽ እና የመበሳጨት ነገር ትቶብኛል፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ከዚያም እወጣለሁ። በእርግጥ ለእኔ አስደንጋጭ ነገር ነበር፡ ይሁን እንጂ በመልካም እና በጸና ሁኔታ እገኛለሁ።

5 እናም በዚህ ሳምንት ታላላቅ ድሎችን አስመዝግበናል፡ የሆነ ነገር ማሳወቅ እፈልጋለሁ።

6 አሁን፡ ጌታ የነገረኝን ባዳምጥ ኖሮ፡ ያ በጭራሽ ባልመጣ ነበር። ከአራት አመት በፊት ነግሮኛል። አሁን በዚህ ጉባኤ ውስጥ፡ ከኋላ አካባቢ ያለችው ባለቤቴም፡ ልጄም ተቀምጧል... ከጥቂት ጊዜያት በፊት እዚህ መድረክ ላይ ነበር፡ እና ሌሎች ብዙ ጊዜ ደጋግሜ ስናገር ሰምተውኛል፡ "ይህ የተሰወረውን የመለየት አገልግሎት ለአንዴ እና ለመጨረሻ የማደርገው አሁን ነው።" አያችሁ? እንዲህ ሆነ... ወደ አምላክ ቅርብ ሆኜ ለመኖር ጣርኩኝ፡ ይህን በማድረጌ፡ ከዚያም ሰዎች ማሰብ እስኪያቅታቸው ድረስ እንዲጣመሙ የሚያደርግ ነገር አመጣብኝ።

7 ሌላው ደግሞ፡ ያንን የገጠመን የግብር ጉዳይ ላይ፡ እኔ ጌታን ብቻ ባዳምጥ ኖሮ በዚህ ጉዳይ ላይ አንድም ቃል አያነሣብንም ነበር። ነገሮች እራሴ ባደረግኩ ቁጥር... እርሱን ባልታዘዝኩ ቁጥር ሁል ጊዜ ችግር ይገጥመኛል። በደንብ እያዳመጥኩት አብሬው ከተጓዝኩ!

8 እንዲህ ይሆናል... አገልግሎቱ ወደ ሆነ ነገር እስኪቀየር ድረስ መለኮታዊ ይሆንብኛል... አንዳንዴ ወደ ሌላኛው አድማስ እንዳልሄድ እፈራለሁ። አሁን፡ እንዲህ ለማለት ፈልጌ፡ አይደለም... ሁላችሁም... ይህን እንድትረዱኝ፡ እፈልጋለሁ፡ ማለቴ ከጌታ እጠፋለሁ፡ ከእርሱ ሸሽቼ እሄዳለሁ ለማለት አይደለም፡ ከአሁን በኋላ ግን ከሰው አእምሮ በላይ የሆኑትን መለኮታዊ ነገሮች መግለጽ አልፈልግም፡ እያችሁ፡ ለምሳሌ የሰውን ልብ እንደ ማንበብ የመሳሰሉ የመለየትና—እና የመሳሰሉ ነገሮች።

9 አሁን፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ጌታ በቸርነቱ ረድቶናል፥ የትንቢት ቃል ያለውን፡ ወንድም ኔቪልን አስነስቷል፥ እንደነ ወንድም ሂጊንቦታም የመሳሰሉና ሌሎች ብዙዎች ወንድሞች ፍጹም በሆነ መልኩ... በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ ስጦታዎችን፡ እና ተአምራቶችን የሚያደርጉ ናቸው።

10 እንደውም ምስክርነት ልንገራችሁ። እህት ኦፓል ዊቨር የተባለች ሴት ነበረች፡ ዛሬ ጠዋት እዚህ ቤተክርስትያን ውስጥ ከእኛ ጋር ትኑር ወይም አትኑር አላውቅም። እዚህ ነሽ፡ እህት ኦፓል? ምናልባት ላላያት—እችላለሁ። ኦህ፡ ብቻ፡ ከብዙ ዓመታት በፊት በካንሰር ለሞት ተቃርባ ነበር፡ ካንሰሩም ከሴታዊ እጢ ውስጥ ተነስቶ ወደ ኩላሊቷ ወጣ። እና ለመኖር አንድ ምሽት ብቻ ሰጧት፡ በጣም ተዳክማ ነበረች። ሄጄም ጸለይኩላት፡ ራእይም መጣ፡ ፍጹምም ተፈወሰች። ይህም ከአስራ አምስት ዓመታት በፊት ነው። ላለፉት ብዙ ዓመታት በመካከላችን ትገኛለች።

11 በቀደም አንድ ችግር ይገጥማትና... ጉሮሮዋ ክፉኛ ታምማ ከጉሮሮዋ ደም መፍሰስ ጀመረ። ወዲያውኑ ሐኪም ቤት እንድትታይ ሐሳብ ቀረበላት። (እና ካናዳ በነበርኩበት ጊዜ ነበር።) እና ወንድም ኔቪልን ጠራችው፡ ወንድም ኔቪልም ሄዶ ወንድማችንን ሂጊንቦታምን ይዞ ሄደ። ወንድም ሂጊንቦታም እዚህ ያለ አይመስለኝም፡ ዛሬ ጠዋት፡ ሊኖርም ይችላል። ወንድም ሩፐርት ሂጊንቦታም ከቀድሞ ባለአደራዎቻችን አንዱ ሲሆን፡ ጥሩ ወንድም ነው። አለ እንዴ? ስለዚህ ለሴቲቱ ሊጸልዩ ወጡ፡ ስለ እርሷ ሲጸልዩም... ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነ አላውቅም እንጂ፡ ደም እየፈሰሳት፡ ለቀናት፡ ለሁለት ወይም ለሶስት ቀናት፡ እና ዝም ብላ ደም ስትተፋ ቆይታ ነበር። ወንድም ነቪል ከጸለየላት በኋላ ግን አንዲት ጠብታ ደም እንኳ አልተፋችም። በትክክል።

12 ሁለት ያበጡ ነገሮች፡ ብቻ እብጠት ይሁን ምንም ይሁን በላይኛው የአፍዋ ጣርያ ላይ ነበሩ፡ በአፍዋ በላይኛው ክፍል ላይ ትልቅ እብጠት መሳይ፥ የተንጠለጠለ ነገር፡ ነበረባት። ከዚያን ጊዜ በኋላ አላረፈችም፡ መጠናቸውም... እሷ እንዳለችው፡ "የሂከሪ ለውዝ ግማሽ ያህሉ ነበር።" በአፍዋ ውስጥም—ረዘም ላለ ጊዜ፡ ለቀናት ቆይተው ነበር። እና ወንድም ሂጊንቦታም... ያንን የጀርመን ስም በደንብ ባልጠራውም፡ ወንድም ሩፐርት፡ ለዚያም ይቅር በለኝ። ለማንኛውም ግን፡ እ... ምናልባት ተሳስቼም ሊሆን ይችላል። ወይም፡ አይደለም፡ በልሳኖች የመናገርና ልሳኖችን የመተርጎም ስጦታ—እንዳለው አምናለሁ። እናም በዚህ ጊዜ፡ እጁን በፊቷ ላይ፡ ጫነባት። እና እንዲህ አለችኝ፡ "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ትናትናም አይደለም፡ ማታም አይደለም፡ ነገር ግን ወዲያውኑ ከቦታው ጠፋ" ከአፏ ጣሪያ ለቀቀ። ወዲያውኑ!

13 ስለዚህ ዶክተሮች መጡና፡ ጉሮሮዋን መረመሩ፡ ወዘተረፈ፡ "የጉሮሮ ካንሰር

ስላለባት ወደ ሆስፒታል መሄድ አለባት፡” አሉ።

14 በዚህም ምክንያት... ወደ ሆስፒታል ወሰዷት። እናም መልካሙን ፓስተራችንን፡ ወንድም ኔቪልን፡ እዚህ እስካገኘሁት ድረስ እዚያ እንዳለች አላወቅኩም ነበር፡ ወደ ሆስፒታል በመንገዴ ላይ ሳለሁ ያን ጊዜ ነገረኝ—እዚያ እንደነበረች ነገረኝ። እኔም ላያት ወጣሁ፡ ባሏም እዚያ ተቀምጦ ነበር። እና አምስት፡ አራት ወይም አምስት፡ ዶክተሮች ገብተው ምርመራ አደረጉ፡ ራሳቸውን እየነቀነቁ፡ “ይህ፡ በእርግጥ፡ ካንሰር ነው፡ የቫይረስ ካንሰር፡ ካንሰር ነው፡” አሉ።

15 ተለማማጁም ገባና—ናሙና ወሰደ። “ይህ፡ ያለ ጥርጥር፡ ካንሰር ነው፡” አለ።

16 እኔም አልኳት፡ “ግን’ኮ፡ እህቴ፡ እግዚአብሔር ከዚህ በፊት ከካንሰር ከፈወሰሽ... አሁንም ምንም ይሁን ምንም። ምናልባት እነዚህ ሰዎች ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ። እነርሱ—ካንሰር እንደሆነ ወይም ካንሰር እንደሚመስል ወይም ምን እንደሆነ ለማወቅ በዚያ መስክ የሰለጠኑ ሰዎች ናቸው። ማለት... ለዚያ ዓላማ የሰለጠኑ ሰዎች ናቸው። ስለዚህ ካንሰር ስለሚመስል ካንሰር ነው እያሉ ነው።” “በርግጥም እንደሱ ሳይሆን አይቀርም፡” አልኳት።

17 እሷ ግን ካንሰር እንደሆነ ማመን አልፈለገችም። ስለዚህ፡ አልኳት፡ “እግዚአብሔር የደም መፍሰሱን ለማቆም—በዚያ ጸሎትን ከሰማ፥ እግዚአብሔር እነዚያን ትልልቅ ነገሮች ከአፍሽ ለማስወገድ፡ ጸሎትን ሊሰማ ይችላል። ምንም ይሁን ምን፡ እግዚአብሔር እዚህ ማቆም አይችልምን? ”

18 “አሜን!” አለች፡ ባሏም በዚያ ተቀምጧል። እርሰዋም “አሁን ተሰፋዬ በዚያ ነው፡ እግዚአብሔር ያቆመው ዘንድ ነው፡” አለች።

19 እኔም ጸለይኩላት። እና ናሙናዎቹን ለመመርመር ከሄዱበት ተመልሰው መጡና “ነጻ” አሏት፡ ሁሉም ግን **ካንሰር** ነው ብለው ነበር። አያችሁ?

20 ስለዚህ ነገሩ፡ ወዳጆች ሆይ፡ እሱ አምላክ ነው ጸሎትም ይመልሳል። ስለዚህ እኛም በዚህች በትንሿ ተበርናክል እዚህ ስላገበኘን እጅግ ደስ ብሎናል። ለማየት ብዙም አይማርክም፡ ከብዙ አመታት በፊት፡ ተባብረን የለጣጠፍናቸው ቦርዶች ብቻ ነው፡ በጭንቅላታችን ላይ መጠለያ፡ ወይም፡ ጭንቅላታችንን ከዝናብ፡ እና ከበረዶ ወዘተ የሚከለክል ጣራ። ነገር ግን ብዙ ሰዎች ዛሬ እየኖሩ ያሉት በዚህ ጥረት ምክንያት ነው፡ ለዚህም በጣም እናመሰግናለን።

21 ባለአደራዎቻችን እናመሰግናለን። ዲያቆናቻችን እናመሰግናለን። ጉባኤያችን እናመሰግናለን። እና ስለ ፓስተራችን እናመሰግናለን። እርሱ ለቤተ ክርስቲያን ስለ ሰጠው ሰጦታ ሁሉ እናመሰግናለን። እናም ለእነዚህ ሰዎች ማስተዋልን እንዲሰጣቸው እንጸልያለን፡ እነሱ በተሳሳተ መንገድ በጭራሽ እንዳይሄዱ ነገር ግን በመንገዱ መካከል በትክክል እንዲጸኑ ይሰጣቸው። ከበሬታን ወይም ሌላ ነገር ፈጽማችሁ አትፈልጉ፡ ይህን ያደረጋችሁለታ፡ ወዲያውኑ መጨረሻችሁ ይሆናል፡ አያችሁ። ያ ሳይለያችሁ ትሁታን ሁኑ።

22 አሁንም፡ እንግዲህ ሰዎች፡ የታመሙና፡ የተጨነቁ ሰዎች ሲገቡ፡ ምናልባት አንድ ወይም ሁለት ዓመት እያረፍኩ ሳለ ጸሎት ፍለጋ ይመጣሉ፡ ስለዚህ እኔ

በእረፍት ላይ ሰሆን እግዚአብሔር ራሱ የራሱ መንገድ ያወጣል። አያችሁ? ኦህ፡ አይደንቅም ወይ? በዚህ ምክንያት... ልናመሰግን አይገባንምን? እግዚአብሔር እራሱን ያለ ምስክር አይተውም፡ እኛም በዚህ ደስ ይለናል።

23 አሁን፡ በዚህ በሚቀጥለው ሳምንት፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ አሁን ከትምህርት ቤት የወጡትን ሴት ልጆቼን በትንሽ የትምህርት ቤት የእረፍት ጊዜያቸው ለመውሰድ አላማ አለኝ፡ ስለዚህ እንድትጸልዩልን እማጸናችኋለሁ። ትልቋ ሴት ልጄ፡ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውሰጥ፡ ፖል ሬቭር እኩለ ሌሊት ጉዞውን ወዴት እንዳደረገ፡ እዚያ ቤተ ክርስቲያንን ለቆ የወጣበትን ቦታ ማየት ትፈልጋለች። እኛም... እዚህ በኒው ኢንግላንድ ውስጥ ነው እና እኛም ወጥተን ያንን ማየት እንፈልጋለን።

24 ከዚያም፡ የድሮ አይረንሳይድን ማየት ሁሌ እመኝ ነበር። ስለ **ድሮው አይረንሳይድ** ግጥም ሰንቶች ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? እኔ ከማውቃቸው ሌሎች ሁሉ ይልቅ ተወዳጅ እሱ ነው፡ ከክርስቲያን በቀር፡ ለኔ ምርጡ እሱ ነው። በቃ... ማንበብ ጀምሬ ሲተናነቀኝ፡ ትቼ ተቀመጥኩ፡ ዞር አልኩ ተመለሰኩ። እንዴት ይዋጥላችኋል... ልክ ለራስህ እና ለቤተሰብህ መተዳደሪያውን ከፈጠረላችሁ በኋላ ፈረሱን ወሰዳችሁ እንደመግደል አይነት ነው። እንደው—ያንን ማየት አልችልም። "ስለዚህ እሷን አጠፋታለሁ!" አይ፡ ያንን አታድርጉ። የብሪቲሽ መድፍ እየተተኮሰ ከአሮጌው የኦክ አጠገብ እየተፈናጠረ ሲመለስ፡ አውጥታችሁ ስታሰምጧት አ—አላየሁም።

ለንፋሱ አማልክት ሰጧት፡
ለመብረቁ እና አውሎ ንፋስ!

በጣም ይመቸኛል።

25 ስለዚህ ወደዚያ ለመሄድ ፈልገናል፡ በርግጥ ሚስተር ኬኔዲ አልጋበዘንም፡ ይሁን እንጂ በዚያ ቆይታችን ላይ ዋይት ሃውስን ማየት እንፈልጋለን። ለእነርሱ... ለልጆቹ ነው እንጂ እኔ ራሴ በተደጋጋሚ አይቼዋለሁ። ከዚያም ጌታ ቢፈቅድ፡ ወደ ቤት እንመለሳለን። ስለዚህ ጸልዩልን።

26 ወደ ቫኬሽን ስለወጡ ወዳጆቻችን እየጸለይንላቸው ነው፡ ብዙዎቹ ወደ ልዩ ልዩ ሰፍራዎች ጉዞ አድርጓል። እና አንዳንዶቹ ዛሬ ጠዋት ወደ ኬንታኪ፡ እና ቴነሲ እና ወደ ተለያዩ ቦታዎች ሄደዋል። ስለዚህ እንጸልይላቸዋለን።

27 አሁን፡ ሌላው እንደ ማስታወቂያ መናገር የፈለግሁት ነገር ነበረኝ። ኦህ፡ አዎን፡ የጥምቀት ስነ ስርዓት ከዚህ አገልግሎት በኋላ ወዲያውኑ ይደረጋል። ከዚያ በኋላም—ህጻናትን አደራ የመሰጠት ስነ ስርዓት የሚደረገ ይመስለኛል፡ የህጻናት አደራ ስለ መሰጠት፡ አንድ ወንድም እየነገረኝ ነበር። እና እንደገና ልንሰራቸው የሚገቡ ብዙ ነገሮች-... ምን አሉኝ? [አንድ ወንድም ሰለ ምሽት አገልግሎት ወንድም ብራንሃምን ጠየቀው—እርታዒ።] አይ፡ ሁለቱንም አገልግሎቶች ማገልገል አይስማኝም። አየህ፡ እኔ አንዱን አገልግዬ ወንድም ኔቪል ሌላውን ያገለግላል። ይህ አይገባኝም... አይደረግም... ሁለታችንም እዚህ እስካለን ድረስ፡ አንዳችን ብቻ ለምን እንሰራለን? ትክክል አይደለም፡ ወንድም ኔቪል? በትክክል ትክክል ነው።

28 ከዚያ፡ በመቀጠል፡ ዶክ አንድ ነገር አሳሰቦኛል-... ለተበርናክሉ ቃል የገባችሁትን፡ እንዳሳሰባችሁ ነግሮኛል፡ ይህም—ይህም ለቤተክርስቲያኒቱ...

ለቤተክርስቲያኒቱ በቂ የሆነ አቅርቦት ማግኘት ሲችሉ ወዲያውኑ ግንባታ ለማስጀመር በማሰብ ላይ ናቸው።

29 ስለዚህም እ—እኔ ደግሞ... የሆነ ነገር ያለ መስሎ ታየኝ፡ ስለዚያ ስለ ህጻናት አደራ መስጠት በነገርከኝ ጊዜ፡ ይህ የሆነ ይመስለኛል። ያ ነበር። ስለዚህ ይህ ጉባኤው ሲጠናቀቅ ወዲያውኑ ያንን እናደርጋለን።

30 አሁን፡ እነዚህ ልብሶች፡ እንዲጸለይላቸው የመጡ ናቸው፡ አይደል? በጣም ጥሩ፡ ወዳጄ። ያንን አንድ ላይ እናደርጋለን፡ ከዚያ በኋላ...

31 አሁን፡ ወደ ቃሉ ከማለፋችን በፊት... እስኪ በቃሉ ሰንቶች ተባርካችኋል? ኦህ፡ ማይ፡ በከፍታዎች ላይ አኑሮናል! አስተውላችኋል፡ በእግዚአብሔር መንገድ ማድረግ ምን ማለት እንደሆነ ካለፈው እሁድ ማየት ት—ትችላላችሁ። አያችሁ? በእነዚያ ውድ ወንድሞች መካከል የገባ መንፈስ እንዳለ ባየሁ ጊዜ፡ ጤነኛ ሰው ያንን መንገድ ይመርጣል ብሎ ማሰብ ይከብዳል። ስለዚህ ማድረግ ያለብን ብቸኛው ነገር አደራ መስጠት ወይም ለጌታ አሳልፎ መስጠት ነበር፡ እና በጥቂት ሰዓታት ሁሉም ነገር ተጠናቀቀ።

32 አሁን፡ ፓስተር (እኔ እሄዳለሁ)፡ በዚህ በጌታ ስራ ላይ ከአንተ ጋራ የአንተ ረዳት በመሆኔ፡ ጳውሎስም እንዳለው፡ "በእግዚአብሔርና በተመረጡት መላእክት ፊት እመክርሃለሁ፡" አየህ። እና ለዚህች ቤተ ክርስቲያን፡ አንድ ሰው በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ከሥርዓት ውጪ ሲሆን ምን መደረግ እንዳለበት ይህ ፍጹም ምሳሌ ነው። አያችሁ?

33 ስለዚህ፡ ትክክል ያልሆነ ነገር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲነሳሳ፡ ይህ ትክክል እንዳልሆነ የሚያውቅ፡ ያ ግለሰብ፡ ወደ ሰውየው ይሂድ። ሰውዬውም የማይታረቅ ከሆነ፥ ከዚያም የሚቀጥለው ነገር ምስክር ወሰደህ ሂድ፡ ምናልባት አንድ ወይም ሁለት ምስክሮች፡ እንዲታረቁ ወይም ነገሩን ለማስተካከል ወደዚህ ሰው ይሂዱ። አሁን፡ በደንብ ሰሙ! እንግዲህ፡ እየተቀዳም፡ ነው። ስለዚህ አሁንም ያ ካልጠቀመ...

34 ሌላ ጥቃቅን ኢዝሞች፡ ወይም እንደዚያ የመሳሰሉ ነገሮች፡ በመካከላችሁ የሚያድጉ መጥፎ ስሜቶች እንዲገቡ አትፍቀዱ። አሁኑኑ ከመንገድ አስወግዱት! ስለዚህ ያ ጥቃቅን... የወይኑን ፍሬ የሚያበላሽ ጥቃቅን ቀበሮ ነው፡ ታውቃላችሁ። ስለዚህ አስወግዱት! የሆነ ጥቃቅን ስሜት ሲሰማችሁ፡ ሂዱና ከሰውዬው ጋር ተነጋገሩበት። በሉትም፡ "እኔ—ሰቻለሁ። ስለ—አንተ የነበረኝ አሳብ፡ ወይም የሆነ ነገር ተቀይሮብኛል። ነገሩን ለማስተካከል፡ እንድጸልይበት እግዘኝ።" ምክንያቱም፡ በመካከላችን ያለውን ያልተበረዘ፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ብቻ እንጂ፡ ምንም አንፈልግም። እኛ የምንፈልገው ያ ብቻ ነው። ከዚያ ስጦታዎች እና ነገሮች በትክክል ይሠራሉ ሁሉም ነገር በትክክል ይቀመጣል።

35 አንድ ሙሉ ቤተ ክርስቲያን መሆን ስትችሉ ለምን ግማሽ ቤተክርስቲያን ትሆናላችሁ? ሰማይ በሙሉ እውነተኛ በሆኑ ነገሮች የተሞላ ሆኖ ሳለ እሱን የሚተካ ለምን ትፈልጋላችሁ? አያችሁ? እኛ ያንን አንፈልግም። ስለዚህ እዚህ ያላችሁ አባላት በሙሉ፡ አንዳችሁ ከሌላው ጋር፡ የተለየ ስሜት ሲመጣባችሁ ወደ ሰውዬው ሂዱ።

ንገሩት፡ "አየህ፡ እንዲህ አረጉኝ... "

36 ይህ... ማለት... እንግዲህ፡ አስታውሱ፡ “በወንድምህ ላይ ጥፋት ወይም ስህተት ሲኖርብህ” አይደለም፡ ነገር ግን “አንድ ወንድም **አንተን** ሲበድል ነው።” አያችሁ? ወደ እሱ ሂድና ታረቅ፡ በሱ ላይ እንግዳ ስሜት እንደተሰማህ—ከእርሱ ጋር ወዳጅ መሆን እንደምትፈልግ ንገረው፡ ጸልዩ ወደ መሰውያው ሄዳችሁ ነገሩን ከመካከላችሁ አርቁት።

37 አሁን፡ እዚህ ምድር ላይ እስክትጨርሱ ድረስ ሰይጣን ያለማቋረጥ ይመታችኋል። ያንን አትርሱ። በውጊያ ውስጥ ስለሆናችሁ፡ የማያቋርጥ ቡጢውን ያሳርፍባችኋል ጊዜም አይሰጣችሁም። ወደ ክርስቶስ የተጠራችሁት፡ ለሽርሽር ነው’ዴ? እንግዲህ፡ የማያቋርጥ ውጊያ ስለሆነ፡ በርግጥ ትደነቃላችሁ። ላለፉት ሠላሳ-አንድ ዓመታት መስክ ላይ ኖሬያለሁ፡ እና በየመንገዱ በእያንዳንዱ ኢንች ተዋግቻለሁ። እውነት ነው። እስራኤልም መንገድ ላይ እያንዳንዱ ኢንች ላይ መዋጋት ነበረበት። ፍልስጤም... ለእነርሱ—ተሰጥቷቸው ነበር፡ እሷን ለማግኘት ግን እያንዳንዱ ኢንች ላይ መዋጋት ነበረባቸው።

38 ስለዚህ፡ አሁን ይህን አስቡ፡ ምናልባት... ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ አንዳች ነገር ቢገባ፡ ፓስተሩ ራሱ እንዲህ ያድርግ... እናንተም—ወደ ሰውዬው ለመውሰድ፡ ፓስተሩን ማግኘት ካለባችሁ ያን ያድርግ። ከዚያም ያንን አልሰማም ካለ፡ በቤተ ክርስቲያን ፊት አቅርባችሁ በቤተ ክርስቲያን ፊት ንገሩ። ለመታረቅ ብዙ ጊዜ ስጧቸው፡ ምናልባትም ከአንድ እሁድ እስከሚቀጥለው። ቤተ ክርስቲያንን የማይሰሙ ከሆነ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል። “እንደ አረማዊና ቀራጭ ይሁን።”

39 ማለት፡ አያችሁ፡ በቤተ ክርስቲያን እስከተጠበቁ ድረስ፡ ሰይጣን ሊደርስባቸው አይችልም። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ከቤተክርስቲያን ጥበቃና ከክርስቶስ ደም ስታሰወጣቸው፡ ከዚያም ሰይጣን ይጠቀምባቸዋል። ያ እንደገና ወደ እርቅ ያመጣቸዋል። አያችሁ? ይህን ተ—ተረድታችኋል፡ አይደል፡ ፓስተር? አዎን፡ ጌታዬ።

40 ስለዚህ ሁል ጊዜ ማስታወስ ያለባችሁ ነገር ይህ ነው፡ መታረቅ፡ ወደ እግዚአብሔር ቀርባችሁ በእግዚአብሔር መንገድ መመላለስ። በእኛ ላይ...

41 ይህ ምን ያረጋግጥልናል? በዚህኛው ሰው ሥር ለሁለትና ለሦስት ዓመታት እንደሠራሁ የሚያውቁ ሁለት ወይም ሦስት ወንድሞቻችን ናቸው። ትክክል ነው። ነገር ግን ወደ አንድ ቦታ ስደርስ እንደ ሰዎቹ አሰብኩ፡ በመጨረሻም ከዚያ ነገር መለየት የሚያቅታቸውን እነዚያን ሰዎች በደንብ ወደድኳቸው። ከእኔ ጋር ምስክር ይዤም ሄድኩ። ወደ ቤተ ክርስቲያን ማምጣት ነበረብኝ። እናም ባለፈው እሁድ ከመድረክ ላይ ሆኜ፡ እንዲህ አልኩ፡ “ከእንግዲህ ወዲህ መስማት አልፈልግም። ከዚህ ነገር ነፃ ነኝ። ለእግዚአብሔር አሳልፌ ሰጠሁት፡ አያችሁ፡ ለእርሱ ሰጠሁት።”

42 ወዲያውኑ ሰዎቹ የተጠሩ መሆናቸውን ያሳያል። ይህም... እንግዲህ፡ እንደዚያ ባይሆኑ ኖሮ፡ በቅዱስ ቃል በተገሰጹ ጊዜ... አንድ ሰው በቅዱስ ቃል ተግሳጽ ሲገሰጽ፡ ከተቆጣና ከተናደደ፡ ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል አለመሆኑን ያሳያል። በትክክል! እውነተኛ የእግዚአብሔር ቅዱስ ሰው ግን ከእግዚአብሔር

ጋር በቃሉ ይታረቃል። ትክክል ነው። ቃሉም የተግሳጽ መንገድ ነው። እነዚያ ወንድሞች እግዚአብሔርን ያመሰግኑት ዘንድ ይገባቸዋል...

43 ተመልከቱ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል “በመጨረሻው ቀን ሐሰተኛ ክርስቶሶች ይነሣሉ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ።” ይሁን እንጂ አይቻላቸውም። አይቻልም፡ ጌታዬ። የተመረጡት አሰቀድሞ ተወስነዋልና፡ አይታለሉም፡ አያችሁ።

44 ስለዚህ ወዲያውኑ እነዚያ ወንድሞች... በማግሥቱ ወደዚያ ቤት መጡ፡ አያችሁ፡ መጥተውም የያዙት ቅዱሳን መጻሕፍት ይሰጡኝ ጀመሩ። ከዚያም መንፈስ ቅዱስ በቅዱሳት መጻሕፍት የተናገሩትን ሁሉ ይወቅሳቸው ጀመረ። አያችሁ? ስለዚህ ሰዎቹ፡ ነገሩን አዩት፡ እነዚህ የተመረጡ ሰዎች በእግዚአብሔር መገኘት ፊት ወጡ። ስለ እነዚያ አይነት ሰዎች እንዳመሰግነው ያደርገኛል። አዎን፡ ጌታዬ። ትክክለኛ ሰዎች ናቸው።

45 የተሳሳተ ሰው አግኝታችሁ፡ ስህተቱን ስታሳዩት፡ ክርስቲያን መሆን ሲፈልግ ስታዩት፡ እና ከፈቃዱ ወጥቶ፡ “አጥፍቻለሁ” ይላል። እውነተኛው ክርስቲያን—እሱ ነው።

46 ወዲያ ወዲህ የሚለው፡ እና የሚናደደው እንዲህም የሚለው ሰውዬ ግን፡ “አይ፡ እንዲህ ብሎ ነገር የለም፡” እና ከእንዲህ አይነቱ፥ ወንድሜ ሆይ፡ ተጠንቀቅ፡ ያን ጊዜ ከእኛ ወገን ሰላልሆነ ተፈርዶበት እንደ ወጣ ታያለህ። አንተ ግን፡ ፓስተር ሆይ፡ ከቃሉ ጋር ወግን እርሱም ዘወትር ያቃናልሃል። አንተ ግን በቃሉ ዘንድ ጽና።

47 አሁን፡ እኔ... ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ሰመጣ፡ከእንግዲህ—በመለየት ጸጋ የማላገለግልበት ምክንያት ይህ ነው፡ ያን ለማድረግ በፍጹም አላሰብም፡ በቀረው ዘመኔ ሁሉ፡ ወደ ባህር ማዶ እና ወደ ውጭ መስኮች ብቻ አሰባለሁ። እርግጥ ነው፡ እንደ ሰጦታ፡ ወይም እንደ ትንቢታዊ ሰጦታ፡ ሁሌም አለ፡ ነገር ግን እኔ ለራሴ ይዤ እሰራበታለሁ ምክንያቱ... አሁን በዚያ ቀን ውስጥ እጅግ ዘ—ዘግይተናል... ይሄዳልና። ወደ መጨረሻው ዘመን እጅግ ተቃርበናል። በውጭ መስኮች ግን አንድ ወይም ሁለት ጉዳዮችን ከአየሁ በኋላ፡ ወንድሜ፡ ማለቴ ያልቅላቸዋል።

48 ከዚያም ሰጋዊ ማስመሰሎች አሉ። ኦህ፡ ማይ! ያሳዝናል። ይኸውላችሁ፡ እንዲህ ላድርግ... ስንት ጴንጤቆስጤዎች አላችሁ እዚህ? እጃችሁን ከፍ አድርጉ። በጣም ጥሩ። ይኸውላችሁ፡ እናንተ ጴንጤቆስጤዎች፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት እግዚአብሔር በእውነት በእናንተ ላይ ወረደ በልሳኖችም መናገር ጀመራችሁ። ትክክል ነው። ግን ዲያቢሎስ ምን አደረገ? ዞሮ ዞሮ ያንን ሥጋዊ አስመስሎ አመጣ። ትክክል ያልሆነ ነገር ሠራ፡ ሰዎቹን ተጠቅሞ በልሳኖች ተናገረ፡ እና በልሳኖች እንዲናገሩ እና እንዲናገሩ ለማድረግ፡ አንዳንድ ቃላትን እና ነገሮችን እንዲናገሩ አደረጋቸው፡ አንድ ሰው ከሌላ ሰው ሚስት ጋር ይኖራል፡ ሁሉንም ዓይነት ነገሮች፡ እና ሁሉም ዓይነት፡ አንዳንዶቹ ይጠጣሉ፡ ያጨሳሉ፡ ወዘተረፈ፡ በዚህ ሁሉ ግን ልሳን ይናገራሉ። ያንን ያደረገው ለምንድነው? እውነተኛውን መለከት ለህዝቡ የማይታወቅ ድምጽ እንዲሰጥ ለማድረግ ነው። ከዚያ በኋላ ራሱን ለጦርነት ማን ሊያዘጋጅ ይችላል? አያችሁ?

49 ከዚያም ይህ ሲነሳ... እነሆ፡ ከጉባኤው መካከል ሰዎች መነሳሳት ጀመሩ... እኔን ቀድሞ የሄደ... እኔን ቀድሞኝ ወደ ካናዳ የገባ ሰው ነበረ... ታዲያ፡ የጾጥታ ሰዎች ግብረ ሶዶማዊ ሆኖ ስላገኙት ተያዘ። አያችሁ? እርሱም አለ፡ “ምነው፡ ይህን የመለየት ጸጋ የሰጠኝ እግዚአብሔር ነው።” አላቸውም፡ “ሃሌሉያ፡ ይኸውላችሁ... ” “አሁን፡ ጌታ ‘ዮሃንስ... ’ የሚባል ሰው እዚህ እንዳለ ይነግረኛል” አላቸው፡

50 አንድ ቀን ጠዋት እዚህ አንዲት ሴት ነበረች፡ ወደዚህ መጣችና፡ ታስታውሳላችሁ፡ ወደዚያ መጥታ እንዲህ አለች፡ “ጌታ ለእኔም ተመሳሳይ ስጦታ ሰጠኝ።”

እኔም አልኩ፡ “እሺ? ”

“ይህን ለማረጋገጥ እድል ባገኝ እመኛለሁ፡” አለች።

እኔም “ይኸው መድረኩ፡” አልኳት።

51 እና የሆነውን አይታችኋል፡ ንፁህ ሳይኮሎጂ፥ አያችሁ። ስታዩት ግን፡ እህት ሲንደር መጣችና፡ “እርትራይተስ” አለብሽ አለቻት፡ ያ—ያ—ያም ነገሩ ዘጋው። እህት ሲንደር...

52 እኔም እንዲህ አልኩ፡ “በሴቲቱ ላይ ያለው ችግር ይህ አይደለም።” “ወድቃ ዳሌዋ ተሰብራለች፡” አልኳቸው። እንዲህም አልኩ፡ “በመሰረቱ በዚህ አልቆመችም... ” እርግጥ ነው እህት ሲንደር የመሰማት ችግር አለባት፡ እና እንዲህ አለች... እና የነበራት ነገር፡ ሆዷ ውስጥ ያደገ ነገር ወይም ሌላ ችግር ነገር ነው፡ ብዬ አምናለሁ። አልኳቸውም፡ “ችግሯ ያ ነው፥ ከወንድሞች ጋር ቁጭ ብለን ቀኑን ሙሉ ተነጋግረንበታል።” አያችሁ?

53 ይህም ይህ ነገር—ስጋዊ ንጽጽር መሆኑን፡ አያችሁ፡ ለቤተክርስቲያን ለማሳየት ያክል ነው፡ አያችሁ። ያስ ምን ይፈጥራል? የትክክለኛውን መለከት...

54 እና፡ እኔ ካናዳ ላይ ሳለሁ ይህ ወደዚያ የሄደውን ግለሰብ ያዙት። እናም (በብዙ ኖርዌያውያን መካከል)፡ እንዲህ አለ፡ “ጌታ እዚህ አንድ ሰው እንዳለ ነገረኝ... ” ከዚህ ይልቅ አሥር እጥፍ በሚሆን ሕዝብ መካከል፡ “ሰሙ ‘ጆን’ ወይም ‘ጆናስ፡’ ‘ጆእን’ የተባለ ግለሰብ፡ እዚህ እንዳለ ነግሮኛል።” “እዚህ አካባቢ ውስጥ፡ ይመስለኛል፡” አለ። “አይደለም፡” አለ፡ “የሆነ ቦታ ላይ እዚህ አካባቢ ነው፡” አለ፥ እርግጥም ወጣ። በኖርዌይ አገር ላይ? ከመላ ጎደል... ዘጠና በመቶ ስሞቻቸው ፔተርሰን፡ ካርልሰን፡ ጆን፡ ጆናስ፡ እንዴታ፡ ያለጥርጥር ይወጣል። አያችሁ፡ የሆነ ጥግ ላይ መኖሩ... የማይቀር ነው። በመቀጠልም፡ “የወገብ ህመም ያለበት ሰው እንዳለ ጌታ ያሳየኛል፡ ጀርባዬ ላይ ህመም ይሰማኛልና።” መጽሐፍ ቅዱስ እየተማረ ያደገ ሰው ሁሉ ይህ ሳይኮሎጂ እንደሆነ በትክክል ያውቃል። በትክክል... እንደዛ፡ ነው።

55 ነገር ግን፡ አያችሁ፡ ምን ሆነ? (ከዚያም ሰውዬው እዚያው በ—ኤፍቢአይ ተያዘ፡ ከዚህ በተላኩ ሰዎች ምክንያት፡ ሮያል ማውንትድ ፖሊሶች ያዙት።) እና የአገልጋዮች ማሕበር ወደ እኔ መጥተው፡ እና፡ “ግብረሶዶማዊ፡” እንዲህ አሉ፡ “ያው፡ ወንድም ብራንሃምም ያው ሊሆን ይችላል። አገልግሎቱ እንደዚያ ነውና አሉ፡ አያችሁ።” ምን እያደረገ ነው? መለከቱ የማይታወቅ ድምጽ እንዲያወጣ ለማድረግ ይጥራል። አያችሁ? በትክክል። ሁሌም እንደዚህ ነው፡ የማይታወቅ

ድምጽ ለመስጠት እንደዚህ አይነት ነገሮችን ለማድረግ ይሞክራል፡ ይህን የሚያደርግ የሰይጣን ሴራ ነው።

56 አሁን ግን፡ ከዚህ ቃል፡ ፈጽማችሁ አትራቁ። አስታውሱ፡ በእግዚአብሔር ፊት እመክራችኋለሁና፥ **በቃሉ ላይ ጽኑ**! በምንም መንገድ ከሱ ፈቀቅ አትበሉ። እና እነዚህ ነገሮች በሰዎች እና በመሳሰሉት ነገሮች መካከል ሲነሱ፡ እውነተኛ ባለበት በዚያ ሐሰተኛው ደግሞ አለ። የውሸት ዶላር አለ—ማለት፡ ውሸተኛው የተሰራበት ትክክለኛው ዶላር መኖሩ ማሳያ ነው። አንዳንድ ግብዞች በልሳኖች ሲናገሩ ስትሰሙ፡ መንፈስ ቅዱስን ተሞላ ማለት አትችሉም። ነገር ግን፡ አስታውሱ፡ በልሳን የመናገር ስጦታ ያለውን አንዳንድ እውነተኛ ነገርን እያስመሰለ ነው። እነዚያን ሐሰተኛ ነገሮች ስታዩ፡ አስታውሱ፡ የተሠሩት ከእውነተኛው ነው። የመልካም ነገር ሁሉ ፈጣሪ አምላክ ነው፡ ሰይጣን ግን እነዚህን ስጦታዎች ያስመስላቸዋል። እንደው፡ ወደ ሌላ ነገር ገባሁ፡ ወደ ትምህርታችን አንገባም፡ አይደል እንዴ?

57 [ወንድም ቤን ብራያንት እንዲህ አለ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ አንድ ደቂቃ ብቻ ይቅርታ አድርግልኝ? ”—አርታዒ።]

እሺ፡ ወንድሜ።

[“አባክህ? ባለፈው እሁድ እዚህ አልነበርኩም፡ እና ከጥቂት ወራት በፊት ስለተናገርከው ነገር ደርሶኛል፡ እና ነገሩ በመጠኑም ቢሆን፡ በጣም ረበሸኝ፡ መጥቼም አንተን እና ለወንድም ኔቪል ልነግራችሁ ተሰማኝ። ነገር ግን ሚስቴን እራስህ ታውቃታለህ ብዬ ስላሰብኩ በጸሎት እንዲያልፍ አደረግኩት። እናም ዛሬ ጠዋት ወደ ተበርናክሉ በመጣሁ ጊዜ፡ የሆነውን አላወቅሁም ነበር፡ እና ከውድ ወንድሞች መካከል አንድ ወደ እኔ ቀርቦ ይቅርታ እንዳደርግለት ጠየቀኝ። ያም የክርስቶስ-መንፈስ እንዲህ እንዲመስል አስባለሁ።”]

አሜን።

[“እና ሊደነቅ የሚገባው ወንድም ይመስለኛል።”]

አዎን፡ ጌታዬ።

[“ይቅርታ እንዳደርግለት ጠየቀኝ፡ ምክንያቱም አንድ ነገር ለማድረግ እየሞከረ ነበር… ያን ትምህርት ወደ እኔ ለማምጣት እ—እየሞከረ ነበርና።”]

አዎን።

[“እኔ ግን አልተቀበልኩትም። እናም ዛሬ ጠዋት ይቅርታ አድርግልኝ አለኝ፡ እናም በኢየሱስ ስም ይቅርታ አድርጌለታለሁ።”]

58 አሜን። አመሰግናለሁ፡ ወንድም ቤን ብራያንት። እንግዲህ፡ ዋናው—ነገር ይህ ነው… ወንድም ቤን፡ ይህን መናገርህ ደስ ብሎኛል። አየህ፡ ምክንያቱም እነዚያ ሰዎች በየቦታው እየዞሩ ነገሩን እያቃኑ ቆይቷል። ስለዚህ፡ እውነተኛ ክርስትና ማለት ይህ ነው። ክርስትና በሰራ ላይ ማለት ይህ ነው። ስትሳሳት፡ ወጥቶ መሳሳትህን መታመን። አያችሁ? ቆማችሁ “ተሳስቻለሁ፡ አያችሁ፡ ይቅርታ አድርጉልኝ፡” በሉ።

59 አሁን፡ ነገሩን መሰወር የሚሞክር ሰው፡ የሸፈነው ነገር አለ። አይገባም፡ ጌታዬ፡ አንድ… እንደ ሞስኪኑ ዶክተር… አያችሁ፡ የማይሆን ነገር… እሱ… እሱን ለማሳጣት አይደለም፡ ነገር ግን፡ ብቻ፡ አንድ ነገር ማድረግ ፈለገ፡ እና። “ኦህ፡

ዶክ፡ አይቻልም፡ እግዚአብሔርን ጉቦ መስጠት አትችልም፡” አልኩት። “እዚህ ቦርዱ ላይ በትክክል ማስቀመጥ አለብህ፡” አልኩት። ልክ ነው፡ እንደዚሁ ሊሆን ይገባዋል። እርግጥ ነው፡ ሰውዬው ምንም አይነት ስህተት ለመሥራት ከመሞከር ፍጹም ንጹሕ ነበር። ብቻ አንዲት አነሰ ያለች መሬት ባገኝ መልካም ነው ብሎ እንዲሁ አ—አሰበ። እና በክፋት ሳይሆን፡ በመልካም መንገድ ለማድረግ ፈለገ። ይሁን እንጂ እርሱ የፈለገው... እንዳለውም፡ “እኔ... ” ወዲያ ወዲህ ማለት የሚችልበት መንገድ ያውቃል፡ አንድ ሰው በዚህ ሰው ላይ ተጽዕኖ እንዲያሳድር የሚያደርግ አንድ ነገር እንዲያደርግ ሰው ይይዛል። እንደዚያ አታድርጉ። ፊት ለፊት ቅረቡ። አያችሁ? እንደ ቃሉ ሁኑ፡ ያን ጊዜ ታሸንፋላችሁ። እንደ ቃሉ ሁኑ! እግዚአብሔርም ባረከው ትልቅ ነገርንም አደረገለት። አዎን፡ ጌታዬ።

60 እሺ፡ አሁን ለጸሎት አንገታችንን ዝቅ እናድርግ። ስንቶች በጸሎት መታሰብ ትፈልጋላችሁ? እዚህ በተሽከርካሪ ወንበር ላይ የተቀመጠች ሴት በእርግጠኝነት መታወስ እንደምትፈልግ አውቃለሁ፡ አምናለሁም። ይህች እህት፡ ሁላችሁም፡ እዚያ ላይ እዩ። አሁን፡ ነገር ሁሉ አሰወግደን ወደ አምልኮ እንግባ። ለሚቀጥለው ሠላሳ-አምስት፡ አርባ ደቂቃዎች፡ እዚህ ያለነው ለዚያ ነው፡ ለአምልኮ።

61 አሁን፡ ጌታ ሆይ፡ በፊትህ ራሳችንን ጸጥ ሰናደርግ፡ ታላቁ ኢያሱ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ የዚህ ቀን መለኮታዊ መሪያችን እንደሆነ ይሰማናል... ኢያሱም በሙሴ ፊት ሕዝቡን ጸጥ አሰኘ “ምድሪቱን ለመውረስ እንችላለን፡” አላቸው። ምክንያቱም እነዚያን፡ አማሌቃውያንንና አሞራውያንን ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን መለኮታዊ ቃል ኪዳን ይመለከት ነበርና።

62 እናም በዚህ የግርግር ቀን እና ዓለም ባለበት በዚህ ሁኔታ፡ እና በዚህች ውብ የሰንበት ማለዳ፡ እና በዚህ ሁሉ ማስመሰል መካከል፡ እና ሥጋዊ ንጽጽር መካከል፡ በክፋት እና በሳቱ መናፍስት ባሉበት በዚህ ጊዜ፡ እራሳችንን በፊትህ ጸጥ እያደረግን፣ ወደ እግዚአብሔር ቃል እየተመለከትን ከአሸናፊዎች በላይ ነን እንላለን! እግዚአብሔር ጠባሳ ወይም የፊት መጨማደድ የሌለባት ቤተክርስቲያን እንደሚኖረው ተናግሯል፡ እና ያቺ ቤተክርሰትያን አንድ ቀን እንደምናያት እናውቃለን። እኛም ዛሬ በምድር ላይ ያለን፡ የዚህ ታላቅ ዳግም-የተወለደ የእግዚአብሔር ጉባኤ አባላት መሆናችንን በማመን እንደ አባልነት እየታገልን ዛሬ በምድር ፊት ባለች ቤተ ክርቲያን፡ በጌታ በኢየሱስ ስም ወደ እግዚአብሔር እንቀርባለን።

63 እናም በትህትና ስንመጣ፡ የአለምን ነገሮች በሙሉ ከአእምሮአችን እና ከልባችን እንድትጥል እንለምናለን፡ ከሕይወት ድካምና ጭንቀቶች ሁሉ፡ አንተም፡ አምላክ ሆይ፡ በአምልኮ ውስጥ አስገባን፡ ይህም ቃልህን በመስማት እንድናመልክህ ነው።

64 አሁን፡ ዛሬ ጠዋት በትምህርታችን፡ መጽሐፉን ሊወስድ የሚችል ሰው ስለሌለ፡ እንደ ዮሐንስ፡ በልባችን ዛሬ ጠዋት እናለቅሳለን፡ ጌታ ሆይ፡ ይህን መጽሐፍ ሊከፍት የሚገባው ማንም የለምና። ነገር ግን የዮሐንስ ልቅሶ ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነበር፡ ብዙም ሳይቆይ ተጽናና በጉም መጥቶ መጽሐፉን ወሰደ፥ የእግዚአብሔር በግ ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ና መፅሐፉን ወሰደህ ክፈትልን፡ ጌታ

ሆይ። አንተን እንጠብቃለን። በዚህ በጉድለታችን ስንጠብቅህ... በቃልህ እና በመገኘትህ አብቃን።

65 የእግዚአብሔር በግ ሆይ፡ ብዙ እጆች ወደ አንተ ተነስተዋል። አንተ ልብን ሁሉ እንደምታውቅ እናውቃለን፥ አሳባቸውን አውቀሃልና። አንተ እንደ ድሮህ እንዲሁ አምላክ ነህና። ወደፊትም እንዲሁ ያው ነህ፡ ምክንያቱ አንተ ፍጹም እና ፍጻሜ የሌለው የማትለዋወጥ ነህና። ስለዚህ ዛሬ ማለዳ የሰው ሁሉ ጥያቄ በመመለስ፡ ብቁዎች እንድታደርገን እንጸልያለን። ጌታ ሆይ፡ ሕንፃውን ለቀው ሲወጡ ሁሉም እንዲረኩ፡ አድርጋቸው፡ ይህም በእግዚአብሔር ፊት እንደነበሩ እና የልባቸውን መሻት አግኝተው እንዲመለሱ ነው። ጌታ ሆይ፡ እኔንም፡ በዚያ ቁጥር ማካተት እንዳትረሳ። በኢየሱስ ስም እጠይቃለሁና። ኣሜን።

66 አሁን፡ በጉ ማኅተሞቹን እንዲከፍት ወይም መጽሐፉን እንዲከፍትልን እየጠበቅን፡ ወደ ጸጋው መጽሐፋችን እንሸጋገር። **የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ** መጽሐፍ ላይ ነንና፡ 5ኛው ምዕራፍ እንክፈት።

67 አሁን፡ እናንተ ይህን በመግነጢሳዊ ቴፕ ለምትሰሙት በተለያዩ የአለም ክፍሎች ላላችሁ ወዳጆቼ፡ እዚህ ላይ ይህን ለማሳካት አስተምህሮቶችን መግለጽ እና የመሳሰሉትን ልናገር እችላለሁ። አስተምህሮ የሌለው ሰው ደግሞ አገልግሎት የለውም። ስለዚህ ጉባኤያችሁ ቴፑን መስማት የለበትም ብላችሁ ካሰባችሁ፡ እንግዲያውስ ከልክሉ። እኔ ግን የራሴን አስተያየት እና የራሴን ስሜት፡ የራሴን የእግዚአብሔር ቃል መገለጥ እተርከዋለሁ።

68 አሁን፡ ከጥቂት ወራት በፊት ወደ ኋላ መለስ በማለት ዳራ ሰርተናል... ማለቴ፡ ከጥቂት ቀናት በፊት፡ 4ኛውን ምዕራፍ፡ 3ኛውን ምዕራፍ የ 4ኛው ዳራ አድርገነዋል። አሁንም፡ ባለፈው እሑድ፡ 4ኛውን ምዕራፍ የ 5ኛው ዳራ አድርገናል። እና አሁን፡ ዛሬ፡ 5ኛውን ዳራ ማድረግ እና ለሚመጣው 6ኛው መሰረት መጣል እንፈልጋለን።

69 እና ዛሬ ዓላማዬ ቅዱሳት መጻሕፍትን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ነው፡ ምክንያቱም ምናልባት ወደፊት፡ መቼ እንደሚሆን አላውቅም፡ ጌታ ከሰጠን ግን፡ አንድ ቀን በተበርናክሉ ውስጥ **በሰባት ማኅተሞች** ላይ የሰባት-ቀን ሰብሰባ እናደርጋለን። ሰባት የቤተክርስቲያን ዘመናት አይተናል፡ አሁንም ስለ ሰባቱ ምስጢራዊ የእግዚአብሔር ማኅተሞች ሰባት ምሽቶችን እንወስዳለን፡ ሰባት ማኅተሞች እስኪያልቁ ድረስ በእያንዳንዱ ሌሊት አንድ ማኅተም እናያለን። አሁን፡ ጌታ መቼ ያንን እንደሚያመቻችልን አላውቅም፡ ካመቻቸልን፡ ግን፡ እኔ ዛሬ ጠዋት ዳራውን አስቀምጣለሁ።

70 እናም በዚህ ስክሪፕት የመጨረሻ ጥቅሶች ላይ-... ወይም በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መጨረሻ፡ **የዳንኤልን ሰባ ሳምንታት** እናስገባለን። እና ያለፉት ሶስት ሳምንታት፡ ህዝቡን ወደ መ-... መጨረሻዎቹ ማሕተሞች ወደሚያደርሰው የጴንጤቆስጤ ኢዮቤልዩ ዘንድ የተሳሰሩ ነበሩ፡ ስለዚህ በጉ ማሕተሞች ሲከፍታቸው ተመቻችታችሁ ተቀመጡ።

71 እና፡ ያስታውሱ፡ ማኅተሞቹ ሚስጥራዊ ናቸው። መጽሐፉ የታተመ ሲሆን በጀርባው ላይ፡ በመጽሐፉ ውስጥ ያልተገለጹ ሰባት ማኅተሞች ነበሩት። እነዚህ ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፉ አይደሉም። ነገር ግን፡ ማንም ሰው ትርጓሜውን መስጠት ቢወድ፡ ከተቀረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ጋር

በማነጻጸር ይሁን። እና፡ አቤት፡ እንደምትባረኩበት እርግጠኛ ነኝ፡ ወይም እንደምትባረኩበት እሰባለሁ። እንዲሁ እንደሚሆን እምነቴ ነው።

72 የዛሬ ማለዳ ብርሃን ውስጥ ከመምጣቴ በፊት ኮቴን መልበስ እስኪሳነኝ ድረስ ሆኜ ነበር፡ ምክንያቱ ነገሩ... እዚያ ተቀምጬ፡ እያነበብኩ ነበር፡ እና መንፈስ ቅዱስ በቸርነቱ ደጋግሞ እያጥለቀለቀኝ ነበር። እና... ያን ሳየው፡ እንዲህ አሰብኩ፡ "አቤቱ፡ እዚህ በሰጠኸኝ መንገድ ወደ እነርሱም እንዲሁ መናገር ብችል፡ ሁላችንም ድንቅ ጊዜ ይኖረን ነበር።" ግን፡ በሆነ መንገድ፡ በሰዎች ፊት ስትቀርቡ፡ በጸሎት ለብቻችሁ ሆናችሁ፡ ወይም ሌላ ነገር እንደምታደርጉ አይሰማችሁም።

73 አሁን፡ ግን፡ በመጀመሪያዎቹ ጥቅሶች ለመጀመር፡ ይህን አይተናል... እንግዲህ፡ ባለፈው እሁድ ካቆምንበት ዳራ ለማድረግ ያህል፡ እዚህ ላይ ጳውሎስ፡ በኤፌሶን 1፡13 እስከ 14 ድረስ፡ እንደነገረን... የመዳናችን ቀብድ፡ የቤዛችን ቀብድ እንደተቀበልን ነግሮናል። የቤዛችን ቀብድ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ነው። ይሄም... የሚቀጥሉት ጥቂት ሳምንታት ትምህርት ሁሉም በቤዛነት ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡ እያችሁ፡ ጽድቅ ላይ ሳይሆን፡ ቤዛነት ላይ። አይ... በቤዛነት ላይ የተመሰረተ ነው፡ እንጂ—በአማላጅነት የመካከለኛው አገልግሎት የተመሰረተ አይደለም፡ **በቤዛነት** እንጂ። ኦህ፡ የጠፋ ወይም በሌላ ተወስዶ የነበረውን ርስት እንደገና ለእኛ የተቤዠልን፡ እና ይህ ሁሉ እንዴት እንደ ሆነ እና እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር እንዴት እንዳቀደው፡ እና ቤተ ክርስቲያን ምን ያህል እርግጠኛ እንደሆነች ነው።

74 እንዴት እንደምንቆም የምናውቅበት ጊዜ ላይ የደረሰ ይመስለኛል። በምታደርጉት ነገር ላይ እምነት እስካላደረባችሁ በቀር ማንኛውንም ነገር እንዴት ማድረግ ትችላላችሁ? እምነት ሊኖራችሁ ይገባል። እኔም እዚህ ካለው ቤተ ክርስቲያን ጋር ይህንን የማደርግበት አላማው ይህ ነው፡ አማኞች በሚያደርጉት ነገር ሁሉ ላይ እምነት እና ድፍረት እንዲኖራቸው መስጠት ነው፡ ምክንያቱም የጌታ ቃል ነው። ከዚያም በቅዱሳት መጻሕፍት ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ድረስ በሉአላዊነት እስከ ተቀመጠ ድረስ፡ ወደ ኋላም ወደ ፊትም፡ ወደ ላይም ወደ ታችም፡ ዲያብሎስ መፈናፈኛ መንገድ አያገኝም፡ ያን ጊዜ ፍጹም ድፍረት ይኖራችኋል፡ እያችሁ፡ ምን ላይ እንደቆማችሁም ያን ጊዜ ታውቃላችሁ።

75 እዚህ በዊልቸር ላይ ባለችው እህታችን፡ ወይም ምናልባት በሌሎች በታመሙ እና በተጎዱ ሰዎች ላይም ተመሳሳይ ነው። "እናንተን መፈወስ የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ መሆኑን" በትክክል ብታውቁ ኖሮ፡ እናንተን ሊያሳምም የሚችል ዲያብሎስ በአገሪቱ ውስጥ ባልተገኘ ነበር። እያችሁ? ልክ ነው፡ እናንተን መፈወስ የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ እንደሆነ፡ እንዳደረገላችሁም ስትረዱት፡ ያን ጊዜ አንድን ነገር ለማድረግ እንዴት መሄድ እንዳለባልችሁ ታውቃላችሁ።

76 እንደዚህ ነው። በሙሉ ልቤ ልንገራችሁ... ተርባችሁ በረሃብ ለመሞት ብትቃረቡ፡ እና እንደ እውነተኛ ሰው በእኔ ላይ ፍጹም እምነት ቢኖራችሁ፡ እኔም አንድ ሺ ዶላር የተቀመጠበት ሰፍራ፡ እንዴት እንደምትደርሱበት፡ በየትኛው መንገድ መሄድ እንዳለባችሁ፡ የት መሄድ እንዳለባችሁ ብነግራችሁ፡ እናንተም ገንዘቡ የተቀመጠበት ሰፍራ በትክክል ብትረዱት እንደ ማለት ነው። እያችሁ?

ያን ጊዜ እኔን ብታምኑኝ፡ ገንዘባችሁ በእጃችሁ ውስጥ እንዳስገባችሁት ሆናችሁ፡ መደሰት ትጀምራላችሁ።

77 ስለዚህ፡ እያችሁ፡ ከማግኘታችሁ በፊት... የተለየ ስሜት ወይም ሌላ ነገር ሳይሰማችሁ በፊት፡ ማግኘታችሁ በትክክል እርግጠኞች ስለምትሆኑ "አገኘሁት" እያላችሁ፡ ስለመፈወስሳችሁ መደሰት ትችላላችሁ፡ ምክንያቱ ተስፋ በሰጣችሁ አካል ላይ ድፍረት አላችሁ። እያችሁ? እያችሁ? የተቀመጠበትን ትክክለኛውን ስፍራ ስለነገራችሁ፡ እና እርሱ ስለማይዋሽ ይህ ድ—ድፍረታችሁ ነው፡ ከዚያ በኋላ አስቀድማችሁ ያንን ስላገኛችሁ፡ ለመሄድም ድ—ድፍረት ይኖራችኋል፡ ምክንያቱም ይህ እምነታችሁ እርሱም የቤዛችሁ ቀብድ ነው።

78 በሌላ አነጋገር፡ ከበሽታ ለመቤዠት ትሞክራላችሁ፡ እምነታችሁም የነገሩ በረከት ጭብጣችሁ ነው... ወይም፡ ይልቁንም፡ የፈውሳችሁ ቀብድ ነው። አንድ ነገር በልባችሁ ውስጥሽ "የምፈውስ**ሽ** ጌታ እኔ ነኝ፡" ብሎ ከተናገረሽ፡ የሚያስፈልግሽ ነገር፡ በበቂ ሁኔታ ይህ ብቻ ነው። ያ ነው... ኦህ፡ ምንም ይሁን ምን፡ ደስተኛ መሆን ትችላላችሁ። ካልተፈወሳችሁ፡ ከባሰባችሁም፡ ፍጹም ደህና ስትሆኑ ባላችሁ ዓይነት ደስታ፡ እንዲሁ ደስተኞች ትሆናላችሁ፡ ምክንያቱ ነገሩ መፈጸሙን የሚያረጋግጥ ማረጋገጫ አላችሁ። ይህን ሰንቶች ተረድታችኋል አሁን፡ እጆቻችሁን እንያቸው። ይኸው። "የማይታዩ ነገሮች ማረጋገጫ ነውና።"

79 እንግዲህ፡ በዚህ የምዕራፉ የመጀመሪያ ክፍል ላይ እንዳየነው፡ መጀመሪያ ላይ-... 5ኛው ምዕራፍ የክራባት የመጨረሻዋ ቁልፍ ነው፡ የቤተ ክርስቲያን ዘመን የመጨረሻውን ክፍል፡ ምዕራፍ 3ን የሚያገናኝ የአልማዝ መ—መ—መስኪያ ነው። 4ኛው ምዕራፍ ዮሐንስ ወደ መንግሥተ ሰማያት የተወሰደውን ይናገራል። 5ኛው ምዕራፍ ለእነዚህ እየተዘጋጀ ነው... በሰባተኛው የቤተክርስቲያን ዘመን ውስጥ ያያችሁት፡ ከዚያም ዮሐንስ በ4ኛው ምዕራፍ ወደ ላይ ተወሰደ። 5ኛው ምዕራፍም፡ ለሰባት ማኅተሞች መክፈቻ የተዘጋጀ ትዕይንት ነው። በራዕይ 1ኛ ምዕራፍ ላይ እንዳደረገው፡ ለሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመናት መንገድ ከፈተ (በዚያ በሰባቱ የወርቅ መቅረዞች ውስጥ ቆመ፡ እናም እንደ ኢያስጲድ እና እንደ ሰርዲዮስ ድንጋይ ይመስል ነበር)፡ እና ለእነዚያ ሰባት የቤተክርስቲያን ዘመናት እያዘጋጀ ነበር።

80 አሁን ለእነዚያ ሰባት የቤዛ ማኅተሞች ለመክፈት የሚያዘጋጅ ነው። እያችሁ፡ 5ኛው ምዕራፍ ያ ነው። ያንን አንብቤ ከዚያም በመነሣት የወሰድኩበት ምክንያት፡ በሱ ላይም የተናገርኩት እንዲሁም የቅዱስ ቃል ሌላኛው ክፍሎች የሰጠሁበት ምክንያት ያ ነው፥ ምክንያቱ ጥቅስ በጥቅስ ላይ ነውና፡ እየሆነ የሚቀጥል ነገር፡ የሆነ ነገር እንዲፈጸም የሚያዘጋጅ ነገር ነውና። ስለዚህ አሁን ዝግጅት ካደረጋችሁ፡ ከዚያ በኋላ... ለዚያ የተዘጋጃችሁ ትሆናላችሁ። ስለዚህ በእምነት ይሁን ወይም በሌላ ነገር እንደዚያ ነው። አሁን፡ ስለ፡ ማህተሞቹ...

81 አንዳንድ ቅዱሳት መጻህፍት እና አስተያየቶች ጽፌ ይዣለሁ። አሁን፡ በኤፌሶን 1፡13-14፣ እ... ማስታወሻ መያዝ ከፈለጋችሁ፡ ማለት፡ "አሁን ቀብድ አለን። መንፈስ ቅዱስም የርስታችን ቀብድ ነው።" በሌላ አገላለጽ፡ ማረጋገጫ ነው፡ **ቀብድ** ማለት "ዋስትና፡" "ቅድመ ክፍያ" ነው፡ በክርስቶስ ዘንድ

ተቀባይነትን ማግኘታችን ያሳያል። ይህም የዘለአለም ህይወት እንዳለን እና እርሱ የዋጀልንን ነገሮች ሁሉ ወራሾች መሆናችንን የሚያሳይ የተባረከ ተስፋ እና ማረጋገጫችን ነው። ኦህ፡ ማይ! አይታያችሁምን?

82 ኦህ፡ በመንፈስ ቅዱስ ስንታተም (ደጋግሜ የምጠቅሰው እንዳትረሱት ስለፈለግኩ ነው)፡ ክርስቶስ የሞተለት ሁሉ የእኛ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የእግዚአብሔር ማኅተም ነው። እግዚአብሔር ራሱ እንዲህ በማለት እየተናገረ ነው፡ "አሁን ተቀብዬሻለሁ፡ ጊዜው እስኪደርስ ድረስ እንድትጠብቂኝ እነሆ ይህ ማኅተም ሰጥቼሻለሁ፡" አሁን ቤዛችን በከፊል ስለሆነ፡ ወደ ሙሉ ቤዛነታችንን እስክንደርስ ድረስ ነው።

83 ባለፈው እሁድ ይመስለኛል፡ እንዳልኩት፡ **እዚህ** ታች የተሰመረው መስመር ኃጢአተኞች የሚርመሰመሱበት፥ ጭቃ፡ ቆሻሻ፡ እድፍ፡ እና እድፈት ነው። አሁን፡ ምናልባት... በየአራት ሰዓቱ ሻወር የሚወስዱ... እጅግ ንጹሐን ሊሆኑም ይችላሉ፡ በጣም ጥሩ የተባለውን ልብስ ይለብሱ ይሆናል፡ የተማሩ የተመራመሩ ምሁራን ሊሆኑም ይችላሉ፥ በነፍሳቸው ውስጥ ግን፡ በሲኦል ውስጥ እንዳሉ ግድግዳዎች ቆሻሻ እና እድፋሞች ናቸው። አያችሁ?

84 ስለዚህ፡ የክርስቲያን አካሄድ ግን ከዚያ ከፍ ያለ ነው፡ ምክንያቱም **እዚህ** ጋር የርስታችን መያዣ የሆነውን ቀብድ ተቀብሏልና። ወደ ላይ ከፍ እንዲል ተደርጓል፡ ከዚያ እድፍ እና እድፈት ወደ ላይ ወጥቷል፡ **ወደዚህ** ወደ ላይ፡ ስለዚህ አካሄዱ ከፍ ያለ ነው። ኦህ፡ ደስ ይላል! ፖል ራደር ያንን ጊዜ ግንድ አጠገብ ላይ እንደተናገረው፡ ታውቃላችሁ፡ እንዲህ አለ፡ "በላዩ ላይ እሄዳለሁ! እኔስ በላይ እሄዳለሁ!" አሁን ያለውም በዚያ ነው፡-

> የሱስ የኔ ነው፡ መልካም ተስፋ!
> ኦህ፡ መለኮታዊው (ከምንጩ ላይ እንድጠጣ ተፈቅዶልኛል።) ክብሩ ይሰፋ!
> የህይወት ወራሽ ልንሆን ጠራን፡ በእግዚአብሔር ተገዝተናልና፡
> ከመንፈስ ወልዶ በደሙ አጥቦን።
>
> ይህ ነው ታሪኬ፡ ልዘምረው፡
> በዝማሬ—በዝማሬ መድኃኒቴንም ላመስግነው።

85 አያችሁ፡ ከጥላዎች በላይ፡ ከእድፈት፡ በቅምሻ ከፍ ከፍ ተደርገናል! የርስታችን የሙላቱ ቀብድ ተቀብለናል፡ እግዚአብሔር የምድርን ሥር ከዓለም ነገር ነቅሎ በከፍታ ቦታ ላይ ስለተከለን ነው፥ ከፍ ከፍ አደረገኝ፡ ለውጦ-ኛል፡ ከዓለም ነገሮች ለወጠኝ፥ ሥሩን፡ ቅርንጫፎችን፡ ሁሉን፡ ነቃቅሎ ከፍ ከፍ አደረገኝ፡ ከረግረግ ከጭቃው፡ ካረጀው የኃጢአት ጭቃ አወጣኝ፥ በተወደደው የአትክክልት ሰፍራው፡ በእግዚአብሔር ቅዱሳን አስቀመጠኝ፡ በጽዮን ተራራ ተከለኝ። ስለዚህ አሁን የዚያ መንግስት ዜጎች ነን፡ በክርስቶስ ኢየሱስ ያላችሁ ወንድሞችና እህቶች ሆይ፡ ርኩሰትና አመጽ ሁሉ ከአእምሮአችን ተወግዷል። ውኃችን... ሰውነታችን በንፁህ ውሃ ታጥቦ ልባችን በጌታ በኢየሱስ ደም ተረጭቷል። መንፈስ ቅዱስም ከትንፋሹ ጋር አንድ በመሆን ቀኑን ሙሉ በቅርንጫፎቻችን ሲነፍስ ይኖራል፡ ይህም እየገፋን እና እየገፈተረን ጥሩ ሰር

እንድንሰድ እና ወደ ጥልቅ እንድናድግ ያደርገናል። ደስ አይልምን? “የመዳናችን ቀብድ ነው።”

86 ይህ ምዕራፍ፡ የጠፋው ርስታችንን ይገልጣል። የጠፋው ርስታችን በተወደደውና፡ ቸር በሆነው ዋርሳችን ተመለሰልን። እግዚአብሔር ወርዶ እንዴት ይህ ሆነ... ሰው ለመሆን፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ የነበረውን መልክ ቀይሮ ሰው ሆነ፡ ሰው የሆነ ዋርሳ ለመሆን፡ ተፈጥሮአዊው ዓለም ለተፈጥሮአዊው ህዝብ ይመልስ ዘንድ ነው። አሜን! እግዚአብሔር (መለኮታዊ የሆነው) ዋርሳ ለመሆን ተፈጥሯዊ ሆነ፡ የገዛ ህጎቹ አይጥሰምና። እንዲሁ ሆኖ መምጣት ነበረበት-... የዋርሳ ቤዛነት አካሄዱ ነውና... ዕቅዱ ያ ነው። አደራረጉም ያ ነው።

87 እግዚአብሔር ሰው እንደሚወድቅ እያወቀ፡ ሰው እንዲወድቅ ግን አላደረገም። እግዚአብሔር ሰው እንደሚጠፋ ቢያውቅም፡ ማንም እንዲጠፋ አይፈልግም። ነገር ግን የእግዚአብሔር የባሕርይ መገለጫዎች ለሰው ሁሉ ይገለጡ ዘንድ፡ ማለት እርሱ ቤዛ ይሆን ዘንድ፡ አዳኝ ይሆን ዘንድ፡ ሰው መውደቅ ነበረበት። መውደቅ በእርሱ ውስጥ ነበር፡ ከዚያም እርሱን እንደገና እንዲቤዠው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር። ያ ነው-... በቀኑ ለመደሰት፡ ማታ መኖር ነበረበት። በጤና ለመደሰት፡ ህመም መኖር ነበረበት። ሁሉም ነገር፡ አንበሰ እና ጎፈር አለው። አሁንም፡ የዋርሣ ቤዛችን...

88 አሁን፡ እዚህ እንድታስተውሉ እፈልጋለሁ። እዚህ 5ኛውን ምዕራፍ እየተመለከትኩ ነው፡ እሱ ሲያየው፡ “አትፍራ!” በ5ኛው ቁጥር ላይ፡ “አትፍራ!” አያችሁ፡ ሁሌም ቢሆን... ስለ ምንም ነገር መፍራት አያስፈልጋችሁም።

> ... **ከሽማግሌዎቹ አንዱ እንዲህ** አለኝ፡ **አታልቅስ፡ እነሆ፥ ከይሁዳ ነገድ የሆነ አንበሳ፡ እርሱም የዳዊት ሥር፡ መጽሐፉን ይዘረጋ ዘንድ ሰባቱንም ማኅተሞች ይፈታ ዘንድ ድል ነሰቷል።**

> ... **እና፡ እ፡** እነሆም፡ **በ... እ፡ በዙፋኑ መካከል እና... አራቱ እንሰሶች፡... በሽማግሌዎችም መካከል፡ አንድ በግ ቆሞ ነበር...**

89 “በግ።” በጉን አስቀድሞ ለምን አላየውም? በጉ በአብ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ነበር፡ በሚጋርዱት—ውስጥ። ዮሐንስ ወደዚያ ማየት አልቻለም፡ እነዚያን ባለ አራት-ራሶች... ወይም የቆሙት አራቱ እንሰሶች ብቻ አየ፡ ወይም ቅዱሱን ሰፍራ የሚጋርዱ አራቱ ኪሩቤል ቆመው አየ። እናም ባለፈው እሁድ፡ እና በሌሎቹ ትምህርቶች ውስጥ አይተነዋል፡ ከእነርሱ አልፎ ሌላ ነገር ማየት አልቻለም ነበር። በዚያም፡ በድንገት፡ ታየ... በምስጢራዊ፡ ቅጽበታዊ፡ አንዱ መጣ፡ በግ ነበር።

90 አሁን፡ የተፈጥሮ እንሰሳ፡ በግ አለመሆኑን ለማሳየት፡ በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠው ከቀኝ እጁ መጽሐፉን ወሰዶአልና፥ በግ ይህን ማድረግ አይችልምና፡ አያችሁ። እሱ—እሱ—እሱ በጉ ነበር፡ ክርስቶስ ነበር። በሌላ አባባል፡ በባህሪያቱ እንደ በግ የዋህ እና ትሁት ነበር።

91 አሁን፡ አስተውሉ፡ የበግ ቤዛ፡ ልክ እንደ መጀመሪያው የበግ ቤዛ ነበር። እግዚአብሔር ፈጽሞ አይለወጥም! አሜን! በኤደን ገነት፡ የመጀመሪያው ቤዛ በግ ነበር፡ እግዚአብሔር ያቀረበው በግን ነው። አሁንም እንደገና፡ ወደዚህ ወደ ራእይ ተሻግሮ፡ እንደገና በግ ሆኖ እናየዋለን። ምን ለመቤዠት? የወደቀው

ሁኔታቸው እና የወደቀው የሰዎች ዘር ርስት። ያኔ በመጀመሪያ በእኛ ዘንድ እንደነበረው፡ ይቤዥ ዘንድ በግ መጣ፡ እኛን ይቤዥ ዘንድ ነው።

92 ምን ለቤዡት? የሚቤዡልን ነገርስ ምን ይሆን? ሊቆርስልን... ሊያመጣልን... የሚቤዡ ነገር ሰንል ጠፍቶ የነበረ ማንኛውም አይነት ነገር ነው። የጠፋው እና ከዚያ እንደገና የተመለሰ ነገር ነው። ይህ በግ፡ ወደ እኛ ምን አመጣ? መጀመሪያ ላይ የነበረን ሁሉ።

93 መጀመሪያ ላይ ምን ነበረን? የዘላለም ሕይወት። የዓለም ወራሾች ነበርን። ሕይወት ነበረን፡ መሞትም የሌብንም ነበር። በጭራሽ መታመም አልነበረብንም። መቼም ቢሆን ማርጀት አልነበረብንም። በጭራሽ ምንም ጭንቀት ሊኖርብን አይገባም ነበር። የቀብር ሥነ ሥርዓት የሌለበት፣ መቃብር የሌለበት፣ ክፋት የሌለበት፣ ሞት የሌለበት፣ ሽበት የሌለበት፣ ትከሻ መጉበጥ የሌለበት፣ ኀዘን የሌለበት፣ የሚያለቅሰበት የለም ነበር። ዘለአለማዊ ሕይወት፡ ነበረን! በምድር ሁሉ ላይ ስልጣን ነበረን። በምድር ላይ አማልክት ነበርን (ይሄው ነው)፡ በመንገዳችን፡ በትክክል ያልቆመ ዛፍ ሰናይ፡ እንዲህ እንለዋለን፡ “ተነቅለህ ወደዚህ ተቀመጥ፡” እሱም ይታዘዘናል። ነፋሱ ሲነፍስ፡ ነፋሱ እንዲነፍስ ካልፈለግነው፡ “ሰላም ይሁን፡ ጸጥ በል፡” እንለዋለን እርሱም ይላል። እና ምን ሊያደርግ መጣ? ያን ሁሉ እንደገና ወደ እኛ ለመመለስ (ኦህ፣ ኦህ፣ ኦህ፣ ኦህ፣ ኦህ፣ ማይ!)፣ ያንን ሁሉ እንደገና ሊመልሰልን።

94 እና አሁን ተፈጥሮ ራሱ እያቃተተ፡ ምን እየተጠባበቀ ነው? የእግዚአብሔር ልጆች መገለጥ፡ የእግዚአብሔር ልጆች ይገለጡ ዘንድ።

95 አሁንም የመዳናችን ቀብድ ተቀብለናል፡ እና በካንሰር የሚሞተውን ወንድማችንን ይዘን፡ ከዚያች ከትንሿ የቤዛነት ትንፋሽ ጋር አብረን እንቆማለን፡ እናም ጥላ የሆነውን የሰውዬው ህይወት እንደገና ወደ ጤናማ ሰው በሚመልሰ መልኩ በእሱ ላይ የእምነት ጸሎት እንጸልያለን፥ ርስታችን በሙላት ሲመጣስ ምን እናደርግ ይሆን? አሜን!

96 ተፈጥሮ ያውቀዋል። ተፈጥሮ ይቃትታልና እኛም አብረን እንቃትታለን። ተፈጥሮ ከአለቃዋ ጋር ስለተረገመች፡ የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ እየጠበቀች ነው። አለቃዋ (ዋናው) ሲረገም፡ ተፈጥሮ ደግሞ ከአለቃዋ ጋር ወደቀች። ነገር ግን ይህ የዋርሳ ቤዛ መጥቶ (ሃሌ ሉያ!) እና በተፈጥሮ ላይ አለቃ የሆነውን ሰውን መልሶ ተቤዠው። ስለዚህ ተፈጥሮ በሙላት ሰውዬውን፡ አለቃዋን እየጠበቀች ናት።

97 ምን አደረግን? ስንፈልግ መጥረቢያውን ወስደህ በእጃችን ይዘን ዛፉን እንቆርጠዋለን፥ ያን ቀን ላይ ግን እንዲህ አናደርግም። አሜን!

98 ተፈጥሮ አለቃዋን በመጠባበቅ ላይ ናት። አለቃዋም ይህን ምድር የተሰጠቻቸው የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው። አሁን፡ እግዚአብሔር በእርግጥ፡ ሰማያትን ይገዛል፡ ይህ ግን ለሰው ተሰጥቷል። ስለዚህ ይህ የዋርሳ ቤዛ ሲመጣ ወደ ጠፋብን ሊቤዠን ይመጣል። እንዴት የሚያምር ነው! ማይ! ብቻ ሳስበው... “የበግ ቤዛ።”

99 ሰራው ሲጠናቀቅ፡ ሁሉም ነገሮች እንደገና ይኖረናል። ሁሉም ነገሮች ምን ዓይነት ናቸው? ስልጣን ሁሉ ይኖረናል። የዘላለም ሕይወት ይኖረናል። ዘላለማዊ ጤና ይኖረናል። ዘላለማዊ ወጣትነት ይኖረናል። ዘላለማዊ ስልጣን

ይኖረናል። ኦህ፡ ከዘላለማዊው ጋር ዘላለማዊ እንሆናለን! እና፡ እንግዲያውስ፡ ሁላችንም ያን ጊዜ እየጠበቅን ነው፡ እየጠበቅን እና እየቃተትን፡ እየጠበቅን እንገኛለን።

100 እናም ይህ የሰባት መአዝናዊ የመቤዠት ዕቅዶች መጽሐፍ ወደ እኛ ቀርቦልናል፡ ይህ መጽሀፍ በውስጡ የያዘው ነገርም ያ ነው። አሁን፡ ይህ ብርቱ መልአክ ወደሚያውጅበት ወደ 10ኛው ምዕራፍ ላይ እንሻገራለን... እርሱም ዮሐንስ ሊበላው የተገባው ታናሽ መጽሀፍ ይዞ ነበር። እርሱም በበላት ጊዜ፡ ሆዱ ውስጥ ገባችና መራራ ነበረች፡ በከንፈሮቹ ውስጥ ግን ጣፋጭ ነበረች።

101 መፍጨት ስትጀምሩ፡ ያን ጊዜ መራራ ይሆናል፡ ሁሉም ይቃወማችኋል፡ ሁሉም "አንተ ሆሊ ሮለር ነህ፡ አንተ **ይህ፡ ያ፡** ወይም **እንደዚያ** ነህ።" አያችሁ? "አ—አ—አንተ እብድ ነህ።" ስለዚህ እሱን ለመፍጨት አስቸጋሪ ነው፥ ስለ ክብሩ ስትመሰክሩ ግን፡ በከንፈሮቻችሁ ጣፋጭ ነው። ይኼው ነው። አያችሁ? እና በጉባኤ መኃል ተነስታችሁ፡ እንዲህ ካላችሁ፡ "ክብር ለእግዚአብሔር! ሃሌ-... " ኦህ፡ ያን ታላቅ ከበባ ስታልፉት፡ ከባድ ነው፥ ነገር ግን ከዚያ ታላቅ ከበባ ስትወጡ ስለ እሱ ትመሰክራላችሁ፡ ያን ጊዜ በከንፈሮቻችሁ ውስጥ ጣፋጭ ነው። አያችሁ? ትክክል ነው። የቤዛ መጽሐፍ ማለት ይህ ነው።

102 አሁን፡ አሁን፡ እዚህ በ5ኛው ቁጥር ላይ አንድ ተጨማሪ ትንሽ ምሳሌ ልንሰጥ እንፈልጋለን፡ ከዚያም እንደገና እንጀምራለን... 6ኛ ቁጥራችንን እንይዛለን ከዚያም እንጀምራለን። አሁን፡ በቤዛነት እቅድ ውስጥ እግዚአብሔር እንዴት አስቀድሞ እንዳሳየው፡ በሩት እና በቦዔዝ ውስጥ በትክክል እንደሰራው እንድታስተውሉ እፈልጋለሁ። ባ... ባለፈው እሁድ ያቆምነው እዚህ ነበር። አሁን፡ ዛሬም፡ በሩት እና በቦዔዝ ላይ፡ መጀመር እፈልጋለሁ።

103 አሁን፡ በሩት እና በቦዔዝ ውስጥ፡ አራት ጣቢያዎች፡ ወይም አራት መዳረሻዎች አሉ። የመጀመሪያው ሩት **መወሰኗ** ነው። መልእክቱን እኔ ስሰብክ... ሰምታችሁ የምታውቁ አላችሁ? እስኪ እጆቻችሁን አሳዩን። አውቃለሁ... መልካም፡ ሁላችሁ እንደሆናችሁ፡ አሰባለሁ። እዚህ ላይ ተናግሬዋለሁ፡ በቴፕ እና በልዩ ልዩ አገሮች ላይ ይዤዋለሁ። ሩት፡ በመጀመሪያ፡ ከኑኃሚን ጋር ወደዚህ ምድር ልትሄድ፡ ወይም እንደማትሄድ፡ **መወሰን** ነበረባት። ውሳኔ ማድረግ ነበረባት። ከዚያም እዚያ ከደረሰች በኋላ፡ ማድረግ ያለባት በቦዔዝ መስክ **ማገልገል** ነበረባት፥ በዚያም፡ በባዶ እግሯ፡ ከአጫጆች በኋላቸው እየቃረመች፡ ታገለግል ነበር። ከዚያም በቦዔዝ ፊት ሞገስን ካገኘች በኋላ፡ ቦዔዝ የዋርሳ ቤዛ እስኪያደርግ ድረስ **መጠበቅ** ነበረባት፡ ሞዓባዊቷን ሩትን ለማምጣት፡ የጠፋውን የኑኃሚንን ንብረት ሁሉ ይመልስ ዘንድ ነው። ከዚያ በኋላ ቀጣዩ ደረጃ፡ ሩት—**መሸለሟ** ነው።

አሁን፡ ተመልከቱ። ሩት፡ በትክክል፡ **ወሰነች**...

104 ኦህ፡ እነዚያ "መጽሐፍ ቅዱስ በምሪት የተጻፈ አይደልም" ባዮች፡ የሆነ ችግር አለባቸው። እያንዳንዷ ቃል በምሪት ናት፡ እያንዳንዱ የቃሉ ቃል በ—በየቦታው—ልክክ ብሎ እንደተሰካ ነው። ልክ በሚሽከረከር ታላቅ መንኮራኩር ላይ ባልተዛነፈ መንገድ እንደሚሄድ፡ ልክ በሰከንድ ሚልዮኖች ጊዜ እንደሚቆጥር፡ በትክክል ልክ ነው።

105 አሁን፡ በዚህ ጊዜ፡ ሩትን አስቧት፡ **ወሰነች**፡ ወደዚያ ለመሄድ ወይም ላለመሄድ መወሰን ነበረባት። ውሳኔ ማድረግ ነበረባት። አሁንም፡ እያንዳንዱ አማኝ ማድረግ ያለበትም በዚህ መንገድ ነው። የድሮ ዱካዎቻችሁን መተው አለባችሁ፡ አሮጌውን ህይወት መተው ይኖርባችኋል፡ አሮጌውን መተው—ያረጁ የዓለም ነገሮችን መተው ይኖርባችኋል።

106 ወንድም ሮይ፡ እህት ሮበርሰን ታማለች እንዴ? ኦህ፡ ምናልባት የታመመች ወይም የሆነ ነገር መሰለኝ። ከታመመች ወይም የሆነ ነገር ከሆነች ወደዚህ አምጣት ልልህ ነበር።

107 የድሮ የሕይወት ጎዳና፡ ወይም እንደዚህ ያለ ነገር መተው ነበረባቸው፡ ከዚያም—ከዚህ በፊት ከማታውቁት አዲስ ህዝብ ጋር፡ ወደ አዲስቷ ምድር ትሻገራላችሁ። ያደረጋችሁት ያ ነውን፡ ክርስቲያን ሆናችሁን? ከገንዳው ወጥታችኋል፡ የምሽት ክለቦችን ትታችኋል። የተረበሸ ስሜት ያላቸው ወደሚመስሉ ሰዎች ዘንድ መቀላቀል ነበረባችሁ፡ የሚንቀጠቀጡ እና የሚንፈራገጡ እና የሚጮኹ፡ ጭንቅላታቸውን እየወዘወዙ እና ወደ-ላይ-ወደ ታች ወደሚዘሉ ተቀላቀላችሁ፡ እና፡ ያም—ያም፡ ለ—ለእናንተ—ደ—ደግሞ "የእብድ ስብሰባ" ነው። ስለዚህ ለመሄድ ወይም ላለመሄድ መወሰን ነበረባችሁ። ትክክል ነው። እናንተም ከሄዳችሁ፡ ትታችኋቸው የመጣችሁ፡ የገዛ ወገኖቻችሁ እንደሚሳለቁባችሁ አስቀድማችሁ ታውቃላችሁ። ልክ ነው? ያ አውቶማቲክ ነው። ብቻ... ይህ እንዲጀምር መጠበቅ አለባቸው፡ ምክንያቱም እንደዛ ነው።

108 አሁን፡ ሩትም ተመሳሳይ ነገር ገጥሟታል። ወደ እስራኤል ወደ ጽንፈኞች ስብሰብ ለመሻገር ስትሄድ፡ ሞዓባውያን ምን ይሏታል? አያችሁ፡ ውሳኔ ማድረግ ነበረባት። መወሰን ነበረባት። እናንተም መወሰን ይኖርባችኋል። እና፡ በመጨረሻም፡ ውሳኔዋን ባደረገች ጊዜ፡ ወደ አዲሱ ምድር—ተሻግራ ገባች።

109 እንግዲህ፡ ያ ጽድቅ ነው። ልክ ነው? አሁን፡ ቤተ ክርስቲያ ይህን እዩ። ኦህ፡ ፍጹም ነው።

110 እንዴት እንደሆንን ታውቃላችሁ... ስለ **የአብርሃምን ዘር** ስሰብክ ሰንቶች ሰምታችኋል? **ስለ ጽድቅ፣ ቅድስና፣** የመንፈስ ቅዱስ **ጥምቀት**። አሁን፡ ይህ ልክ ይሁን አይሁን አሁን ተመልከቱ።

111 ሩት፡ የራሷን **ውሳኔ** ስታደርግ፡ የቤተክርስቲያን፡ የአህዛብ ቤተክርስቲያን ጥላ ናት። እሷም ወሰነች፡ እና ወደ ምድር ተሻገረች። አሁን፡ ብዙ ጊዜ፡ እኛ ሜቶዲስቶች እና ባፕቲስቶች፡ ማድረግ ያለብን ነገር ያ ብቻ ነው ብለን እናስባለን። ገና ጅማሬ ላይ ናት! ገና የትም አልሄደችም፡ ገና ወደ ምድሪቱ መግባቷ ነው።

112 አሁን፡ በመቀጠል ማድረግ የሚገባት ነገር፡ **መስራት** አለባት። የወግ ሰው ሆነች። ልክ እናንተ እንደምታደርጉት "በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ መዳኗን መስራት" ነበረባት። ወደ ማሳው ወጣችና ልብሷን በላይዋ ላይ ጣል አርጋ፡ በማሳው ለዕለት ጉርሻ የሚሆናትን ለመቃረም ከገረዶች ጀርባ ቃረመች። ልክ ነው? ምን እየሰራች ነበር? ከቦዔዝ ዘንድ ሞገስ ለማግኘት እየሞከረች ነበር። ስለዚህ በወግ ደረጃ ውስጥ ሠራች።

113 ቤተክርስቲያንም ያደረገችው ያ ነው። ሉተራኖች በእምነት አምነው ወደ ምድሪቱ መጡ። ሜቶዲስቶች ግን ቅድስናን አስተማሩ፡ ይህም የዚያ ነገር የወጉ ክፍል ነበር፡ አያችሁ፡ "የሆነ ነገር ማድረግ ይጠበቅባችኋል።" ሴቶች "ይህን መተው አለብኝ! ጸጉሬ እንዲያድግ ማድረግ አለብኝ፡" ይላሉ። በቃ፡ ከዚያ በኋላ እንደዚያ ማድረግ ይተዋሉ፥ አሁን ግን—እንዲህ ያደርጋሉ፡ ጸጉራቸውን ያሳድጋሉ። ፊታቸው ላይ የሚቀባቧቸውን ቀለሞች መተው ነበረባቸው። ቀሚሶቻቸውን—በተሳሳተ አለባበስ አ—አይለብሱም፡ ወይም፡ ሌሎቹ እንደሚያደርጉት ቁምጣዎች አያደርጉም። አንድ ነገር ማድረግ ይገባቸዋል። አያችሁ? እሷም እንዲሁ አደረገች፡ የጽድቅ እርከን፡ የቅድስና እርከን።

114 በመጨረሻ፡ በቦዔዝ ፊት ሞገስ ስታገኝ፡ ምን ሆነ? ኑኃሚንም እንዲህ አለቻት፡ "ቦዔዝ የዋርሳ ቤዛነት ሥራ እስኪሰራ ድረስ እዚህ **ጠብቂ**፡ ምክንያቱ ይህን ማድረግ የሚችለው እርሱ ብቻ ነው። እርሱ የቅርብ ዋርሳችን ነው፡ አንቺም እዚህ ጠብቂው። ከእንግዲህ ወደ ማሳው አትውጪ። **ይህን፡ ያንን፡** ወይም **ሌላውን** አታድርጊ። የቅርብ ዋርሳችን ጉዳዩን እስኪፈጽም ድረስ ጠብቂው።" ያን ጊዜ **አረፈች።** አሜን!

115 በዚህ የጸንጠቆስጤ የመጨረሻ ደረጃ ላይ ቤተክርስቲያን የመጣችው በትክክል ወደዚህ ነው። አያችሁ? በበዓለ ሃምሳ መጀመሪያ ላይ ሁሉም ስራቸውን ሰሩ እና "**ይህንን** ማድረግ ነበረበት፡" እና እነሱን ነቀነቋቸው እና ሌላም ሁሉ ነገር አደረጉ። አሁን ቤተክርስቲያን ምን እየሰራች ነው? እውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን **እርፋለች**። እረፍት ምንድን ነው? ይኸው ነው፡ **እረፍት** ማለት "መንፈስ ቅዱስ፡" **ሰንበት** ቀን ነው። (የሰባተኛው-ቀን አድቬንቲስቶች ስለ ሰባተኛው-ቀን ሰንበት መሆን፡ ወይም እንደዚያ ያለ ነገር ሊነግሩን ይፈልጋሉ፡ ታውቃላችሁ።) በዕብራውያን ምዕራፍ 4 ላይ፡ እንዲህ አለ፡ "ወደ **ዕረፍቱ** የገባን እኛ ከሥራችን አርፈናል እግዚአብሔርም ከሰራው እንዳረፈ።" ስለዚህ **ሰንበት** መንፈስ ቅዱስ ነው።

116 እና ሩት **ስታርፍ**፡ በእግዚአብሔር ተስፋዎች ላይ ያረፈችው የቤተክርስቲያን ምሳሌ ነበር! አሁን የመዳናችን ቀብድ አለን። ወደዚያ እንሄድ ይሆን አይሆን ብለን አሁን አንጨነቅም፡ እንሄዳለን! በትክክል። እግዚአብሔር ተናግሯልና! እግዚአብሔር ቃል ገባልን ቀብዱንም ተቀብለናል (አሜን።)፡ በቃ ተቀብለናል፡ ክርስቶስም ተቀብሎናል። ከእንግዲህ ከዚያ ሊያርቀን የሚችል ነገር የለም፡ ገብተናል! አሜን! እኛ ማድረግ ያለብን እስኪመጣ ድረስ መጠበቅ ብቻ ነው... ይወስደናል... የዋርሳን የቤዛ ስራ እየሰራ ነው። እርሱ ተመልሶ የሚመጣበትን ጊዜ እየጠበቅን፡ አሁን ቀብዱን ይዘናል።

ከዚያም ሩት ምን ሆነላት፡ ሩት **ሽልማቷን** ተቀበለች።

117 ቤተክርስቲያን ያደረገችው ይህንኑ ነው። በሉተር ስር፡ ወደ መጽደቅ ገባ። በዌስሊ ስር፡ ወደ መቀደስ ገባች። በዚህ በመጨረሻው ቀን፡ ወደ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ገባች። አሁንም በውስጣችን የሆነ ነገር እንደ ተፈጠረ እያወቅን ከርስታችን ቀብድ ጋር **አርፈናል**፡ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግረናል፡ ከተፈጥሮ ጋር እየቃተትን፡ የማይጠፋውን ህይወት የምንወርስባትን ጊዜ፡ የማይጠፋውን

ሙላት፡ የስውነታችንን ቤዛነትን ለመቀበል፥ በመጠባበቅ ላይ ነን። ሁሉም ነገር ተቤዥቷል፡ እኛም እርሱ ከደጅ እስኪመጣ ድረስ ብቻ እንጠብቃለን። አሜን!

118 ከዚያስ ምን ሆነ? ሩት **ተሸለመች።** እናም የምንሸለመው ያኔ ነው። ይህ በሰባት-ማሕተም የታተመው መጽሐፍ ሊከፍትልን ያለው ነገር ይህ ነው። እነዚህ ነገሮች ምንድን ናቸው? ሚስጥሮች ናቸው። በቃሉ ውስጥ የተጻፉ አይደሉም፡ መንፈስ ቅዱስ ሊገልጣቸው ይገባል፥ በርግጥ፡ ብታስተውሉት፡ በቅዱሳን መጻሕፍት መካከል የተገለጡ ናቸው ይሁን እንጂ ከሰዎች ተሰውረው ነበር። ከአፍታ በኋላ ወደ ጥቅልሉ ሰንገባ፡ አቀማመጣቸው እንዴት እንደሆነ ታስተውላላችሁ፡ ከዚያም ነገሮቹ እንዴት እንደተከፈቱ ታውቃላችሁ።

119 አሁን፡ አዎን፡ **እረፍት**። ሩት በመጽደቅ ሰር... ካያችሁት፡ “አሜን” በሉ። [ጉባኤው “ኣሜን፡” አለ።—አርታዒ።] ሩት በመቀደስ ሰር፡ **እየሰራች**፡ የሕግ ሰው ነበረች። ሩት፡ ቦዔዝን ከሥራው እስኪመለስ ድረስ ስትጠብቀው፡ **እረፍት** ላይ ነበረች።

120 አሁን፡ የእኛ ቦዔዛችን ሰራውን ሁሉ በቀራንዮ ላይ ጨርሷል። ነገር ግን ወደ ቤቱ ሊወስደን ከመምጣቱ በፊት፡ አስቀድሞ ስፍራ ሊያዘጋጅልን (በዮሐንስ 14) ወደ ቤቱ ሄደ። ክብር ይሁን!

> ልባችሁ **አይታወክ፥ በእግዚአብሔር** ካመናችሁ፡ **በእኔም ደግሞ እመኑ።**
>
> **በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ** አለ፥ **እንዲህ** ባይሆን **ኖሮ፡ በነገርኋችሁ ነበር። እኔ ግን እሄዳ**ለሁ **ሄጄ**ም **ቦታ አዘጋጅላችኋለሁ።**
>
> **እና... እናንተን** ለ**መውሰድ፡ እንደገና** እመለሣለሁ...

121 እነሆ፡ ቦዔዝም ወረደ፡ ምን አደረገ? ወርዶ፡ ቆመ... ሽማግሎችንም ይዞ በበሩ ፊት ሄደ፡ ጫማውንም አውልቆ፡ እንዲህም አለ፡ “ኑኃሚንንና ርስትዋን ሁሉ እንደ ተቤዠሁ ዛሬ ይታወቅ።” በዚያም ውስጥ ሞዓባዊትዋን አገኛት።

122 ኢየሱስ በመጣ ጊዜ፡ ማንን ሊቤዥ መጣ? እስራኤልን። እስራኤልን ሲወስድ ምን አደረገ? ከአሕዛብ ወገን የሆነችው ሙሽራ አገኘ። አዎን፡ እስራኤልን ሲወስድ፡ እንዲሁ አደረገ። እርሱም ሄደ... መሄድ ስለነበረበት፡ ወደ ገዛ ወገኖቹ ሄደ። በመጀመሪያ ምን ማድረግ ነበረበት? የራሱ የሆኑትን መቤዠት። የአሕዛብ ቤተክርስቲያን ደግሞ ለዚያች ሴት፡ የእስራኤል ቤተ ክርስቲያን እህት ናት። በትክክል! ስለዚህ **እቺን** ለማግኘት እስራኤልን መዋጀት ነበረበት። ሙሽራይቱን፡ ሩትን ለማግኘት ኑኃሚንን መቤዠት ነበረበት።

123 አሁን፡ ምን አደረገ? እሷን ከመውሰዱ በፊት... ኦህ፡ ክብር ይሁን! ዋው! ምን አደረገ? ወደ እርሻው ወጣ፡ ሁሉንም ነገር ቀባብቶ ወለል ላይ አዲስ ምንጣፎችን አነጠፈ። ኦህ፡ አ—አዲስ ቤት የገነባ ይመስለኛል። (በእኛ እሳቤ፡ አዲስ ቤት ነው።) እና ሁሉንም ነገር አዘጋጅቶ፡ ለሠርጉ የሰርግ ልብስ ይዞ ተመለሰ። አሜን!

124 ሩት ምን እያደረገች ነበረች? ምንም። እያረፈች! እየጠበቀች! ከእንግዲህ ድካም የለም፡ ግራ መጋባት የለም!

125 “ሜቶዲስት መሆን አለብኝን? ባፕቲስቶችን መቀላቀል አለብኝን? ፕሪስባይቴሪያን መሆን አለብኝን?” የለብህም፡ ወዳጄ፡ መንፈስ ቅዱስ ብቻ ተቀበልና እረፍ። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—እርታዒ።]

የተወደደችውን የሺ አመት መንግስት እንጠብቃለን፡ (ክብር ይሁን!)
የተባረከ ጌታችን መጥቶ የምትጠብቀውን ሙሽራ ይወስዳል፥
ኦህ! ምድር ስለ ነጻነት ቀንዋ፡ ትቃትታለች።

ፍጥረት፡ በሙሉ ይቃትታልና፡ የበለስ ቅጠሎች፡ ሁሉም ስለ ነጻነት ቀን ይናፍቃሉ፡ የዋርሳ ቤዛ መጥቶ ሙሽራይቱን የሚወስድበት ቀን።

126 ስለዚህ አሁን እረፍት ላይ ናት። በመቀደስ ስር ነውን? አይደለም። በመጽደቅ ስር ነውን? አይደለም። **በመጽደቅ**፡ **በመቀደስ**፡ እና **በእረፍት** በሁሉም ጭምር።

127 አሁን፡ ኢሳያስ፡ ምዕራፍ 28 እና 18ኛው ቁጥር፡ እንዲህ ይላል።

> ... **ትእዛዝ በትእዛዝ፡... ሥርዓት በሥርዓት፡... ጥቂት በዚህ፡ ጥቂት በዚያ ነው፥** መልካሙን ያዙ።
>
> **በባዕድ አፍ** በልዩም ልሳን **ለዚህ ሕዝብ ይናገራል እርሱም።**
>
> ... **ዕረፍት ይህች ናት፡** ስንበት ይህች ናት፡ ቤተክርስቲያን ወደ መጠበቅ መግባት ያለባት በዚህ ጊዜ ነው።

128 በመጽደቅ፡ በመቀደስ በኩል አሁንም በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አርገን፡ ወደ እረፍት፡ እና ወደ መጠባበቅ፥ አሁን እንዴት እንደደረስን ተመልከቱ። ይህ ምንድነው? አሁን፡ አሁንም፡ ወደ እነዚህ መገለጦች ስንደርስ አሁን ምን እንደሆነ ታያላችሁ። አያችሁ? ይገርማል... እስከዚህ ዘመን ድረስ እነዚህ ነገሮች ማስተማር አልተቻለም ነበር። እነዚህን ትምህርቶች ማስተማር፡ የማይቻል ነበር። ለሰዎች ልጆች አልተከፈቱም ነበርና። መጽሀፍ ቅዱስም ይናገራል። እስከ (የሰው ልጆች)፡ እስከ ዛሬ ድረስ አይከፈትም እንዳለ እዚህ በመጽሐፍ አሳያችኋለሁ። እና አሁን በእነዚህ ታላላቅ የተባረኩ ነገሮች ላይ እንጨርሰዋለን። አሁን... መልካም ነው።

129 6ኛ ቁጥር... ወይም የ5ኛው ክፍል፡ በ5ኛው ቁጥር ላይ ያለው ሽማግሌው “እነሆ፥ በጉ!” ብሎ እስከሚናገር ጊዜ ድረስ ይህ ነበር፡ ነገር ግን፡ ዙሪያውን ሲመለከት፡ አንበሳ አየ። በበጉ ፈንታ አንበሳ ነበር። ታዲያ ይህ ምን ማለት ነው? የመካከለኛነት ስራው አለቀ፡ መካከለኛነት። እንዲሁ... በቤተ ክርስቲያን ዘመን መጨረሻ ላይ መካከለኛ መሆኑን አቆመ፡ የይሁዳ ነገድ አንበሳ ለመሆን ያንን ነገር አቆመ፡ የመካከለኛነት ስራው አለቀ። ስለዚህ ፈራጅ የሆነውን አንበሳ መሆን ነበረበት፡ ስለዚህ፡ መጽሐፉን ከእጁ በወሰደው ጊዜ፡ ተቀበለው።

130 አሁን፡ አስታውሱ፡ ያ ሰው ዋርሳ ለመሆን በሄደ ጊዜ፡ አሁን ይህን እንዳትረሱት፡ ያ ሰው ዋርሳ ለመሆን በሄደ ጊዜ፡ ከእርሱ ጋር ሰዎችን ይዞ ወደ ከተማይቱ በሮች ሄደ፡ እነርሱም ሽማግሌዎች ነበሩ። በዚያም ደግሞ በዚያ የተገኘበትን ዓላማ ተ—ተ—ተናገራቸው። ያደረገው ይህንኑ ነው፡ ወደ በሩ

ሄደና፡ ተናገረ፡ “እኔ እንደ ዋርሳ ለዚህ ርስት ቤዛ ለመሆን ለማሳውቅ በዚህ መጥቻለሁ፡ እነሆም በከተማይቱ ሽማግሌዎች ፊት አሳውቃለሁ።” አያችሁ?

131 እና ዮሐንስ... ባለቀሰ ጊዜም። አሁን፡ ባለፈው ሳምንት እንዳልኩት፡ አንድ ሰው፡ “ዮሐንስ ያለቀሰበት ምክንያት ብቁ የሆነን ሰው ስላላገኘ ነው፡” አለ። ያ አልነበረም። በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ስር ያለ ሰው ለዛ አያለቅስም። የመሰለው፡ “እርሱ ብቁ አልነበረም፡” ምናልባት ዮሐንስ ራሱ ብቁ አልነበረም። የሚበቃ ማንም የለም። ይሁን እንጂ በዚያ ምክንያት አላለቀሰም።

132 አጠቃላይ የቤዛነት እቅድ እዚህ መፅሃፍ ላይ ስለተጻፈ በደስታ እያለቀሰ ነበር ብዬ አምናለሁ። የተገባው አንድም ሰው ስላልነብረ አይደለም፡ ምክንያቱ፡ በዚያ የነበረው በጉ ራሱ የተገባው ነበርና። ስለዚህ እያለቀሰ ነበር፡ እዚያም እንዲህ አለ፡ “ኦህ፡ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!” በቀጥታ መጮኽ ሲጀምር ሰሙት። አሁን ግን፡ እዚህ ሲያለቅስ እናየዋለን ምክንያቱም በጉ መጽሀፉን ስለወሰደ እጅግ ተደስቷል በ... በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠው ከእርሱ እጅ ወሰደው።

133 ልክ ይህ ሲያደርግ... ይሄኛው መልአክ፡ ብርቱው መልአክ፡ በታላቅ ድምጽ “የተገባው ማን ነው? ” ሲል ያን ጊዜ እያስተዋወቀ ነበር፡ የዋርሳውን ቤዛ በማስተዋወቅ ላይ ነበር። ወዲያውም፡ “መጽሐፉን መውሰድ የሚገባው ማነው? ” ባለ ጊዜ፡ አንድ ነገር ሆነ... ዮሐንስም ማልቀስ ጀመረ። ከዚያስ ምን ተፈጠረ? አየ፡ በዚያም የቆመ መጽሐፉ ነበር። እነሆ በዚያ ነበር፡ የተገባው ግን ማን ነው?

134 መልካም፡ ገብሪኤል በዚያ ቆሞ ነበር፡ እርግጥ ነው፡ እርሱም ብቁ ነበር፥ ነገር ግን፡ ተመልከቱ፡ እርሱ ሰው አልነበረም፡ መልአክ ነበርና። ሚካኤልም በዚያ ቆሞ ነበር፡ እርሱም ብቁ ነበር፡ እርሱም ግን ሰው ሳይሆን፡ መልአክ ነበር። ስለዚህ እንደ እኛ ምድራዊ ሰው የሆነ ሰው መሆን ነበረበት። ያን ጊዜም ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የታረደውን በግ፡ ሲመጣ ባየው ጊዜ፡ እና ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የታረደ መሆኑን ባየ ጊዜ፡ ያን ጊዜ ዮሐንስ አለቀሰ። አሜን! ምክንያቱ ያን ጊዜ፡ መላውን ነገሩን አይቷል። አያችሁ?

135 “የተገባው ማን ነው? ” እያለ ባስተዋወቀ ጊዜ ስለሚመጣው የዋርሳ ቤዛ ያስተዋውቅ ነበርና። እነሆም፡ በጉ ቆመ። እርሱ ምን አደረገ? የእግዚአብሔር መንፈስ ወዳለበት ወደ ዙፋኑ ሄደ፡ በዙፋኑም ላይ ከተቀመጠው ቀኝ እጁ መጽሐፉን ወሰደ። ሽማግሌዎቹም ሁሉ ወድቀው “ታርደሃልና አንተ የተገባህ ነህ፡” አሉ። አያችሁ? እና ያን ጊዜ እንዲህ ሆነ... ያ መጽሐፉ፡ ወይም የቤዛነት መጽሐፍ፡ ወ—ወይም በቤተ ክርስቲያን ዘመን ውስጥ የአማላጅነት መጽሐፍነቱ አበቃ፡ አሁን ቤዛ ሆነ።

136 አሁን፡ እንዴት እንዳደረገው መገለጡ በእነዚህ ሰባት ማኅተሞች ውስጥ ይገኛል። አሁን፡ እዚህ የምናስተውለው... የእርሱ የመካከለኛነት መጽሐፍ ስራ በተገባደደ ጊዜ፡ ስራው ተፈጽሟል፡ በቤተክርስቲያኑ መጀመሪያዎቹ፡ በሦስት ምዕራፎች ውስጥ ተጠናቀቀ። አሁን ግን መቤዠት፡ መቤዠት ሊገለጥ ነው። ይሄ ምንድነው? አሁን፡ ይህን መጽሐፍ በወሰደ ጊዜ... አሁን፡ ጥልቅ አስተሳሰባችሁን ለመልበስ ሞክሩ፡ ምክንያቱም፡ እነዚያን ሰባት ምሽቶች ስናገኛቸው፡ አሁን ት—ትረዱታላችሁ።

137 ካልተረዳችሁት፡ እጃችሁን ከፍ አድጋችችሁ፡ “አል—አልገባኝም፡” በሉ፡ እሺ፡ ይኸውላችሁ፡ እርግጠኞች እንድትሆኑ ስለፈለግኳችሁ ነው።

138 አሁን፡ አስተውሉ “ቤዛነት።” ከዚያ በኋላ፡ ስለ ቤተ ክርስቲያን የሚሰራው አማላጅነቱ እንዳለቀ፡ ያን ጊዜ እራሱን እንደ ዋርሳ ቤዛ አስተዋወቀ። አሁን እየተከታተላችሁ ነው? አሁንም ይህ ሁሉ እንዴት እንዳደረገው ለቤተ ክርስቲያን ሊገልጥላት ነው። ስለዚህ ይህ መገለጥ ከጀመረ፡ በመንገዱ ፍጻሜ ላይ መኖራችንን እናረጋግጣለን። አሜን! አሁን፡ ይህ ነገር እንዲህ ይሁን... ወይስ አይሁን፡ አሁን በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ስናልፍ ተመልከቱ።

139 ምን እየተገለጠ እንደነበረ፡ አውቀናል? የቤዛነት መገለጥ ምንድነው፡ እኛስ የተቤዠነው እንዴት ነበር? በእነዚህ የመጨረሻዎቹ ጥቂት ዓመታት ውስጥ የሆነውን ተመልከቱ፥ በኢየሱስ ስም በውሃ ጥምቀት መገለጥ፡ የዘላለም ገሃነም አለመኖር መገለጥ፡ ከዚህ በፊት አይታወቅም ነበር (የምትወዳቸው ሰዎች ለዘለአለም እንደሚኖሩ በማሰብ)። አያችሁ?

140 እና ካልዳናችሁ በቀር የዘላለም ሕይወት ሊኖራችሁ አይችልም። የዘላለም ሕይወት አግኝታችሁ፡ ለዘለዓለም በገሃነም ልትቃጠሉ አትችሉም። ስለ ኃጢአቶቻችሁ በሰጋዊ ተፈጥሮአችሁ ትቀጣላችሁ፡ በገሃነም ውስጥ ግን የዘላለም ህይወት ሊኖራችሁ አይችልም። የዘላለም ሕይወት ካላችሁ ግን፡ ለዘላለም መቃጠል አትችሉም ምክንያቱም የዘላለም ሕይወት አንዲት ዓይነት ብቻ ናትና። እና ቤተክርስቲያንም ይህንን እንደምትረዳው እርግጠኛ ነኝ።

141 አሁን፡ ይህ ምንድን ነው? ሌሎች ነገሮችስ ምንድናቸው? የመቤዠት እቅድ ናቸው። በቅርብ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ የተሰጠንን ነገር ተመልከቱ፡ አያችሁ፥ የአብርሃምን ዘር፡ ማለት መገለጡ ምን ማለት እንደሆነ ተመልከቱ።

142 የእባቡ ዘር። ይህን የራዕይ መጽሐፍ አይታችኋል? ወደዚያ ስንደርስ፡ እንዴት እንደሚከፈት ተመልከቱ። እናም ያ ትክክለኛው እውነት እንደሆነ፡ በዚህ በቅዱሳት መጻሕፍት አረጋግጫለሁ። ወደ ኋላ ወደ ራእይ ተመልሼ-... ወይም፡ ወደ ዘፍጥረት ተመልሼ አነሳና እና ያ ማሳተም በመጽሐፍ ቅዱስ በኩል ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ድረስ ሲከፈት፡ ያን ጊዜ አሳያለሁ።

143 እስቲ አስቡት፡ ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ድረስ “በአብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ” ስም የተጠመቀ አንድ የለም። የውሸት ጥምቀት ነው! ባለፈው ጊዜ በቺካጎ በታላላቅ የአገልጋይ ማኅበር ሰባኪዎች ፊት በሦስት መቶ ሰባኪዎች ፊት ቆሜ ነበር፡ ሁሉም እርስ በርሳቸው እስኪላቀሱ ድረስ አረጋግጬላቸዋለሁ። ከመካከላቸውም ሰባዎቹ በጌታ በኢየሱስ ስም ሊጠመቁ እየመጡ ነው።

144 ስለዚህ የእባቡ ዘር ከዘፍጥረት የጀመረ ነው! እባቡ እንዲህ ካልሆነ... ማለት እርሱ ዘር ከሌለው፡ እንግዲያውስ ክርስቶስም አልተወለደም፥ ምክንያቱም “በዘርሽ እና በእባቡ ዘር መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፡” ተብሏልና። እና የእባቡ ዘር ተረት ከነበረም ክርስቶስም ተረት ነበር፡ ቤተክርስቲያኒቱም ተረት ናት፡ አያችሁ፡ ሁሉ መለያየት አይቻልም። እባቡ ዘር ነበረው፡ አንደኛው የሚያንገዳግዳቸው ነገርም ይህ ነው። ለምን ሊረዱት አልቻሉም? ምክንያቱም መገለጡ የላቸውም።

145 ለምን መጥተው አይከራከሩም? ቸልፒቱ ሁል ጊዜ ክፍት ነው፡ ከማንም ጋር መገናኘት እችላለሁ። ከእነሱ ጋር አልከራከርም፡ ከእነርሱ ጋር እንደሞወያይበት ግን እርግጠኛ ነኝ፡ ከፈለጉ ነው... እንዳንዶቻችሁ ስህተቱ የት እንደሆነ እንድትነግሩኝ እፈልጋለሁ! ብዬ እዚያው በማኅበሩ ፊት ጠይቄቸዋለሁ። የሆነ ጥግ ቆማችሁ፡ በዚህ ነገር ላይ፡ ስለ እኔ አትናገሩ ኑ ወደፊቴ ቅረቡና ቁሙ። እስኪ—እስኪ በደንብ እንየው፡ ወደዚህ እንምጣ እና ማን ትክክል እና ስህተት እንደሆነ እንይ አልኳቸው። ግን አይቋቋሙትም። እውነቱን ለመናገር፡ በተሻለ መልኩ ያውቃሉ። አያችሁ?

146 ምክንያቱ፡ እኔ አይደለሁም፡ ነገር ግን የምታዩት የእግዚአብሔር መልአክ፡ መንፈስ ቅዱስ ራሱ ነው። ይህ ሁሉ በሆነበት በእነዚህ ቀናት፡ ይህ የእግዚአብሔር መልአክ አጠገቤ ሲቆም ምን ማለት ይቻላል? እነዚህን ነገሮች እኔ አላውቃቸውም ነበር፡ ዘመኑ ነው፡ ራሱ እዚህ ነው። በእነዚህ ሰባት መናፍስት፡ ሰባቱ ቀንዶች፡ እና ነገሮች ውስጥ ስናልፍ፡ ዛሬ፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ የት እንዳለ ታዩታላችሁ። ይህም—እነዚህ መገለጦች ሊመጡ ባለበት ሰዓት ላይ ያለንበት ሰዓት ነው። ይህ የራእይ መጽሐፍ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ነው። በመጀመሪያው ምዕራፍም፡ እርሱ ማን እንደ ሆነ፡ ማንነቱን ገልጿል። አሁንም ምድርን እንዴት እንደተቤዠ በመግለጥ፡ ወደ ሰባቱ ማኅተሞች እየገባ ነው።

147 ከእነርሱም አንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነበር። ሌላው ፍርሃትን ከህዝቡ እያሰወጣ፡ እንደ፥ የዘላለም፡ የዘላለም ቤዛነት፡ በእምነት መጽደቅ፡ መቀደስ፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። እና ምን? ጥርጣሬዎች ሁሉ ከሰዎች በማስወገድ፡ በዘላለማዊ ደህንነት የተጠበቅን መሆናችን ማሳየት ነው። እናንተም የመዳናችሁ ቀብድ ከተቀበላችሁ፡ እስከ ቤዛችሁ ቀን ድረስ አትሟችኋል። ኤፌሶን 4:30 እንዲህ ይላል፥

> **... እስከ ቤዛችሁ ቀን** ድረስ **የታተማችሁበትን፡ ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ።**

148 አሁንስ፡ እንዴት—እንዴትስ ትወድቃላችሁ? ምናልባት ትወድቁ ይሆናል። ነገር ግን አትጠፉም። በዚያ በውድቀት ላይ ከጸናችሁ ግን፡ ከመጀመሪያውም እንዳልተቀበላችሁት ያሳያል። የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ግን፡ “መስዋዕት አቅራቢው አንድ ጊዜ ከነጻ በኋላ የኀጢአት ሕሊና የለውም፡” ይላል ዕብራውያን። ያ እውነት ነው። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ተሞልታችሁ ወጥታችሁ በዓለም እየኖራችሁ፡ ክርስቲያኖች መ—መሆን አትችሉም። “ዓለምንና፡ የዓለምን ነገር ብትወዱ፡ የእግዚአብሔር ፍቅር በእናንተ ውስጥ የለም።” ስለዚህ የሆነ ቦታ ላይ የውሸት ድምጽ እየሰማችሁ ነው፡ ዲያቢሎስ ተንፍሶባችኋል። ህይወታችሁን በእግዚአብሔር ቃል መርምራችሁ በዚያ በመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ላይ እንደምትኖሩ ከተረዳችሁ፡ የዘለለም ደህንነት አላችሁ።

149 ስለዚህ ምንም የሚያስፈራን ነገር አይኖርም። እግዚአብሔር የገባውን ቃል፡ እግዚአብሔር ራሱ ይፈጽማል። ሁላችሁ ሰዎች ይህን እንድትቀበሉ እጠይቃለሁ። ይህን ተቀበሉ እና ከቃሉ ጋር ተጓዙ፡ ከዚያ በእናንተ ላይ የሚሆነውን ጠብቁ። ወንድሜ ሆይ፡ ሁሉንም እንዲፈጸም ያደርገዋል፡ እግዚአብሄርም ተናግሯልና። እግዚአብሔር ቃል የገባው ሁሉ፡ ይፈጸማል።

150 ስ... ስራዬ መጀመሩን አስቀድሜ ነግሬያችኋለሁና፡ በመላው ዓለምና በዓለም ዙሪያ ሁሉ ወደ አሥራ አምስት ዓመታት ገደማ ሆኗል፡ አንድም ቀን ወድቆ አያውቅም። ለምን? ምክንያቱም፡ በመሠረቱ፡ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ላይ ቆሜያለሁ። እውነት መሆኑን አውቄ ነበር። አንዳንድ ታላቅ የራሴ ጥበብ እንደሆነ እንድነግራችሁ አትጠብቁኝ፡ ነገር ግን የልብን ምስጢር የሚገልጠው ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ያሳየኝ እርሱ ራሱ ነው። ምክንያቱ ሲባል... የዛሬ ሰላሳ አመታት፡ ሰብከት መሰበክ በጀመርኩ ጊዜ፡ የሴት ጓደኛዬን እዚያ ተቀምጣ መጽሐፍ ቅዱስን እንድታነብ አደርጋት ነበር። ብዙ ትምህርት ስላልነበረኝ፡ ማንበብ እንኳን አልችልም ነበር። እህት ዊልሰን፡ ያኔ ሆፕ መጽሀፍ ቅዱስ ስታነብልኝ የነበረ ጊዜ ታስታውሺው ይሆናል፡ ቁጭ ብላ ታነባለች፡ እኔም እንዲህ እላቸዋለሁ፡ "የሚናገረውን ስሙት፡ እንደሚለው አድርጉ። እኔ ለእናንተ የምነግራችሁ ነገር ይህ ብቻ ነው።" ያን የሚያደርጉ ሁሉ፡ ለምን፡ ትክክለኛውን አግኝተውታል። ይኸው ነው። እ—እኔም...

151 እሷ "እግዚአብሔር አለምን እንዲሁ ወዶ አንድያ ልጁን ሰጠ፡" ትላለች።

እኔም "ይሄን ሰንቶች ታምናላችሁ? " "ቀጣዩን አንብቢው፡ የኔ ማር፡" እላት ነበር።

"አንድያ ልጁን ሰጠ፡ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት አለው።"

"ሰንቶች ታምኑታላችሁ? የሚለውን ነገር ስሙት፡" እላቸው ነበር። እራሴ ማንበብ አልችልም ነበር።

152 ስለዚህ፡ ተመልከቱ፡ ከየትኛውም ትምህርት ቤት የመማር መንገድ አልነበረኝም። ነገር ግን፡ ኦህ፡ እኔ የሄድኩባት ትምህርት ቤት እጅግ እወዳታለሁ! ኦህ፡ በዚያ በትንሿ ዋሻ ጥግ፡ እጆቼን ወደ እግዚአብሔር ዘርግቼ፡ ከቀን ቀን እንዲሁ እቆያለሁ፡ መንፈስ ቅዱስ በጣፋጭነቱ ወርዶ ራሱን መግለጥ ሲጀምር፡ እንዲህ ይለኛ ነበር፡ "**ይህ እንደዚህ** ነው፡ እና **ይህም እንደዚህ** ነው።" ከየትኛውም ዓይነት ፍጥረት፡ እና ማንም ሰው፡ እንዲህ ባለው ነገር ላይ እጁን ሊጭን አንድም እንኳ አይችልም። እና በምድሪቱ ሰፋት የተሰፋፋውን ወግ አጥባቂነት እና ነገሮች በሙሉ እያሉ፡ እግዚአብሔር ከማንም በላይ ከፍ አድርጎ ንጹሕ አድርጎታል፡ በምድር ዙርያ ሁሉ አዳርሶታል። ሃሌሉያ! ወንድሞች ሆይ፡ በመጨረሻው ዘመን ላይ ነን። እዚህ ያለነው በመጨረሻው ሰዓት ላይ ነው። ይኼው ነው። "ሲመሽ ብርሃን ይሆናልና።" እርሱ ያለው ይህ ነው።

153 ስለዚህ፡ ይህ የራእይ መጽሐፍ፡ እግዚአብሔር ራሱን የሚገልጥበት ነው። እናም አሁን በእነዚህ ታላላቅ ምስጢሮች፡ የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በጥምቀት እየገለጠ ነው፡ የዘላለም ሲኦል የሚባል ነገር እንደሌለ እየገለጠ ነው (ሊሆን አይችልም፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደዚህ ያለ ነገር እንዳለ የሚናገሩ ቅዱሳን መጻሕፍት የሉም)።

154 አሁን፡ ሲኦል አለ፡ የእሳት ባህርም ደግሞ አለ፡ ይህም ክፉዎች የሚቀጡበት ሲሆን፡ መጨረሻ ላይ ግን ተበልተው ይጠፋሉ። ምናልባት አሥር መቶ ሚሊዮን ዓመታት ሊሆን ይችላል፡ በኋላ ግን ተበልተው ይጠፋሉ። ምክንያቱም ካልዳናችሁ በቀር የዘላለም ሕይወት ሊኖራችሁ አይችልም። ለዘላለም ከተቃጠሉ ግን፡ የዘላለም ሕይወት አግኝተዋል ማለት ነው። ምነው፡ ስጋዊ አእምሮ እንኳን ይህን አይስተውም። አያችሁ? ዘለአለማዊነት እንዴት

ይኖራችኋል-… ? የዘላለም ሕይወትን አላችሁ ማለት ድናችኋል ማለት እንደሆነ ስንቶች ታውቃላችሁ? እንግዲያውስ፡ ለዘለአለም የምትቃጠሉ ከሆናችሁ፡ ዕውቅና ልትሰጡት የሚገባ ዘለአለማዊ ህይወት ያላችሁ አትሆኑምን? እንግዲያውስ፡ ተመከቱት፡ ትርጉም አይሰጥም። አያችሁ?

155 አሁን፡ "ደህንነት።" አስቀድሞ ያወቃቸውን፡ ጠራቸው፥ የጠራቸውንም፡ አጸደቃቸው፥ ያጸደቃቸውን እነርሱ ደግሞ፡ አክብሯቸዋል። ጳውሎስ በኤፌሶን ምዕራፍ 1 ላይ፡ እንዲህ ብሎናል፡ ይህም "እግዚአብሔር፡ ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ በክርስቶስ ኢየሱስ ልጆች ልንሆነው አስቀድሞ ወስኖናል።"

156 ዮሐንስ እዚህ በራዕይ ላይ እንዲህ ይለናል፡ "ጠላት በመጨረሻው ዘመን ላይ፡ ሃይማኖታዊ ጠላት፡ በሰዎች መካከል ገብቶ ድርጅቶች እና ልዩ ልዩ ነገሮች፡ ጥቃቅን አምልኮዎች እና ልዩ ልዩ ነገሮች፡" ዛሬ እንዳለ አይነት ነገሮች እንደሚያመጣ፡ "ቢቻል ኖሮ የተመረጡትን እስኪያስት ድረስ፡ እና ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ስሞቻቸው በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ላይ ያልተጻፉትን **ሁሉ** ያታልላል።"

157 ስምቻሁ በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ላይ የተቀመጠው መቼ ነው? ዓለም ከመፈጠሩ በፊት። ክርስቶስ የታረደው መቼ ነበር፡ ከሺ ዘጠኝ መቶ አመታት በፊት ነውን? አይደለም፡ ወዳጄ። ዓለም ሳይፈጠር በፊት ነው። "ዓለም ሳይፈጠር የታረደው በግ።"

158 ምን እየሰራ እንደሆነ ተመልከቱ? የሚከፈቱት እነዚህ ማኅተሞች ናቸው፡ የቤዛውን እቅድ፡ እንዴት እንደሚያደርገው መግለጥ ጀምሯል። አሁን ሁሉም ነገር አብቅቷል፡ ሊያልቅ ትንሽ—ይቀራል። ስለዚህ በመጨረሻው ሰዓት ላይ ነን። ስለዚህ ለዚህ ነው—ነገሮች እየተገለጡ ይገኛሉ። በጣም ጥሩ።

159 አሁን፡ ዋርሳችን በሰባት-ማሕተም የታሸገውን የቤዛነት መጽሐፍ ከዋናው ባለቤት ተሰጥቶታል። ዋናው ባለቤት… በኤደን ገነት፡ በአዳም ምክንያት፡ በጠፋብን ጊዜ ወደ መጀመሪያው ባለቤት ተመለሰ። በምድር ላይ ግን ቀማኛው መጣ፡ ዘራፊው፡ ያም ሰይጣን ነው፥ መጣ፡ እርሱም ቀማኛ ነው። ይህች ምድር የእርሱ አይደለችም፡ የእግዚአብሔር ናት። እሱ ግን ዘራፊ፡ ቀማኛ ነው። ሰው ሆይ፡ ልናገር ብል ብዙ የምለው ነገር አለኝ፡ ይሁን እንጂ ዝም ልበል። ይህ በሰባት-ማሕተም የታተመው መጽሐፍ፡ የቤዛችን የባለቤትነት ሰነድ ነው። የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ነው። ወደ እነዚህ ማህተሞች እስክንገባ ድረስ ጠብቁኝ!

160 ማኅተሙን ሰብሮ፡ ገለጠው፡ ርስቱንም ለእኛ ለሕዝቡ ሰጠን። እርሱ የዋርሳ ቤዛ በመሆን፡ የወረሰውን ርስት ሰጠን፡ እንዲሁ በነጻ ሰጠን። ሁሉም የሱ ነበር። የተቤዠውም እርሱ ነው። ነገር ግን ለራሱ ከማቆየት ይልቅ፡ መልሶ ለህዝቡ ሰጠው። ለእኛ ያለው ፍቅር ይህ ነው። ኦህ!

161 አሁን ሰፍሮባት ያለው፡ ሰይጣን፡ ዘራፊው፡ በስተመጨረሻው… ፈጥኖ መልቀቅ አይፈልግም፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ከትንሽ በኋላ እዚህ እናገኘዋለን፡ እዚህ በሌላ ምዕራፍ እያሰብኩት ነው። ፈጥኖ መልቀቅ አይፈልግም፡ ይልቁንስ ለመያዝ ይዋጋል እንጂ። ነገር ግን፡ በመጨረሻ፡ ወደ ትዕይንቱ በቀረበ ጊዜ፡ ወደ እሳቱ ባሕር ተጣለ። ትክክል ነው።

162 ኢየሱስ፡ በወንጌል ውስጥ ያለው **ኢየሱስ** የተባለው ስም አራት “የልጅነት” የማዕረግ መጠሪያዎች አሉት። ይህን ታውቃላችሁ? በወንጌል ውስጥ ኢየሱስ እንደ **ልጅ** አራት የማዕረግ መጠሪያዎች አሉት። ከመካከላቸው አንዱ “የዳዊት ልጅ”፥ ሌላኛውም “የአብርሃም ልጅ”፡ ሌላኛው፡ “የሰው ልጅ”፡ ሌላኛው፡ “የእግዚአብሔር ልጅ።”

163 አሁን፡ ተከታተሉ። የዋርሳ ቤዛችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሆነ ጊዜ፡ የዳዊት ልጅ ሆነ፡ እርሱም የዙፋን ወራሽ ነው። ክብር ይሁን! የዳዊት ልጅ በመሆን ዙፋኑን ወረሰ። እግዚአብሔር ዳዊትን ፈጽሞ እንደማይተወው አስቀድሞ ተናግሮት ነበር፡ “ዳዊትን ያለ ዘር አይተወውም።” ክርስቶስም የዳዊት ልጅ ነው። እናም እሱ የቅርብ ዋርሳችን ሆነ፡ እና ከእኛ ጋር የሚነግስበትን ስፍራ እያዘጋጀ፡ በመጠባበቅ ላይ ነን። እንደ ዳዊት ልጅ የዙፋኑ ወራሽ ነው።

164 እንደ አብርሃም ልጅ፡ የንጉሣዊው ስጦታ ወራሽ ነው። ኣሜን። ልክ ነው? እሱ የንጉሣዊው ስጦታ ወራሽ ነው (አሜን!)፡ ፍልስጤም እና በእሷ ውስጥ ያለውን ሁሉ፡ “የአብርሃም ዘር።” የአብርሃም ልጅ ነበር።

165 እንደ ሰው ልጅ፡ የሰው ልጅ ምን አደረገ... ሰው ምን አጣ? ምድርን አጣ። ስለዚህ የሰው ልጅ ስለሆነ በምድር ላይ ያለውን ሁሉ ወራሽ ነው። ያገኘው ሁሉ መልሶ ለእኛ ሊሰጠን ተገባው፡ ከዚያም ወደነበረበት ተመለሰ። እ...

166 አሁን፡ ስለዚህ፡ እንደ እግዚአብሔር ልጅም ሁሉን ወራሽ ይሆናል። እንደ ዳዊት ልጅ የዙፋኑ ወራሽ ነው፡ እንደ አብርሃም ልጅ የንግሥና የመዓርግ ወራሽ ነው፡ እንደ ሰው ልጅ የምድር ወራሽ ነው፡ እንደ እግዚአብሔር ልጅ በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ ወራሽ ነው። ኦህ፡ ማይ! ቤዛችን ይህ ነው፡ የዋርሳ ቤዛችን እርሱ ነው።

167 አሁን፡ አስተውሉ! ኦህ፡ ይህ ለእኔ በጣም ጥሩ ነው። እኔ ትክክለኛውን ምግቤ—እዚህ ውስጥ ነው። አሁን፡ ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ልባችሁ ለእግዚአብሔር ይፈታ። ይህንን ያዳምጡ።

168 ሰይጣን ቀማኛ ነው፡ በህጋዊ መንገድ የዚህ ባለቤት አይደለም፡ የባለቤትነት መብቱ የእርሱ ይሁን ወይስ የሌላ ሰው ላለፉት ሁለት ሺ አመታት ተከራክሯል። ክርስቶስ ግን እንደ ዋርሳ ቤዛ ሆኖ መጥቶ ለእኛ መልሶ ዋጀው። ሰይጣን ግን ይዟታል። ይሁን እንጂ፡ ይኸውላችሁ፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ (ይህ ውጊያ ያበቃል) ያን ጊዜ ወደ እሳቱ ባሕር ውስጥ ይጣላል። እያችሁ? ያን ጊዜ ያበቃለታል፡ ከእርሱ ጋር የሚያመልኩትንም ጭምር። የመዳን ወራሾች ግን ከክርስቶስ ጋር ይመጣሉ። አሁን፡ እሱ ቀማኛ ነው።

169 አሁን፡ አስታውሱ፡ በብሉይ ኪዳን፡ አንድ ሰው—ምድሩ ላይ ሌላ ሰፋሪ መጥቶበት ርስቱን ሲያጣ፡ ከባለቤቱ እስከ አምሳ ዓመት እስኪያልቅ ድረስ የመያዝ መብት የለውም። ከሃምሳ ዓመታት በኋላ ግን፡ የ—የኢዮቤልዩ ዓመት ይደርሳል። የኢዮቤልዩ ዓመትም፡ የኢዮቤልዩ ዓመት ሲመጣም፡ ሁሉም ነገር እንደገና ወደ መጀመሪያው ይመለሳል። ባሮች ሁሉ፡ ወደ መጀመሪያው ይመለሳሉ። አንድ ሰው በሜዳው ውስጥ እየቆፈረ መለከት መነፋቱን ሲሰማ፡ ዶማውን ጥሎ እንዲህ እያለ ይሄዳል፡ “ከእንግዲህ ባሪያ አይደለሁም፡ ወደ ቤተሰቤ ወደ ቤት እመለሳለሁ።” ነገር ሁሉ ይመለሳል። ቀማኛው መሬት

ላይ ከነበረ፡ ከመሬቱ ሊለቅ ይገደዳል። በቃ። ከመሬቱ ይለቃል ምክንያቱ ምንድነው? ሕጋዊው ባለቤት ስለመጣ። ቅድሚያ መስጠት አለበት።

170 ሃሌ ሉያ! ከእነዚህም ቀናት አንዱ የዚህ ዓለም መንግሥታት ይወድቃሉ፡ እና ህጋዊ ባለቤቶችም ከነዚህ ቀናት በአንዱ ውስጥ ይመጣሉ። ኣሜን።

171 አሁን፡ ክርክር ውስጥ የነበረበት ጊዜ ነበር። ከአርባኛው ቀን ጀምሮ፡ የመቅደሱን መንጻት የሚጀመርበት የመጀመሪያው ቀን ጀምሮ፡ ወይም ክርስቶስ ወደ ቀራንዮ ከሄደበት ጊዜ ጀምሮ፡ እስካረገበት ቀን ድረስ አርባ ቀናት ነበሩ። የሰይጣን ቡድን ወሰደው፡ እሱ ከሞት አልተነሳም ይሉ እንደሆነ ክርክር ውስጥ ነበር። በዚያም አዋጅ መጀመር ጀመሩ፡ እና እንዲህ አሉ። "ደቀ መዛሙርቱ መጥተው በሌሊት ሰረቁት።" መጽሐፍ ቅዱስን አንብባችኋል፡ "እንዲህም ተባለ 'የእሱ—ወገኖች መጥተው በሌሊት ሰረቁት።' ወታደሮቹ እንደዚያ እንዲያወሩ ገንዘብ ሰጧቸው።" ያኔ ግን በጥያቄ ውስጥ ነበሩ፡ ሁሉም ሰው ጥያቄ ውስጥ ነበር።

172 "እንግዲህ፡ የምር፡ ምናልባት የድርጅቱ አባል ሊሆን ይችላል፡ እንግዲህ፡ ነገሩ ሁሉ የድርጅቱ ነው።"

173 በአምሳኛው ቀን ግን የጴንጤቆስጤ ቀን ነበረ፡ ሕጋዊው ባለቤትም በመካከላቸው ዘንድ ወረደ (ሃሌ ሉያ!) ድርጅት አለመሆኑን አሳየ። የመንፈስ ቅዱስ መሞላት ነበር። ያም የገዛ ቤተ ክርስቲያኑ በድርጅቶች እና በልዩ ልዩ ነገሮች ቁጥጥር ስር እንዳትሆን የእግዚአብሔር የቀብድ ገንዘቧ ነበር፡ በኃይል እና በእግዚአብሔር ፍቅር የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ቀብድ ሆነ። አሜን! ኦህ፡ ይህ የሆነ ነገር እንዲሰማችሁ አያደርጋችሁምን? ሕጋዊው ባለቤት! የት ነበር? በእግዚአብሔር እጅ። እና ደግሞ...

174 አያችሁ፡ ስለዚህ ከአምሣ ቀናት በላይ መያዝ አልቻለም። ያንን ደግማችሁ—በዘሌዋውያን—በዘሌዋውያን ውስጥ፡ በሕጎቹ—ዘንድ ታገኙታላችሁ። እንዲህ አይችሉም ተባለ... ዋናው ባለቤት። ከሃምሳ ዓመታት በኋላ ወደ ዋናው ባለቤት እጅ መመለስ ነበረበት። ይህን ሁላችንም እናውቃለን። ያንን ብዙ ጊዜ አንብባችሁታል፡ ግን... ተመልከቱ፡ "ከሃምሳ ዓመታት በኋላ ወደ ዋናው ባለቤት መመለስ ነበረበት።"

175 እንግዲህ፡ ስለዚህ፡ ከእነዚህ ሃምሳ ቀናት-ዓመታት በኋላ፡ አንድ ዓመት... አንድ ቀን ማለት እንደ አንድ አመት ማለት ነው። እና እርሱን ከያዙበት ከሰቅለት ቀን ጀምሮ... ይህ የዋርሳ ቤዛ በፋሲካው ቀን ተይዞ—ከታረደበት ጊዜ ጀምሮ፡ ክርክር ነበር። ቤተ ክርስቲያን እስከዚያን ጊዜ ድረስ እርሱ የዋርሳ ቤዛ እንደሆነ ታምናለች፡ "እርሱ ቤዛ ነበርና።" ከዚያስ ምን አደረጉት? አረዱት፡ ይህን ያደረገው ጠላት ነው፡ ከዚያም አስከሬኑን አንስተው የሆነ ቦታ ደበቁት አለ። በሰዎች በሁሉም ዘንድ ጥርጣሬ ነበር፡ "ምን አጋጠመው? ምን ተፈጠረ? "

176 አሁን፡ በሃምሳኛው ቀን መገባደጃ ላይ፡ ይኸውላችሁ፡ ይኸው፡ ከዚያ በኋላ መጨቃጨቅ አልተቻለም። ስለዚህ፡ እግዚአብሔር... ከእነሱ ከአሮጌው ኦርቶዶክስ፡ ከግትር፡ ቀዝቃዛ ቤተ ክርስቲያን ጋር—ከመጓዝ ይልቅ፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን እንደገና ላከ፡ ቀማኞቹን ሁሉ አሰወገደ፡ ከዛ በኋላ ራሱ ተቆጣጠራት። የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወረደ እና ቤተክርስቲያኑ የመዳኗን ቀብድ ተቀበለች።

177 አሁንም፡ ወንድሞች ሆይ፡ ስሜታችሁን ወይም ምንም ነገር ለመጉዳት አይደለም፡ ድርጅቱ ትክክል ከሆነ እና በድርጅት ካቶሊክ ብቻ ከሆናችሁ፡ በድርጅቱ ባፕቲስት ከሆናችሁ፡ ጠፍታችኋል። አያችሁ፡ የመዳናችን ቀብድ የቤተክርስቲያን አባል በመሆን አልነበረም፡ የመዳናችን ቀብድ የአንድ ድርጅት አባል በመሆን አልነበረም። የመዳናችን ቀብድ ያለማንም ድርጅት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው! ኣሜን።

178 የዚያን ያህል፡ ከአምሳ ቀን በላይ መያዝ አልቻሉም፡ ምክንያቱም ያ ቀን ሁሉም ነገር ወደ መጀመሪያው የሚመለስበት የኢዮቤልዩ ቀን ነው። የ—የእግዚአብሔር ኃይልም ወደ ዋናው መጀመሪያው ተመለሰ፡ ሁሉ ነገር የተመለሰበት የኢዮቤልዩ ዓመት፡ በሀምሳኛው ቀን።

179 አሁንም፡ ሌላ የኢዮቤልዩ ዓመት ይመጣል፡ ይህም፡ ልክ በዚህ ጊዜ ያገኘነው ነው። ካስተዋላችሁ፡ በዚያ ጊዜ፡ ጴንጤቆስጤ በአሜሪካ ውስጥ ለሃምሳ ዓመታት ያህል እየወረደ ነው። ልክ የዛሬ ሃምሳ አመት ገደማ ጴንጤቆስጤ መውረድ ጀመረች። አሁን እየሆነ ያለው፡ ቤተክርስቲያኑ ባለ ሰባት-ማሕተም መጽሐፍ እየተቀበለች ነው እርሱም የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ (የሰባቱ ማኅተም ነው) ከእነርሱም አንድ አሰረኛ እንዳቸውም ሊቀበሉት አይችሉም።

180 ነገር ግን መጨቃጨቅ እና መወጠር እና መጎተት የሌለብን የኢዮቤልዩ አመት ማየት ሰትጀምሩ፡ እኛ በክርስቶስ ዘንድ አስቀድመን የተጠበቅን ነን! የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ሰም በጥምቀት ተቀብለናል። በእነዚህ ሰባት ማኅተሞች ውስጥ የምናነሳቸው እነዚህ ሁሉ ታላላቅ ምስጢሮች አሉን፡ ከሰዎችም ዓይኖች ተሸፍነው የታተሙ ማኅተሞች እንደ ሆኑ አስረዳችኋለሁ። እግዚአብሔር ረዳቴ ስለሆነ፡ ያንን ማየት እንደማይችሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ አረጋግጥላችኋለሁ (ያን ጊዜ፡ በርግጥ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ የሚል ከሆነ ታምናላችሁ።)፡ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ከ "አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ" በቀር ሌላ ማየት አይችሉም። እስከዚህ ጊዜ ድረስ ዘላለማዊ ሲኦል እንደሌለ፡ ማየት አይችሉም። ዘላለማዊ ደህንነት መኖሩን ማየት አልቻሉም-... ለእውነተኛው አማኝ ማለቴ ነው። እርግጥ ነው፡ የማይታወቅ ድምጽ የሚያሰሙ፡ በሁሉም ሰፍራ መሳለቂያዎች ሆኑ። ለዚህ ነው ህዝቡ... ሲናገሩ፡ "ለምን፡ ፕሪስባይቴሪያን እና የመሳሰሉትን ተመልከቷቸው፡ ያጨሳሉ፡ ይጠጣሉ፡ ሌላም ሁሉ ያደርጋሉ፡ በዚህ ሁሉ ዘለአለማዊ ደህንነት አለን ይላሉ።" አዎን፡ ይሁን እንጂ፡ ይኸውላችሁ፡ ይህ—እውነተኛውን መለከት እንዳይሰማ ለማድረግ ነው።

181 እስኪ እዚህ ወደ ኋላ መለሰ ብለን መለከት ድምጽ ያለው ከሆነ እንመልከተው፡ ካልቻላችሁ ወደ ኦሪት ዘፍጥረት ወደ ራዕይ፡ ወደ ኋላና ወደ ፊት ተመላለሱ፡ ይህ ማኅተም ሲከፈት፡ እያችሁ፡ እነዚህ ነገሮች ሲገለጡ ተመልከቱ።

182 አሁን፡ ኦህ፡ ወንድሜ! እንዲህ ይመስለኛል... ወደዚህ እንደገና እስክመለስ ድረስ እዚህ አቆማለሁ። ገና ሰድሰት ገጾች ይቀሩኛል፥ ወይም—ወይም፡ እሺ፡ ብቻ፡ የጥምቀት ስነ ሰርዓት ይደረጋል። እስቲ እነዚህን አንዳንድ ጥቃቅን ነገሮች፡ እዚህ ጋር ላንብብ፡ የኢዮቤልዩ ዓመት። በጣም ጥሩ።

183 አሁን፡ ሁላችሁ—ቃሉን እየጻፋችሁ ነውን? በኤርምያስ 32፡ ከ 6ኛው ቁጥር ጀምሮ... ወደ ቤታችሁ ስትመለሱ፡ ታነቡታላችሁ። አሁን፡ ይህ ጥቅልል ምን እንደሆነ ማየት እንድትችሉ፡ ከኤርምያስ፡ ይህን አወጣለሁ። ለማንኛውም፡ እስኪ ጥቅልሉን እንየው። ይህ ከጥቅልሉ ሌላ፡ አሰር ደቂቃ ያህል ይወስድብኛል። አሁን፡ አስታውሱ፡ መጽሐፉ የታተመ ነበር። አሁን፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የነበረው መጽሐፍ **እንደዚህ** ባለ አራት-ማዕዘን ቅርጽ ያለው መጽሐፍ አልነበረም። መጽሃፍ ተብሎ የሚጠራው፡ **እንዲህ** ያለ መጽሐፍ ነበር፡ "ጥቅልል።" ስንቶች ታውቁታላችሁ? ኧሃ-ሃህ። በትክክል፡ ጥቅልል ነበር። በጣም ጥሩ።

184 አሁን፡ ይህ—መጽሐፍ በሰባት ማሕተሞች ታትሞ ነበር። አሁን፡ ያ መጽሐፍ ቅዱስ በሰባት ማሕተሞች ታትሞ ነበር። አሁንም እንዴት እንደሚደረግ ተመልከቱ።

185 ኤርምያስ፡ እርሱ እንደሚወሰድ... በተናገረ ጊዜ—እንዲህ ይሆናል ባለ ጊዜ ትንቢት ተናግሮ ነበር። በኤርምያስ፡ ምዕራፍ 32 ላይ። ወደ ባቢሎን በምርኮ ተወሰደ፡ በዚያም ሰባ ዓመት መቀመጥ ነበረባቸው። ትንቢት ተናግሮ ነበር። እና እናንተ የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች ብዙ ጊዜ አይታችሁታል። ለሰባ ዓመትም ያህል ወደዚያ መሄድ ነበረባቸው። እና እርሱ—እርሱ ለሟቹ የአጎቱ ልጅ የቅርብ ዘመዱ ነበረ። የአጎቱ ልጅ (H-a-n-a-m፡ ደብል e, l) ሃናምኤል፡ ሃናምኤል፡ ሃናምኤል፡ የቅርብ... ዋርሳው እርሱ ነበር። ስለዚህ አንድ ነገር ተረዳ—ይህም ጠላት—ያንን ሰነድ እና መሬት ሊይዝ እንደሚችል—አወቀ፡ ነገር ግን... እግዚአብሔር ሕዝቡን ፈጽሞ እንደማይተዋቸው ስለሚያውቅ፡ ተመልሰው ሲመጡ፡ የርስቱ ባለቤት እንዲሆንና ትክክለኛ ባለቤት እንዲሆን፡ ያደረገውን ይህ ነው፡ ሁሉንም ነገር አዘጋጀ።

186 ስንቶቻችሁ አንብባችሁታል? በጣም ጥሩ፡ አንብባችሁታል፡ እንግዲያውስ አንብባችሁታል። በጣም ጥሩ። አሁን፡ ልክ እነዚህ ጥቅልሎች እዚህ በታሸጉበት መንገድ ወስዶ አተመው። እስካሁን ካያችሁት ድንቅ ነገር ይልቅ፡ እጅግ የሚያምር ነገር ነው።

187 አሁን፡ በዚህ ወረቀት በማሳያ ለማስረዳት እሞክራለሁ፡ ልቻል አልቻል ግን አላውቅም። አሁን፡ የተጻፈበት መንገድ፡ **ይኸውና**። አሁን፡ **እንዲህ** አዘጋጀውና፡ እያንዳንዱን ወደ ታች አተመው። አሁን፡ የተፈጸመው ነገር ይህ ነው፡ በእያንዳንዱ ማሕተም ዙርያው ላይ ስለ ርስቱ እና ስለተፈጸመው ነገር ተጽፎበት ነበር፡ በፊቱ ስለ ወደቁት ሁሉ እና እርሱ እንዴት መውረስ እንደቻለ። ሁሉም እንደዚያ ታትሞ ነበር።

188 ስለዚህ፡ እግዚአብሔር በሰባት-ማሕተም የታተመውን መጽሐፍ የያዘው በዚህ መንገድ ነው። አሁን፡ ይሔኛውን ሲቀደው፡ ያ መገለጥ ብቅ ይልና እስከ መጽሐፉ ጀርባ ክፍል ድረስ ወደ ፊት ወደ ኋላ ይመላለሳል። ለዚህም ነው የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ወሰዳችሁ እና ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ወዲህ እና ወዲያ ብታደርጉት "አባት፡ ልጅ፡ እና መንፈስ ቅዱስ" ብሎ ነገር እንደሌለ ትገነዘባላችሁ። አያችሁ? አይታችኋል፡ በመጽሐፍ ሁሉ ዙርያ ይሄድና፡ ይገልጸዋል።

189 ከዚያም ደግሞ “ዘለአለማዊ ገሃነም፡” የሚባል ነገር ያዙና። ያንን አውጥታችሁ ከላይ እስከ ታች ፈትሹት፥ ዘለአለማዊ ገሃነም ብሎ ነገር የለም ምክንያቱም በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሲኦል **የተፈጠረው** ለዲያብሎስና ለመላእክቱ፡ ለወደፊት ቅጣታቸው እንደሆነ ተናግሯል። ታዲያ ሲኦል ዘላለማዊ፡ ከሆነ እንዴት ሊፈጠር ቻለ? ፍጥረት የሚለው ቃል ፈጽሞ... **ዘላለማዊ** የሚለው ቃል፡ “መቼም ቢሆን ጅማሬ እና ፍጻሜ የለውም።” ሲኦል ዘወትር ከነበረ **ዘለአለማዊ** ሲኦል ከሆነ፡ “በተመሳሳይ ጊዜ ገሃነም ነበር፡ እግዚአብሔር በነበረበት ዘመን ሁሉ ገሃነምም ነበረ፥ ኃጢአት ከመምጣቱ በፊት ሲኦል ነበረ ማለት ነዋ።” ኧሃ! ኦህ፡ ማይ! አያችሁ፡ እንዲህ ማድረግ አትችሉም።

190 ስለዚህ እነዚህ ነገሮች እራሳቸው ሲገለጡ ተመልከቱ፡ ከላይ እስከታች ፈትሾ መጽሀፉን ይከፍታል። ስለዚህ አሁን ይህ የመላውን መጽሃፍ ቅዱስ ምስልና፡ መጽሐፍ ቅዱስ ከጠቢባንና ከአስተዋዮች ዓይን የሰወረው ማኅተም ይገልጣል። እግዚአብሔር፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ እንዲህ በመጽሐፍ ቅዱስ በኩል እየገለጠላቸው ነው። ክብር ለእግዚአብሔር!

191 ወንድሜ፡ እልሃለሁ፡ ይህ ነገር መንፈሳዊው—የምግብ ፍላጎቴን ያነሳሳብኛል። አየህ? እያችሁ? አሁን፡ ወደዚህ ተመልከቱ! አያችሁ፡ ይህ—ይህ ነ-... እ... ልላችሁ የፈለግኩት ነገር ተረድታችሁኛል? አያችሁ፡ ማኅተም፡ ነው። አሁን፡ እዚህ ጋር ተጠንቅቃችሁ ካነበባችሁ፡ ወደ ኤርሚያስ ሂዱና በማኅተም እ—እ—እ—እንዴት እንደዘጋው ተመልከቱ።

192 አሁን፡ ይህ መጽሐፍ፡ እዚያ ውስጥ ተጽፎበታል። አሁን፡ የመጀመሪያው መግለጥ ላይ፡ ይህን ማህተም ይከፍታል። አሁን፡ ወደ ማህተሞች ስንደርስ የመጀመሪያ ማህተም ምን እንደነበረ በደንብ ተመልከቱ። ከዚያም ለሁለተኛው ማኅተም ጊዜ፡ ቀጣዩን ማኅተም ያወጣል። እና የት እንዳለን ታውቃላችሁ? አሁን በሰባተኛው ማኅተም ላይ ነን ማለት ይቻላል። እና ይህ ሰባተኛው...

193 የመጀመሪያው ማኅተም በተከፈተ ጊዜ፡ የመጀመሪያው መለከት ነፋ የመጀመሪያውም መቅሠፍት ወረደ። ስድስተኛው ማኅተም በተከፈተ ጊዜ፡ ስድስተኛው ነፋ ስድስተኛውም መቅሠፍት ወረደ። ብቻ ዝም ብላችሁ ስትመለከቱት፡ እስካሁን ካያችሁት ነገር ይልቅ እጅግ የሚያምር ነገር ነው። ይሄን በማስተምርበት ጊዜ፡ ተለቅ ያለውን፡ ተለቅ ያለውን ጥቁር ሰሌዳ አዘጋጃለሁ፡ ከዚያም ወደዚህ አምጥቼ እያንዳንዷን ነገር እዚሁ አስተምራለሁ፡ ስለዚህ በእያንዳንዱ ማኅተም ላይ ብዙ ጊዜ ወሰደን ወደ ኋላ ተመልሰን ታሪክን እና ነገሮችን እናያለን፡ መቼ እንደተፈጸመም እናረጋግጣለን፡ ከዚሁ ከመጽሐፍ ቅዱስ ተነስተን መቼ ይሆናል እንዳለን አሳያችኋለሁ፡ የተፈጸመበት ትክክለኛውን ጊዜ፡ ቀኑ እና ሁሉ ነገሩ እናየዋለን። ገብቶኛል፡ አሜን፡ ከራሱ ተቀብያለሁ። ትክክል ነው። ማኅተሞች አሉ።

194 አሁን፡ ኤርምያስ ይህን መጽሐፍ ሲጽፍ፡ ታትሞ ነበር... አንባቢ የሆናችሁ ሁላችሁ፡ እነዚህ በማኅተም የተዘጉትን መጻሕፍቶች፡ እንድታስተውሏቸው እፈልጋለሁ... አሁን፡ አስታውሱ፡ እሱ ለመሄድ ተዘጋጅቶ ነበር። ትንቢትም ተናግሯል። አሁን፡ በትንቢት ካልሆነ በቀር፡ እሱም ነገሩን አያውቀውም። እየተከታተላችሁኝ ነው? ይሄን የሚያውቀው በትንቢት በኩል፡ በእግዚአብሔር

መገለጥ፡ ለሰባ ዓመታት ከዚያች አገር እንደሚወጡ አወቀ። ያንን ትንቢት ሲናገር ታስታውሳላችሁ? ሰባ ዓመት እንደሚሆን፡ በምርኮ እንደሚወሰዱ። ስለዚህ ይህ ማኅተም (ይህ ርስቱ) እንደሚጠበቅ እርግጠኛ መሆን ፈለገ፡ ምክንያቱም እሱ... የአጎቱን ርስት ወረሰ። ስለዚህ ሁሉንም ነገር፡ በሕጋዊ መንገድ እንዲጸፍ አደረገ። እሱንስ ምን አደረገው? እንዳይበሰብስ እና እንዳይዝግ፡ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አኖረው፥ ሰባ ዓመት እስኪፈጸም ድረስም፡ እንዳይበሰብስ ወይም እንዳይዝግ አስቀመጠው።

195 ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን! እንደሚገባችሁ ተስፋ አድርጌአለሁ! እግዚአብሔር ያደረገውን አይታችኋል? (ላለፉት ዘመናት ሁሉ ይኮፈሱበት ዘንድ) ለጥበበኞችና ለአስተዋዮች ፈጽሞ አልገለጠውም፡ እርሱ ግን በሸክላ ዕቃ ውስጥ አኖረው እና የየገዛ ልጁን፡ ክርስቶስ ኢየሱስን ፈጠረ። እናም በዚህ በመጨረሻው ዘመን አሁን ማህተሞቹን ከፍቶ ለቤተክርስቲያኑ እያሳያት ነው። እንዳይበሰብስ ወይም እንዳይዝግ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አኖረው! ሃሌሉያ! ኦህ! ሆሊ-ሮለር ነው ብላችሁ እንደምታስቡኝ አውቃለሁ። ምናልባትም ልሆንም እችል ይሆናል። አያችሁ? ነገሩ ግን ይህ ነው! ከምድር በቤዛነት ተዋጅቶ በወጣው ሸክላ ዕቃ ውስጥ ተቀመጠ፡ የሞት ማኅተሞች ከአሁን በኋላ ሊይዙት በማይችሉበት በፋሲካ ማለዳ ላይ መጣ፥ ነገር ግን ማኅተሞቹን ፈትቶ ተነሣና፡ በዚህ በመጨረሻው ዘመን ሕያው መሆኑን አረጋገጠ! አሁን በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ነው! ትናንትና፡ ዛሬ፡ እና ለዘላለም ያው ነው። ይህም ከሴሚናሪዎች፡ እና ከድርጅቶች ተሰውሮ ነበር።

196 በዚህ በመጨረሻ ቀናት እሱ ራሱ በህዝቡ መካከል ተገኝቶ ራሱ እየገለጠላቸው ይገኛል። ከውስጣቸውም ዓለምን እና ነገሮችን በሙሉ፡ ሐይማኖተኝነትን ከውስጣቸው የሚያወጣላቸው አንድ ሰው ተጠቅሞ፡ ስለዚህም በእነርሱ በኩል ይናገራል እነዚህን ማኅተሞች ይገልጣል ይከፍታልም። አያችሁ? ሃሌ ሉያ! ኦህ፡ አትወዱትምን? ማይ፡ ማይ፡ ማይ!

197 የመዳናችን ዕቅድ፡ ያው አሁን በኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጧል። በዚህ የመጨረሻ ቀን እንዴት ገለጠ? በእርሱ በኩል ማኅተሙን ከፈተ። ለምን፡ ከማንም ዘንድ... በሕይወታችሁ ስለ አብርሃም ዘር፡ በመጽደቅ፡ በመቀደስ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት እንዴት እንዳለፋ ሲጸፍ አይታችሁ አታውቁም፡ መልአኩ በመጨረሻው ዘመን እንዴት እንደሚመጣና፡ ጀርባው ወደ ጉባኤው አዞሮ ሣራ በውስጥ ሆና የምታስበውን የልቧን አሳብ በትክክል እንዴት መናገር እንደሚችል፡ ይህ ሁሉ እስከዚህ ዘመን ድረስ አልነበረም፡ እውነት ነው፡ ዘመኑ ይህ ነው፥ እንዲሁም የአብራሃም እምነት፥ እና የኢየሱስ ክርስቶስ ስም።

198 አሁን፡ እዚህ አንድ ነገር፡ ለመናገር የምፈልጋቸውን አምስት ነገሮች አሉኝ፡ አንዴ ጠብቁኝ፡ ቶሎ እጨርሳለሁ። ተመልከቱ። ሰባት... ሰባት ማኅተሞች አሉ፡ እና በእግዚአብሔር የመቤዠት እቅድ ውስጥ አምስት ሰባት ሰባቶች አሉ። **አምስት** የ "ጸጋ" ቁጥር ነው። ሰንቶች ታውቁታላችሁ? J-e-s-u-s፣ f-a-i-t-h፣ አምስት የጸጋ ቁጥር ነው። **ስድስት** የሰው ቀን ነው፡ **ሰባትም** የእሱ የ—የቤዛነቱ ቀን ነው።

199 አሁን፡ ተመልከቱ። በዚህ ውስጥ ሰባት ማኅተሞች አሉ፡ ወይም—ወይም በዚህ ታላቅ የመቤዠት እቅድ ውስጥ ሰባት ደረጃዎች አሉ። ሰባት ምን አሉ?

ሰባት የቤዛነት ማኅተም፣ ሰባት የእግዚአብሔር መናፍስት... **ሰባት መናፍስት** እንደሚል ማየት ከፈለጋችሁ፡ ማየት እንችላለን፡ አንዱ ከዚህ ላውጣው፡ 5ኛው ምዕራፍ፡ ከ 6ኛው ቁጥር ጀምሮ ይመስለኛል፡ እዚህ ላይ እናያለን፣ 6ኛው ቁጥር፦

> **በዙፋኑ፡ እና፡ በአራቱ እንስሶች፡ መካከልም...** እነሆ፡ **በሽማግሌዎችም መካከል፡ እንደ ታረደ በግ ቆሞ አየሁ፡ ሰባትም** ራሶችና **ሰባት ዓይኖች ነበሩት፡ እነርሱም ወደ ምድር ሁሉ የተላኩ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው።**

200 እነዚህ ሰባት መናፍስት ምንድን ናቸው? ሰባት መልእክተኞች ናቸው። ሴንት ኩሉምባ፡ እና ኢራኔዎስ፡ እና—እና ጆን ዌስሊ፡ እና ማርቲን ሉተር፡ እና የመሳሰሉት። አያችሁ፡ “ሰባቱ መናፍስት፡” ሰባት ሰዎች (ሰባት መላእክቶች)፡ ማለትም ሰባት መልእክቶች ናቸው።

201 ሰባት ማኅተሞች፣ ሰባት መናፍስ፣ ሰባት መላእክት፣ ሰባት ቀንዶች፣ እና ሰባት አብያተ ክርስቲያናት። ሰባት ሰባቶችን፡ ተመልከቱ፡ አምስት ሰባቶች አሉ፡ ይህም፡ **ሰባት** ማለት “ፍጹምነት፡” **አምስት** ማለት “ጸጋ፡” የእግዚአብሔር ጸጋ ለሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት። የእሱ ሰባት መልእክተኛ ሰዎች፡ ሰባቱ የእግዚአብሔር መንፈሶች፡ ሰባቱ የቤዛ ማኅተሞች ዕቅዶች (እኛ አሁን በዚያ ገብተን እንገኛለን)፡ ሰባቱ **ቀንዶች** ማለት ሰባት “ዘመናት” ናቸው።

202 ምክንያት፡ **ቀንድ** ማለት “ሰርወ መንግሥት” ነው። በዳንኤል እና በሌሎች፡ በአውሬው (ቀንድ) ላይ አክሊል እንደመጣ ታስታውሳላችሁ? ስለዚህ፡ ሰርወ መንግስት፡ ወይም “ሰባት ዘመናት” ናቸው። ኢየሱስ፡ ያለውም፡ አስታውሱ፡ “አንዳንዶች በመጀመሪያው ሰዓት አንቀላፉ፡ ማለት አንደኛው ዘመን፥ ሌሎች በሚቀጥለው ሰዓት፡ በሚቀጥለው ዘመን፥ ቀጥሎ፥ እና ቀጣዩም፥ እስከ ሰባተኛው ሰዓት ድረስ ደረሰ። እና በሰባተኛው ሰዓት ሙሽራው መጣ፡ እና ሁሉም ነቁ።” ያን ታስታውሳላችሁ?

203 ስለዚህ ሰባት “ዘመናት” ናቸው ሰባቱ **ቀንዶች** ነበሩ፡ ሰባት **አብያተ ክርስቲያናትም** ናቸው፡ ወይም “ሰባት የ-... የአማኞች አካል የዘመን ሙላቶች ናቸው።” ኦህ፡ በነገር ሁሉ ፍጹም ነው። ኤርምያስ... ማይ፡ “መጽሐፉ፡” “ዘመናት፡” እንዴት ተቤዠ! እንዴት... [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]... እዚህ ጋር።

204 ከእነዚህም ማኅተሞች ሰባት እና የመጨረሻው፡ ሲከፈቱ፡ በራዕይ ምዕራፍ 10 ላይ ይገኛል፡ አንድም ብርቱ መልአክ (እርሱም ክርስቶስ ነበረ) አንድ እግሩን በምድር ላይ አንዱንም በባሕር ላይ አደረገ፡ እጁንም አንሥቶ “ዘመኑ አልቋል። ጊዜው አልቋል። ሁሉም ነገር አልቋል። ከእንግዲህ ጊዜ አይሆንም፡” አለ።

205 እርሱም “ድምጹም በሚሰማበት ዘመን... ያን ጊዜ፡ የእግዚአብሔር ምሥጢር ይፈጸማል፡” አለ። እግዚአብሔር ማን እንደሆነ እና እንዴት እንደተገለጠ፡ ማኅተሙ መቼና እንዴት እንደተከፈተ፡ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነና፡ እሱ ራሱ በስጋ የተገለጠ እግዚአብሔር እንደሆነ አሁን መረዳት ጀመርን፥ እንዲሁም እርሱ ማን እንደሆነ ተገለጠልን፥ ይህ ጊዜ ሳይመጣ በፊትም መልአክ እግሩን በምድርና በባሕር ላይ ሲያደርግ ጊዜ “ከእንግዲህ ጊዜ

አይሆንንም” በማለት ማለ። እኛም አሁን በሰፍራው ፊት ለፊት ደርሰናል። እያችሁ?

206 ከእነዚህም ሁሉ የመጨረሻው ራእይ 10 ነው፡ “እግሩ በምድር እና በባሕር ላይ፥” ያኔ ጊዜ አልቆ፡ ቤዛነት አብቅቷል፡ አሁንም እነሆ እንደ አንበሳ ገባ። ያኔ በግ ነበር፡ አሁን ከይሁዳ ነገድ የሆነ አንበሳ ሆኖ ገባ።

207 አሁን፡ ቶሎ እንድጨርሰው፡ የቀረውን ይህን እና 8ኛውን ቁጥር ላንብበው፡-

**መጽሐፉንም በወሰደ ጊዜ፡ አራቱ እንሰሶችና** ሀያ-... **ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በበጉ ፊት ወደቁ፡ እያንዳንዳቸውም በገናንና፡ የቅዱሳን ጸሎት የሆነ፡... ዕጣን የሞላበትን የወርቅ ዕቃ ያዙ።**

208 አሁን፡ በሁሉ መመለክ ያለበት ጊዜ ይህ ነው። አሁን፡ ምን ያህል ተገቢ እንደሆነ፡ አስታውሱ። አሁን፡ ይህን እንዲያመልጠን። በደንብ ስሙኝ። የቤተ ክርስቲያን ዘመን ምስጢራት ሁሉ በተፈጸሙ ጊዜ፡ የቤዛነት ዕቅድ ምሥጢራት ሁሉ ሲፈጸሙ፡ ሰባት ማኅተም ተከፈቱ... ከዚህ ነገር በኋላ ወዲያውኑ፡ ተመልከቱ፡ በሰማይ ያለው እና በምድር ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን የሚያመልክበት፡ የሁሉንም—ጊዜ ይህ ነው። አሁን፡ ምን እንደሚከሰት ተመልከቱ። አዳምጡ... ይህን፡ አንድ ደቂቃ ብቻ አዳምጡ።

**በምድርም ላይ ይነግሣሉ፡ እያሉ፡ አዲሰን ቅኔ ይዘምራሉ...**

209 ይህ ምን አይነት አምልኮ እንደነበር ሰሙት! ሙሉ እቅዱን በፈጸመ ጊዜ፡ ሽማግሌዎቹ፡ እንሰሶቹ፡ ሁሉም በፊቱ ወደቁ፡ ልክ፡ እንደዚያ። ስለዚህ የአምልኮ ጊዜ አሁን ነው፡ እዩት፥

**አዲሰ ቅኔም** ዘመሩ፡ **መጽሐፉን ትወሰድ ዘንድ፡ ማኅተሞቹንም፡ ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፥ ታርደሃልና፡ በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ፡... ከቋንቋም፡ ሁሉ ከወገንም ሁሉ፡ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተ**ሀ፥

**ለአምላካችን ነገሰታትና ካህናት እንሆን ዘንድ** አደረግከን፥ **እኛም በምድር ላይ እንነግሳለን።** (የተዋጁት ነፍሳት ድምጻቸውን ሲያሰሙ፡ ሰሟቸው። እምም!)

**አየሁም፡ በዙፋኑም በእንሰሶቹም በሽማግሌዎቹም** ዙሪያ **የብዙ መላእክትን ድምፅ ሰማሁ፤ ቍጥራቸውም እእላፋት ጊዜ እእላፋትና፡** ሺህ **ጊዜ ሺህ ነበር፥** (በሰማይ ያሉ ሁሉ ይህን በግ እያመለኩ ነው፡ ተመልከቱ።)

**በታላቅም ድምፅ፡ የታረደው በግ** (ሃሌሉያ! ሃሌሉያ!) **ኃይልና፡ ባለ ጠግነት፡ ጥበብም፡ ብርታትም፡ ክብርም፡ ምስጋናም፡ በረከትም ሊቀበል ይገባዋል አሉ።**

210 ሰሙኝ፡ “ፍጥረት ሁሉም!” ዮሐንሰ የሚለውን ሰሙት፡-

**በሰማይና በ... ምድርም፡ ከምድርም** በታች፡ **በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ፡ በእነርሱም ውሰጥ ያለ ሁሉ፡ እኔ** (ዮሐንሰ) **ሰናገር ሰሙ፡** በረከትና፡... **ክብር፡... ምሰጋናም፡... ኃይልም፡ ከዘላለም እሰከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ** ለተቀመጠው፡ **ለበጉም ይሁን ሰል ሰሙ።**

211 ዮሐንስ በእርግጥ የራሱ የሆነ በዓለ ሃምሳ ሳይሆንለት አልቀረም። እንዲህ አለ፡ “በሰማይ ያለው ፍጥረት ሁሉ፡ በምድር ያለው ፍጥረት ሁሉ፡ ከምድር በታች ያለው ፍጥረት ሁሉ፡ በባሕር ውስጥ ያለው ፍጥረት ሁሉ፡ እኔ እንዲህ ስል ሰሙኝ፡ ‘አሜን፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ኃይልና፡ በረከት፡ በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው፡ ለበጉ ይሁን።’”

212 የአምልኮ ጊዜ! አሜን! “እንዴት አደረጉት?” እነሆ ቃሉ፡ እናንተም... ሁሉም ሰሙት።

> **አራቱም እንስሶች፡ አሜን አሉ።** አንተ ልክ ነህ፡ ዮሐንስ፡ በታላቅ ድምጽ አወድሰው። እ...
>
> ... በረከት፡ አሜን፡ **ክብር**፡ ጥበብ፡ **ኃይል፡** ብርታትም፡ **እያልኩ ሰሙ**...
>
> **... ሀያ አራቱ ሽማግሌዎቹም** ለተቀመጠው... **ከዘለአለም እስከ ዘለአለም ለሚኖረው ወድቀው ሰገዱ።**

213 እንዴት ያለ ውብ ታሪክ ነው! አሁን፡ ጊዜ የለኝም። እዚህ ላይ አንዳንድ አንቀጾች፡ ጽፌ ይዣለሁ፡ ነገር ግን ወደዚህ ከመግባታችን በፊት ቀጣዩ ስብሰባችን ላይ... ምናልባት ከእረፍት ሰመለስ ወይም ሌላ ጊዜ ሰመጣ፡ እነዚህን የዳንኤል ሰባ ሳምንታትን ከዚህ ጋር በማስተሳሰር አስተምራለሁ፡ ወደ ጴንጤቆስጤ ኢዮቤልዩም እንደሚወሰድ አሳያችኋለሁ፡ ከዚያም ከመሄዳችን በፊት ሰባቱ ማኅተሞች ለመክፈት ከሰባቱ፡... ነገሮች ጋር እናመጣቸዋለን፡ እና በመጨረሻ ላይ እንደሚሆ፡ እነዚህን አሳያለሁ...

214 በጉ፡ መሲሁ፡ ልዑሉ መምጣት አለበት ለሕዝቡም የተነበያቸው ሰባ ሳምንታት (ያም ሰባት ዓመታት ናቸው) መፈጸም አለባቸው። ከዚያም ልዑሉ መኃል ላይ ይቆረጣል፡ ያም ሶስት ተኩሉ ማለት ነው፡ የሰባት ግማሽ ሶስት ተኩል ነውና፡ ያኔ ይቆረጣል። የዘወትር መስዋዕትም ይቋረጣል፡ የጥፋት ርኩሰትም (ይህም መቅደሱን ባቃጠሉ ቀን በቤተ መቅደሱ ግቢ ላይ የቆመው የዑመር ሙስጊድ ነው)፡ ከዚያም ለእስራኤል የቀረላቸው ሦስት ዓመት ተኩል አለ።

215 ክርስቶስም መጥቶ በትክክል ሦስት ዓመት ተኩል ብቻ ሰበከ እንዲሁም ትንቢት ተናገረ፡ የዕለት መስዋዕት ተቋረጠ፡ ሁሉም ነገር በተቻለ መጠን ፍጹም ሆነ። የዑመር መስጂድም መኃሉ ላይ ተገነባ... በዚያው ቦታ ላይ ተገንብቶ እስከ ዛሬ ድረስ ቆሟል። የአሕዛብም ዘመን እስኪፈጸም ድረስም የኢየሩሳሌምን ቅጥር ይረግጣሉ፡ ቤተክርስቲያኒቱ ማለት (የተመረጡት፡ ሙሽራይቱ) ከዚያ ትወሰዳለች።

216 ከዚያም ሁለቱ ነቢያት፡ ሙሴና ኤልያስ፡ ለተቀሩት ሁለት እና—ሁለት ከግማሽ... ሶስት ከግማሽ ዓመታት ወደ እስራኤል ይመለሳሉ። እንዲህ ወጥቶ ስታዩት ከምንም ነገር በላይ የሚያመር ነገር ነው።

217 ትወዱታላችሁ? በሙሉ ልባችሁ? በሰባት-ማኅተም የታተመው መጽሐፍ ምንም እንደነበረ አሁንስ ገባችሁ? ምንነቱን፥ አሁን፡ “በብራናው ጥቅል፡” ደርሰንበታል። እና ልክ በእነዚህ የመጨረሻ ቀናት ውስጥ፡ አስታውሱ... በሸክላ ዕቃ ውስጥ ተቀመጠ። አሁንስ ይህ ገብቷችኋል? የሸክላው ዕቃስ ማን ነበረ? ኢየሱስ ክርስቶስ። የደረሰበት አንድም አልነበረም፡ ማንም አላገኘውም፡

በእርሱ ብቻ ነው። በቃሉ ውስጥ እንኳን አልተጻፈም ነበር። በቃሉ ከልተጻፈም፡ እንዳታገኙት ተደብቆ ነበር። በትክክል። ስለዚህ የተገለጠው በእርሱ ዘንድ ነው፡ እናም በዚያ በሸክላው ዕቃ ውስጥ አይበሰብሰም ወይም አይዝግም።

218 እና መጣና ፊተኛውን ለገዛ ቤተክርስቲያኑ መዘዘላትና፡ እንዲህ አለ፡ "እያችሁ፡ እኔ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እና እስከዘለአለም ድረስ ያው ነኝ። እያችሁ? እያችሁ? አሁን፡ ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ግራ የሚያጋባችሁ ነገር ነበረ—ኃጢአተኛው ለዘለአለም ይቃጠል ይሆን ወይስ ከአንድ ሚሊዮን ዓመታት በኋላ ይጠፋል። እንዲህ ነው። ከድሮ እንዲህ ነበረ። ዘለአለማዊ ገሃነም ብሎ ነገር የለም። ዘላለማዊ መሆን አይችልም፡ ምክንያቱም ከ... ከመጀመሪያው ገሃነም ከእኔ ጋር አልነበረም። ክፋዎችን ለመቅጣት እኔ የፈጠርኩት ነው። እያችሁ? እያችሁ፡ ስለ አብርሃም ዘር እና ስለ እነዚህ ሁሉ ልዩ ልዩ ነገሮች፡ ምን ያስፈራችኋል? በቃ... " ይኸኛው—ዝም ብሎ ላይ ላዩ ነው፡ እያችሁ፡ ነገር ግን እግዚአብሔር እነዚያን ማኅተሞች እንዴት እንደከፈታቸው ስታስተውሉ፡ እንዲሁም ደግሞ ስትገነዘቡት፡ ወደ ታች ወረድ በሉ፥ እያችሁ፡ ያን ስታደርጉ፡ ከዚህ መጽሐፍ መራቅ አትችሉም። ማኅተሞቹ...

219 እናንተም "ኦህ፡ ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ የማኅተሞቹ ምስጢር ሌላ ነው፡" ትላላችሁ።

220 ቆዩ እስኪ! **ከዚህኛው** ጋር መነጻጸር አለበት፡ ምክንያቱ **ይሄኛውን** ለመግለጥ **ከዚህኛው** ጀርባ ላይ የታተመ ነበር። ይሄ... ይህ ምንድነው? ይህ ምን ነበር? እዚህ ጋር፡ እንደ፡ ኤርምያስ። **እንዲህና-እንዲያ** የሆነ ነገር ተፈጸመ ትላላችሁ፥ **ይሄኛውን** ስትመዙት፡ ጉዳዩ እንደተቀመጠ ይገኛል። በጣም ጥሩ። **ያንን** ቅደዱትና ወደዚህ መለስ ብላችሁ ተመልከቱ፡ ምን ምን እንደተፈጸመ ማንበብ የምትችሉት እዚህ ጋር ነው። በጣም ጥሩ። **ይሔኛው** ከዚህ ቀዳችሁ ስታስወግዱት፡ እዚህ ጋር እዩ፡ ከዚያም ይህ ይሆናል። እያችሁ፡ ይህ መጽሐፍም፡ እያችሁ፡ ከበስተጀርባው በኩል ተመሳሳይ ነገር ነው።

221 እንዲህ ይላሉ፡ "እንግዲህ፡ ሊገባኝ አልቻለም። አንዳንዶች፡ 'አብ፡ ወልድ፡' አንዳንዶችም፡ 'መንፈስ ቅዱስ፡' አንዳንዶችም፡ 'በኢየሱስ ስም፡' የመሳሰሉ ነገሮች ይላሉ።"

222 ባለፉት ዘመናት ሁሉ ተሰውሮ ቆየ። አሁን ግን ይኸው መጣች፡ እንደገና መጣች፡ አምላክ ብቻ እንዳለ ለማሳየት ወዲያውኑ ተመለሰ። አንዱ አምላክ እንጂ ሌላ አልነበረም። ያ እውነት ነው። ሰሙም...

223 እንደ ማቴዎስ መጽሐፍ፡ 28፡19፣ "እንግዲህ ሂዱና፡ አሕዛብን ሁሉ፡ በአብ፡ በወልድና፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፡" አብ ስም አይደለም፡ ወልድም ስም አይደለም፡ መንፈስ ቅዱስ ስም አይደለም። እንግዲያውስ፡ እንዴትስ ታጠምቋቸዋላችሁ? አንዳቸውም ስም ካልሆኑ፡ በየትኛው ስም ታጠምቋቸዋላችሁ? ከዛስ? እንግዲያውስ፡ በሌላ በማንም አታጠምቁም። ያ እንደገና የነቢያት ልጆች ትምህርት ነው፡ እያችሁ።

224 ከዚያ በኋላ ወደዚህኛው ደግሞ ተመለሱና፡ ይሄኛውን ይዛችሁ ወደ ማቴዎስ 1 እያመላለሳችሁ ተመልከቱት፡ ምን ታደርጋላችሁ? ያንን ወደ ኋላ ጎትታችሁ ወደዚህ ታመጡታላችሁ፦

**የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንደዚህ ነበር፡** (አሁን፡ ተመልከቱ፡ ሦስት አማልክት አይደሉም።) **ያኔ... እናቱ... ለዮሴፍ ታጭታ በነበረች ጊዜ፡ ሳይገናኙ፡ ከመንፈስ ቅዱስ ጸንሳ ተገኘች።** (ከእግዚአብሔር አብ አይልም፡ "ከመንፈስ ቅዱስ።" ኧሃ? )

**... ይህ ሁሉ የሆነው፡ ይህም...**

**ባልዋም ዮሴፍ፡... ጻዲቅ ሰው ሆኖ፡... እሷን ይፋዊ ምሳሌ ለማድረግ ፈቃደኛ ስላልሆነ፡ በድብቅ ሊተዋት አሰበ።**

**... በእነዚህ ነገሮች ላይ፡... ሲያስብ ሳለ... እነሆ የጌታ መልአክ፡ በሕልም ታየው። የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ሚስትህን፡ ማርያምን ለመውሰድ... አትፍራ፡ አለው፡- ከእርሰዋ የተፀነሰው ከምን ነውና**... (ከእግዚአብሔር አብ ነውን? )... **ከመንፈስ ቅዱስ ነው።**

225 "አባቱ እግዚአብሔር አብ፡" አልነረበረም ወይ። ይህን የምናገረው ከጥምቀት ጋር ስለሚያያዝ ነው። አያችሁ? "አባቱ እግዚአብሔር አብ፡" ይመስለኝ ነበር። እንግዲያውስ፡ መንፈስ ቅዱስ እና እግዚአብሔር አብ አንድ ናቸው፡ ካልሆነ ግን ሁለት አባቶች ነበሩት፥ እንዲህ ከሆነም ዲቃላ ልጅ ነው፡ እኛስ የምንከተለው ምን አይነት አምላክ ነው? እምም? አያችሁ?

በ**ነቢይ... ከጌታ ዘንድ... እነሆ፡ ድንግል ትፀንሳለች... ልጅም ትወልዳለች፡...**

**... ስሙንም፡** ኢየሱስ **ይሉታል፡...** ተብሎ **የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ነው**፡... (ትክክል ነው? )... እርሱም፡ አማኑኤል **ይባላል፡ ትርጓሜውም... እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው።**

226 እንግዲህ፡ እዩ፡ ማኅተሙን ወደ ኋላ ሲከፍተው፡ የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ሙሉ፡ ወደኋላ ምንድን ነው? ማን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ። ጴጥሮስ በጴንጤቆስጤ ቀን የተናገረው ነገር ነው። ሌሎቹም ሁሉ የተናገሩት ነው።

227 እርግጥ ነው፡ እነዚያ የሮማውያን መንጋ መጥተው እንዲህ ማለታቸው አይቀርም፡ "ኦህ፡ በፍፁም! ሦስት አማልክት ሊኖረን ይገባል። እኛ... " በዚህ ሰዓት ላይ አሰር ሺዎች አሏቸው፥ ማርያም እና ቅዱስ ሴሲሊያ፡ እና ቅዱስ ማርቆስ፡ እና ቅዱስ **እከሌ-እና-እከሊት** አሏቸው። እና በሜክሲኮ ከተማ ውስጥ አምስት መቶ እና ከዚያ በላይ ያላቸው ይመለኛል። አንዲት ሴት ከጥቂት ጊዜ በፊት በአንዳንድ ፍቅረኛዎቿ ተገድላ ነበር፡ እና በሷ ላይ ተጣልተው ገደሏት፡ ስለዚህ እርሷን ቅድስት አደረጉአት፡ ሰዎችም በእሷ ፊት ኃጢአታቸውን ይናዘዛሉ፡ ሌላም ያደርጋሉ። መናፍስታዊነት!

228 ከዚያም የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ብለው የሚጠሩትን ይዘው መጡ፡ "ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ፣ ሰማይንና ምድርን ጠባቂ፡ እና—እና በቅድስት የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አምናለሁ። በቅዱሳን ምልጃ፡ በቅዱሳን ተራዳኢነት አምናለሁ።" ፕሮቴስታንት በእግዚአብሔር መሐላ፡ በቅዱሳን ተራዳኢነት እንደሚያምን ሲምል። መናፍስታዊነት ነው! አያችሁ? ከዚያም ሄደው ያደርጉታል፡ አዎን፡ ምክንያቱም ቤተክርስቲያኒቱ ብላለችና። (አምላክ ሆይ፡ የማውቀውን

በማወቄ ምንኛ ደስ ብሎኛል! የማውቀውን በማውቄ እንዴት ደስ ይለኛል!) ከእግዚአብሔር ርቀው ወደ ጨለማ ወጥተው፡ ራሳቸውን እያተሙ መሆናቸውን አያውቁም። ልትነግሯቸውም አትችሉም፡ በፍጹም አያዩትምና።

229 መጠየቅ እፈልጋለሁ... ማንም ይህን መናገር የለበትም። ቢያንስ አስራ አምስት ወይም ሃያ ሰዎች፡ እዚህ ተቀምጠው፡ እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆንኩ በማሰብ ጥፋተኛ ነበሩ። እንዴት ሊያስቡ ቻሉ? እግዚአብሔር "መንፈስ ነው" እስኪነግረኝ ድረስ በጣም ይዤባቸው ነበር። ሰዎቹም፡ እንዲህ አልኩ... እነዚያ ሰዎች፡ እያንዳንዱን ቃል ያምኑኛል፡ እንዲህ አልኩ፡ "እንዲህ ከነገርኳችሁ፡ ታዲያ **እንዴት** ታምኑኛላችሁ? " ከዚያም ወደ ቃሉ ውስጥ ስንገባ፡ ያኔ መረዳት ጀመሩ፡ እንዲህ አሉ፡ "አዎን፡ ልክ ነው፡ እናምንህም ነበር ወይም አንተን መሰማት ነበረብን።" አያችሁ አይደል?

230 እንደውም በትክክል እኛ ትክክል ነን ብለው፡ በቅንነት አሰበው ነበር። አያችሁ? እና ከመካከላቸው አንዱ መንፈስ በእናንተ ላይ ከደረሰ፡ ከያዛችሁ፡ አያችሁ፡ በፍጹም ታምኑታላችሁ። ማንም፡ ምንም ቢላችሁ... አይገደኝም። አያችሁ? ቃሉ የቱንም ያህል ቢናገር፡ ምንም ይሁን፡ በምንም መንገድ አታምኑትም፥ ትቀጥላላችሁ። "እናንተ እንደዚያ መሆን ከፈለጋችሁ፡ ቀጥሉ፡ እኔ የራሴ መንገድ አለኝ።" አያችሁ፡ ያ የሚያሳየው፡ በተሳሳተ መንፈስ መቀባታችሁ ነው።

231 የእግዚአብሔር መንፈስ ሁሌ-... እንግዲህ፡ እናንተ፡ "አንተስ፡ ወንድም ብራንሃም? "

232 ማናችሁም እጠይቃለሁ... ማንም ሰው ትክክል እና ስህተት የሆነውን እንዲያሳየኝ ሁል ጊዜ ዝግጁ ነኝ፡ ነገር ግን ከቃሉ መሆን አለበት። አይችሉም... ከቃሉ ዘንድ መምጣት አለበት! ስለዚህ እነዚህ ማኅተሞች የሚከፈቱበት ቦታ ያ ነው። እና ደግሞ በምንም አትጨነቁ፡ ማሕተም ከሆነ ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ድረስ በራሱ ይገልጠዋልና። ስለዚህ ማኅተሞች ናቸው። እንግዲያውስ አትወዱትምን?

እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ
ቀድሞ ስለወደደኝ
መዳኔንም ገዛሁ
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

233 አንገታችንን ዝቅ እናድርግ። እዚህ ካላችሁ ሰዎች መካከል እርሱን የማታውቁት፡ ዛሬ ግን በልባችሁ እሱን መቀበል የምትፈልጉ ስንቶች አላችሁ? ታውቃላችሁ አይደል፡ መሰውያው ፊት በመቅረብ አምናለሁ፡ በእውነቱ አምናለሁ። በጣም ጥሩ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ግን ለመዳን ወደ መሠዊያው ሄደው አያውቁም፡ በልባቸው አምነው ይቀበላሉ። ስንቶቻችሁ በመጽሐፍ ቅዱስ መንገድ ትመጣላችሁ፡ "ያመኑት ሁሉ ተጠመቁ"? ዛሬ ስንቶች ታምናላችሁ፡ ከዚህ በፊት በመንገዳችሁ ሁሉ "መሳሳታችሁን" በአደባባይ በግልጽ ያልመሰከራችሁ፡ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛችሁ መቀበል የምትፈልጉ ስንቶች ናችሁ? እጆቻችሁን ከፍ አድርጋችሁ ራሶቻችሁን ዝቅ አርጉና፡ እንዲህ፡ "በሉ... "

234 እግዚአብሔር ይባርክህ። እግዚአብሔር ይባርክሽ። እግዚአብሔር ይባርክህ። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ አንተም። ከኋላ ያለሽው፡ እግዚአብሔር ይባርክሽ። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ አንቺም። ከኋላ ያለሽው፡ እግዚአብሔር ይባርክሽ። "አሁን እምናለሁ።" እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ከኋላ ያለኸው ሰውዬ እግዚአብሄር ይባርክህ። አሁን፡ **እዚህ** ሳይሆን በልባችሁ ውስጥ፡ ለእግዚአብሔር፡ በአደባባይ፡ ምስክርነታችሁን እየሰጣችሁ እንደሆነ አስቡ፡ "ጌታ ሆይ፡ በመጨረሻው ሰዓት ላይ መሆናችንን አውቄአለሁ። በቅቶኛል።"

235 ባለፈው ቀን እዚ ከተማ ውስጥ ካለ አንድ ጓደኛዬ፡ ዶክተር ሳም አዲር ጋር እየተነጋገርኩ ነበር። ቢሮ ውስጥ ተቀምጠን ነበር። እና "ሳም፡ ትንሽ ጋዝ ነገር በዝቶብኛል፡" አልኩት።

"በልብህ ዙሪያ? ጋዝ መሆኑን እንዴት ታውቃለህ፡" አለኝ?

እኔም "አዎን፡" አልኩት።

236 እርሱም "ይህ የልብ—ል—የልብ—የልብ ህመም ትሮምቦ—የልብ ህመም ሊሆን ይችላል፡" አለኝ። አልኩትም... (ይቅርታ።) "የልብ ህመም ሊሆን ይችላል፡" አለኝ።

237 "አሁን፡ ይህ እዚያ መኖሩ እንዴት ታውቃለህ፡" ብዬ ጠየቅኩት? "እስቲ ልይህ፡" አለኝ።

መረመረኛና፡ "አይ፡ አንተ ምንም ችግር የለብህም፡" አለኝ።

238 "ሳም፡ ይህ በተነሣ ቁጥር... " እለዋለሁ፡ እኔ ሃምሳ ሁለት አመቴ ነው፡ እና ሳም ከእኔ ትንሽ ይበልጣል። እኔም እንዲህ አልኩት፡ "ሲነሣብኝ፡ ሳም ሆይ፡ ላለፉት ሰላሣ ዓመታት ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ያምኑ ዘንድ ሰርቻለሁ፡ ይህ ሁሉ ጊዜ የሰራሁት ለእርሱ እና ብቸኛ ለሆነው ውዴ ነበር፡ እሱ ሲመጣ ለእኔ ምንም ለውጥ አያመጣም፡ ወደ ቤት እሄዳለሁ።"

239 "ቢሊ፡ ታውቃለህ፡ ትልቁ ነገሬ ከየት እንደማገኝ ታውቃለህ? ለሌላ ሰው የሆነ ነገር ሳደርግ ነው፡" አለኝ።

"እውነተኛው ሕይወት ያ ነው፡" አልኩት።

240 በዚህ ዓለም ውስጥ ርስት ያለህ ከሆንክ፡ ወዳጄ ሆይ፡ ፈራሽ ርስት ነው። እኛ ግን የማያልፍ ርስት እንቀበላለን። የጠፋው ልጅ ሄዶ ርስቱን ተወ፡ ከእርሱም ጋር ተካፈለ። ተመልሶ ሲመጣ፡ ርስቱ—ርስቱ ረክሷል። ከራስህ ሸሽተህ ከሄድህ ግን፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ እንደዚያ አይደለም፡ የማይጠፋውን ርስት እንቀበላለንና። ይሄን መቀበል አትፈልጉምን? ዛሬ ጥዋት ርስታቸውን ለመቀበል የፈለጉ፡ አሥራ አምስት የሚያህሉ ኃጢአተኞች እጃቸውን ወደ ላይ አንስተዋል። ከመጸለያችን በፊት ሌላ ይኖር ይሆን? አዎን።

አሁን እጅግ በተረጋጋ ድምጽ፦

እወደዋለሁ፡ እ...

አሁኑኑ ሃሳባችሁን ወስኑ። እንደሚገባችሁ ከተሰማችሁ፡ ጊዜው አሁን ነው።

ቀድሞ ስለወደደኝ
መዳኔንም ገዛሁ

በ... (እግዚአብሔር ይባርክህ። እግዚአብሔር ይባርክህ... ? ... )

241 የሰማይ አባት ሆይ፡ በዚህ ጽሞና ውስጥ፡ ይህንን ጉባኤ ወደ አንተ እናመጣለን፡ ዛሬ ጠዋት በተዳከመ ሁኔታ ውስጥ ሆኜ፡ ጌታ ሆይ፡ ይህን መልእክት ወደ ህዝቡ ለማድረስ ሞከርኩ ይህም ስለምወዳቸው ነው። ጌታ ሆይ፡ እንዲሰሙት እፈልጋለሁ። እንደ መልሕቅ እንዲሆኑ እፈልጋለሁ። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ የተደረጉት እነዚህ ሁሉ ነገሮች በአጋጣሚ ብቻ እንዳልሆኑ እንዲያውቁ እፈልጋለሁ፡ አንተ ነህ፡ ጌታ ሆይ። እነዚህን ነገሮች የከፈትካቸው አንተ ነህ። እና፡ አቤቱ፡ ሁላችንም ከፊታችን ታላቅ ኢዮቤልዩ እንዳለ ይሰማናል።

242 እጃቸውን ላነሱት እጸልያለሁ። የተሳሳቱ መሆናቸውን አወቁ፡ ጌታ ሆይ። ምስኪኖቼ... ምናልባት በአንድ ወቅት ከአንድ ሰው የተወሰነ ገንዘብ ወርሰው ይሆናል፡ ግን ምን ጠቀመ? የት እንደጠፋም አያውቁትም፡ በቀላሉ ይጠፋልና፡ ምክንያቱም ይህ የሚበላሽ ርስት ነው። ለሌላ ሰው ቢያወርሱትም፡ እንደገና ይበላሻል።

243 እኛ ግን የማይጠፋ ርስት አለን፡ እርሱም፡ መዳን፡ ቤዛነት፡ እንደገና ወደ ኤደን ገነት መመለስ ነው። ጌታ ሆይ፡ ስናስበው፡ እንደ አዳምና ሔዋን ወደ ኋላ ተመልሶ እዚያ መኖር የማይፈልግ ማን ነው? ምግባችን በየቀኑ ይሰጣል፡ የሰማይ አባት ሁል ጊዜ በመንገድ ላይ ከእኛ ጋር ይነጋገራል፡ ያን ታላቅ ብርሃን በፊታችን ሲሄድ እናያለን። አንበሳና ተኩላ አብረው እየበሉ፣ ኮርማ ጭድ ይበላል፣ አንበሳውም አብሮ ይበላል፥ አሁን እርስ በርሳቸው ሲበላሉ፥ ወይም አንበሳ ወይፈኑን ሲበላ፥ ተኩላም ወይፈኑን ሲበላ፡ ያገኙትን ይበላሉ። ያኔ ግን እንዲህ አልነበረም። ታላላቅ እእዋፋት ይበሩ ነበር። ሐዘን አልነበረም። በተሰፋዎቻችን ላይ የምናልፍበት ምልክት በጭራሽ አይኖርም። እዚያው መንገድ ላይ ልጆቻችንን፡ የምንወዳቸውን ሰዎች እናያለን። አምላክ ሆይ፡ እንዴት ያለ ቀን ነው! እንዴት ያለ ቀን ነው! እዚህ ምድር ላይ ምንም ብንቀበል፡ እነሆ—እነሆ—ሁሉም ነገር ጠፊ ነው፡ ያ ግን አይጠፋም።

244 እግዚአብሔር ሆይ፡ እዚህ ምድር ላይ፡ እጃቸውን ያወጡትን ሰዎች ላነጋግራቸው ፈጽሞ አልችል ይሆናል። አላውቅም። ተስፋ አደርጋለሁ። ካልሆነልኝ ግን፡ እንግዲያውስ፡ ጌታ ሆይ፡ እዚያ ባለው ዱካ ላይ እንድንገናኝ ፍቀድላቸው። ያን ጊዜ እንዲህ ይላሉ፡ “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ይህ ታላቅ ነገር ከመሆኑ በፊት በምድር ላይ ሳለን፡ አንድ ቀን ማለዳ እየተናገርክ ነበር—በሸክላ ዕቃ ውስጥ ስለተጠበቁ ማኅተሞች መከፈት ስትናገር ታስታውሳለህ? እርሱ ወደ ሸክላ ዕቃዬ የመጣው ያን ጊዜ ነበረ፡ ያን ቀን ማለዳ እጃቸውን ካነሱት አንዱ ነበርኩ። ኦህ፡ በዚያ በመገኘቴ እጅግ ደስ ይለኛል።”

245 እኔም እላቸዋለሁ፡ “ወንድሜ፡ እህቴ፡ እኔም፡ ያኔ በመገኘቴ ደስ ይለኛል። አሁን በሁሉም ለዘመናት አብረን ህብረት እያደረግን አለን።”

246 አባት ሆይ፡ ባርካቸው፡ የአንተ ናቸውና። አንተም ብለሃልና፡ “አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም። አብም የሚሰጠኝ ሁሉ ይመጣል፥ አንዳቸውም አይጠፉም።” ስለዚህ እኛም—አባት ሆይ፡ ስለዚያ፡ እናመሰግናለን። አሁን መጥተው የመዳናቸውን ቀብድ ይቀበሉ እንጂ፡ ወደ ቤተ

ክርስቲያን አባልነት አይወሰዱ። ቀብድ ግን መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል አዲስ ልደት እንጂ፡ የቤተክርስቲያን-አባልነት መቀላቀል አይደለም። አንተን ይቀበሉ፡ አባት ሆይ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ለእጆችህ አደራ ስጠናቸው። ኣሜን።

247 ለእነዚህ መሀረቦችም፡ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ በእነዚህ መሀረቦች ላይ እጸልያለሁ፦ ጌታ ሆይ፡ ችግረኞች ለሆኑት ሁሉ፡ ትባርካቸው ዘንድ እንጠይቅሃለን፡ በዊልቼር ላይ ለተቀመጠችው ይህች ምስኪን ሴትም እንዲሁ።

248 ከዚህ ታላቅ ስብሰባ በኋላ፡ አባት ሆይ፡ መንፈስ ቅዱስህ በእኛ ሲንቆረቆር፡ ቃሉ ወደ ታች ሲወርድ እና በሰዎች ልብ ውስጥ ስር ሲሰድድ እየተሰማን ነው። መቼም አይረሱትም፡ ጌታ ሆይ። እነዚህን ነገሮች በሰሙ ቁጥር ማኅተሞች እንደተከፈቱ ያስባሉና። አሁንም፡ ጌታ ሆይ፡ እያንዳንዱ በአእምሮው እንዳይደናቀፍ፡ እነዚያ ማኅተሞች ምን እንደነበሩ እንድናውቅ እርዳን፡ እግዚአብሔር የገለጠልን ማኅተም፡ እግዚአብሔር እንደሆነ “የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል” መሆኑን ይወቁ።

249 የታመሙትን እና የተጎዱትን ሁሉ እንድትፈውስ እንጸልያለን። ይሁን፡ ጌታ ሆይ። መንፈስህ ህያው ነውና። በህንጻው ጀርባ ላይ ኃጢአተኛን ማዳን ከቻልክ፡ በዚያም፡ የታመመውን ሰው መፈወስ ትችላለህ። ጌታ ሆይ፡ ይሁን እንድትለን፡ እና እነዚህ መሃረብ ባለቤት የሆኑትን ዛሬ እዚህ መድረስ ያልቻሉትን እንድትፈውስ እጸልያለሁ። ሁሉንም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አደራ እንሰጥሃለን። ኣሜን።

250 ለጌታ አደራ የሚሰጥ ብላቴና የያዙ ሰዎች መኖራቸውን እምናለሁ። ህጻኑን የያዘች ሴት ህንጻው ውስጥ አለች? አሁን ማምጣት ትችላላችሁን? ህጻኑን አሁን አደራ መስጠት እንፈልጋለን። አይደለም፡ ጨቅላ መሆን አይጠበቅበትም፡ አምጡት። (ከቻላችሁ አንድንድ አገልጋዮች ይመጡና ከጎኔ ይሁኑልኝ።) ስንት አመቱ ነው? ሁለት ዓመት ከስድስት ወር። ስሙ ማን ነው? ስኮት? ስኮት ፎርድ፡ ትንሹ ስኮት ፎርድ፡ የአራት ዓመት ከስድስት ወር ልጅ፡ ዛሬ ጠዋት ለጌታውና ለመድኃኒቱ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ አደራ መስጠት ይፈልጋል። እናቱ ታመጣዋለች። (ወንድሜ፡ ፊት ለፊት፡ ና።)

251 ቸር ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት ይህንን ህፃን አደራ ለመስጠት፡ ወደ አንተ እናቀርበዋለን። በዚህ ብላቴና ላይ፡ እጆቻችንን ጭነን፡ ኢየሱስን ከመቃብር ያስነሳው ሃይል ይህን ትንሽ ልጅ ህይወት እንዲሰጠው እንለምናለን። እግዚአብሄር ሆይ፡ ጉልበትና ጤና ይብዛለት። ጌታ ሆይ፡ ስለ ክብርህ የሚኖር፡ ይሁን። ይህን ህጻን ለመርዳት እንዴት እጅግ ተዘጋጅተሃልና፡ እኛም ስለ እሱ እናመሰግንሃለን። ዘወትር ከዚህ ከብላቴናው ጋር ትሆን ዘንድ ጸሎቴ ነው። ከቤተሰቦቹ፡ ከወዳጆቹ ጋርም ሁን። እናም... ጌታን ለሚወዱት ሁሉም ነገር ለበጎ እንደሚሠራ አውቀናል ተምረናልም። እነዚህ ነገሮች አንዳንድ ጊዜ ሰዎችን ወደ አንተ ያቀርባሉና። የምንጠይቃቸውን በረከቶች እንድትሰጠን እጸልያለሁ። አሁንም፡ አባት ሆይ፡ ቃልህን በመታዘዝ፡ ይህን ትንሽ ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለአንተ አደራ ስጥተናል። ትንሿ መንፈሱን፡ ነፍሱን፡ እና ሥጋውን ተቀበልና፡ ለክብርህ ተጠቀምበት። ኣሜን።

252 እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እህቴ። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ህጻን ሰኮት። ስለዚህም ጌታን እጅግ እናመሰግናለን!

253 አሁን፡ የሚጠመቁት እነማን ናቸው? ለመጠመቅ የተዘጋጁ ሰዎች እንዳሉ፡ አምናለሁ። ለዚያ እየተዘጋጀን ሳለ፡ እንዘምር... ምን ማድረግ እንደምንችል እነግራችኋለሁ፡ እንዘምር... ወንድም ኔቪል እንዲያጠምቃቸው እፈቅድለታለሁ። መልካም እንደሚሆን አውቃለሁ። በጣም ጥሩ፡ ወዳጄ፡ ወንድም ኔቪል።

254 ጌታን የምትወዱ፡ “አሜን” በሉ። [ጉባኤው “ኣሜን፡” አለ።—አርታዒ።] ለእኔስ ትጸልዩልኛላችሁን? [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።] አሜን። አሜን።

61-0618 ራእይ፡ ምዕራፍ አምስት ክፍል ሁለት
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org